# አሻራ

ልዩ ዕትም - መስከረም ፪ ሺህ ፭ ዓ.ም

# አንዳርጋቸው ጽጌ

ፕ/ር አለማየሁ ገብረ ማሪያም

አርቲስት ታማኝ በየነ

ወ/ሮ እስከዳር ጽጌ

ኮሜዲያን ክበበው ገዳ

# AL ANDALAS CAFE

እድሳቱን አጠናቆ በተለመደው ቅልጥፍናና ትህትና
ደንበኞቹን ሊያስተናግድ ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል!!!



የኢትዮጵያ ቡና ፤ ሽሮና የተለያዩ
ቅመማቅመሞች አሉን!
ምርጥ እንጀራም ያገኛሉ!

**127 HALDON ST,**
**LAKEMAB**
**TELE (02) 97589078**

# አሻራ

## ቃለ ምልልሶች

ወ/ሮ እስከዳር ጽጌ — ገጽ 6

ፕ/ር አለማየሁ ገ/ማሪያም—ገጽ 8

አርቲስት ታማኝ በየን -ገጽ 10

ኮሜዲያን ክበበው ገዳ -ገጽ 21


**አዘጋጆች**

ሳምሶን አስፋው
አቢይ አፈወርቅ

**Email:** quatero@gmail.com
**Email:** abiywork@yahoo.com.au


## መጣጥፎች


ገጽ

**አንዳርጋቸው ጽጌ ልዩ የኢትዮጵያ አፈር** ④

...የአንዳርጋቸው ጠላፊዎችና አሳሪዎች የጀግና መንፈስ የላቸውም እንጂ በክብር የሚጠብቁት ልዩ እንቋቸው በሆነም ነበር። ሚኒልክ የጎጃሙን ንጉስ ምርኮኛቸውን የተንከባከቧቸው በክብር በመጠበቅ ነበር። ...

**ከጸጋዬ ገብረ መድህን አርአያ**

**የመለስ ጂዮ-እስትራቴጂ "ትሩፋቶች" እና አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት በአፍሪካ ቀንድ** ⑫

... በቀይ ባህር "ጠረፋችን" ዛሬ ኢራኖችም እስራኤሎችም አሉ ተብሏል። አጃኢብ! የሚያሰኘው ግን ኤርትራ ሁለቱን ተፈላላጊ ጠላቶች ጎን ለጎን ማስተናገድ መቻሏ ነው። ...

**ዮሱፍ ያሲን (ኖርዌይ-ኦስሎ)**

**ሰቆቃ በወያኔ እስር ቤቶች** ⑯

...በአፍና አፍንጫቸው አካባቢም እንዲሁ ደም ፈሷቸዋል። "እራሳቸውን ሰቅለው ገደሉ" የተባሉት የአቶ አበራ አስከሬን ያረጋገጠው አሟሟት ይህን የመሰለ ነበር። ...

**ከወንድማገኝ ጋሹ ( ለንደን)**

**አሸባሪ ብዕሮች** ⑰

... "ለመሆኑ ሰርካለም ፋሲል ላይ ለምን እንዲህ ጨከኑባት? " የሚል ነበር የማርቲን ጥያቄ። እኝህ ታላቅ ሰው ይህን ጥያቄ ለምን እንዳነሱልኝ አሁን ነው የተገለጠልኝ።...

**ክንፉ አሰፋ (አምስተርዳም)**

**ስለ ዞን 9 ጦማሪያን ...** ⑲

**አንዳርጋቸው በኔ እይታ** ⑳

**የመጽሃፍ ቅኝት** 22

# ትንሽ ግዜ ብትሰጡን! አዘጋጆቹም የምንለው አለ

በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የተፈጸመው ድንበር ዘለል አፈና እንደ አብዛኛው ነጻነት፤ ፍትህና ሰላም ናፋቂ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አስቆጭቶናል! አብግኖናል!። በዛው ቅጽበት ደግሞ፡- አገዛዙ አቶ አንዳርጋቸውን ለማጥመድ እንቅልፍ አጥቶ አንዴ በምድር አንዴ በአየር የተሯሯጠው ለምንድነው? የሚል ጥያቄ አጫረብን። ለጥያቄው መልስ ለመሻት ደግሞ የአቶ አንዳርጋቸውን ማንነት በቅርብ ከሚያውቋቸው ሰዎች መረዳት ግድ አለ። ይህን ሃሳብ ይዘን አቶ አንዳርጋቸውን የምትዘክር አንድ ልዩ መጽሄት ለማዘጋጀት ተነሳን።አንዳርጋቸው የምትል።

ለመጽሄቷ ግብአት የሚሆኑ ስራዎች በማሰባሰብ ላይ ሳለን ደግሞ ሌላ ጥያቄ ብቅ አለ። መጽሄቷ ቀጣይነት ሊኖራት የሚችልበት መንገድ ቢፈለግስ? የሚል፤ አዎ! አቶ አንዳርጋቸውን መሰል በርካታ ጀግኖች አሉንና አቅም በፈቀደ በየተራ እንዘክራቸው ዘንድ ዓለምን። የናንተም ይሁንታ ከታከለበት ማለታችን ነው ። ለመጽሄታችን ስም ስናፈላልግ ሰነበትን።አላማችንን የሚገልጽ ስም። በኋላም “አሻራ” ብቅ አለች። ወደድናት።

እውቅና ለመስጠት ንፉግ ሆነን እንጂ በዚህ ትውልድም ቢሆን የገድል አሻራቸው ከወርቅ ጸዳል ፈክቶ የሚያበራ ጀግኖችን አላጣንም። የ “አሻራ” መጽሄት ዓብይ አላማም ይኸው ነው። ለጀግኖቻችን እውቅና መስጠት። ታሪክና ገድላቸውን መዘከር።ለተተኪው ትውልድ ...።

ብዙዎቻችን አባቶቻችን እንቢኝ! ለነጻነቴ፤ እንቢኝ! ለመብቴ፤ እንቢኝ! ለሃገሬ ብለው፤ ቅጠል በጥሰው ጎርሰው፤ አሸዋ ምሰው ለብሰው፤ ድንጋይ ተንተርሰው ያቆዩልን ነጻነት ... ! እያልን በቃልም በብዕርም ገድላቸውን ደጋግመን እንገልጻለን ። በብዕር ሳይወሰኑ ውርሰ ገድሉን በግብር የገለጹት ግን ጥቂቶች ናቸው።ከጥቂቶቹ አንዱ ደግሞ አቶ አንዳርጋቸው ናቸው።

በመሆኑም አሻራ አቶ አንዳርጋቸውን ይዛ ብቅ ብላለች ። በርቱ ካላችሁን እንበረታና እንቀጥላለን። ጀግኖቻችንንም እናበረታታለን። የመጽሄታችንን ውልደት አስመልክተን ይህን ያህል ካልን ይበቃል። ቀጠል አድርገን “እጅ ከምን..?” ሳንባል በፊት እኛው ቅርቅባችንን እናስተዋውቃለን። ከዚያ በፊት ግን በአቶ አንዳርጋቸው ዙሪያ ልዩ መጽሄት ለማዘጋጀት መነሳታችንን በመግለጽ፤ ለመጽሄቷ የበኩላቸውን ሥራ ያበረከቱ ዘንድ ያቀረብናላቸውን ጥያቄ በሙሉ ፈቃደኝነት ተቀብለው ለተባበሩን ወገኖች ሁሉ ከልብ የመነጨ ምስጋና ልናቀርብ እንወዳለን።

ይህቺ እትም በዋናነት ከአቶ አንዳርጋቸው ጋር ታቆያቸኋለች። አገሪቷ ዘርን የፖለቲካ መሰረታቸው ባደረጉ ኃይሎች ስር ከወደቀችበት ቀዳማይ ምዕራፍ ጀምሮ እንደ አገር የገጠማትን ፈተና ሲተነትን፣ መጪውን አደጋ ሲያመላክትና የሚያዋጣውን መንገድ ሲመክር የዘለቀውን የቁርጥ ቀኑን ብዕረኛ የፀጋዬ ገ/መድህን አርአያን ፅሁፍ ይዘናል። ጸጋዬ በዚህ መጣጥፉ የአንዳርጋቸው ጽጌን የረጅም ዘመናት የፖለቲካ ጉዞ በትዝታው እያዋዛ ያወጋናል። አገሪቱ የምትገኝበትን ምዕራፍ ከሌሎች አገራት ታሪክ ጋር እያናጸረም የአንዳርጋቸውን ሌጋሲ እንድናስብ ይሞግተናል። "አንዳርጋቸው ልዩ - የኢትዮጵያ አፈር ነው"ም ይለናል። ምን ማለቱ ይሆን? በአንክሮ ልታነቡት ይገባል።

በቃለ ምልልስ አምዳችን አራት እንግዶች ይዘናል። የአቶ አንዳርጋቸው ታናሽ እህት እስከዳር ጽጌ ስለታላቅ ወንድሟ ያላትን ትዝታ አካፍላናለች። ከሷ ጋር ስለነበራቸው ልዩ ቅርርብ፤ ስለቤተሰባዊ ህይወቱ፣ ስለባህሪያቱና አመለካከቱ በጊዜ ሀዲድ እየተንሸራሸረች ታወጋናለች።አንብቧት።

ለእውቁ የህግ ምሁርና ጦማሪ ለጥ/ር ዓለማየሁ ገብረማርያምም "የአቶ አንዳርጋቸው አፈና ከህግ አንጻር እንዴት ይታያል?" የሚልና ሌሎችም በርካታ ጥያቄዎችን አቅርበንላቸዋል። ከሶስቱም አገራት አንጻር ጠቃሚና ሰፊ ሙያዊ ትንታኔ ሰጥተውናል። አፈናው ስለፈጠረው የፖለቲካ ድባብም የሚሉን አላቸው።

እገታው በፈጠረው ህዝባዊ ቁጣ፣ በአገዛዙ ሰፈር እየተሞከረ ባለው የፕሮፖጋንዳ ዘመቻና በመሰል ወቅታዊ ጉዳዮች ዙርያ ያለውን ምልከታ እንዲያካፍለን አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነን ጋብዘነዋል።አብራችሁት ቆዩ።

አሻራ ተወዳጁን ኮሜዲያን ክበበው ገዳንም ይዛለች። በቅርቡ ስላቀረባቸው ቀልዶችና ተያያዥ ጥያቄዎች ቀርበውለት መልስ ሰጥቷል።ባየሁትና በታዘብኩት ነገር ላይ ተመርኩዤ ቀልድ ከመስራት የሚያቆመኝ የለም! ይላል።

የተለያዩ መጣጥፎችና ጥንቅሮችም አሉን። እውቁ የምስራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ተንታኝ አምባሳደር ዩሱፍ ያሲን በዓለም አቀፉ የጸረ ሽብር ዘመቻ ዙሪያ ያለውን የኃይል ውግናና በኢትዮጵያ ያለው አስተዳደር በዘመቻው ስም እየፈጸማቸው ያሉትን ወንጀሎች ያስቃኙናል። ሀሳባቸውን በነጻነት በመግለጻቸው ብቻ የአገዛዙ ሰለባ መሆናቸው በስፋት እያነጋገረ ያለው የዞን 9 ጦማርያንን ህልምና ጉዞ በተመለከተም ከእስር ከተረፉ የዞኑ አባላት አንዱ ጆማኔክስ ካሳዬ ስለ ጓደኞቹና አንግበውት ስለተነሱት አላማ ያወጋናል።

ጋዜጠኛ ክንፉ አሰፋም የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስን የፈተና ጉዞና የጋዜጠኞቹን መከራ ይፈትሻል። በዘመነ ኢህአዴግ በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ የሚፈጸመውን ለህሊና የሚከብድ ሰቆቃ ለማስታወስ እንዲረዳን የሰብአዊ መብት ተሟጋቹን ጋዜጠኛ ወንድማገኝ ጋሹን እስቲ ከትውስታህ ብለነዋል። በአካል ተገኝቶ ምርመራ ካደረገባቸው የመብት ረገጣዎች መሀል የተወሰኑ ሰለባዎችን በናሙናነት አቅርቦልናል። በቅርቡ ለንባብ የበቃው የአቶ ኤርምያስ ለገሰን “የመለስ ትሩፋቶች” የቃኘ ስራም ይዘናል። መልካም ንባብ...!

# የ፪ሺህ ፯ ዓ.ም. የኪሳት የዓመቱ ምርጥ ሰው!

ምዕራባዊያኑ Person Of The Year ወይም Man Of The Year በማለት በአሮጌው ዓመት ፍጻሜና በአዲሱ ዓመት ዋዜማ ይፋ የሚያደርጉትን ሰው መምረጥ የጀመሩት ከዛሬ 85 ዓመታት በፊት እ. ኢ.አ. በ1927 ዓ.ም. እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

በታዋቂው የአሜሪካ መጽሄት በ"ታይም" የተጀመረው ይህ ሂደት በተለያዩ መገናኛ ብዙሀን እየተለመደ የመጣ ሲሆን እንደ አውስትራሊያ ባሉ አገራት የዓመቱን ምርጥ ሰው ይፋ የማድረግ ሥርዓት በጉጉት የሚጥበቅና በየዓመቱ ጃንዋሪ 26 ቀን የሚከበር ታላቅ ብሄራዊ ሥ/ስርዓት ሆኖ ቀጥሏል። በኢትዮጵያ ሚዲያዎች፣ በተለይም በድረ ገፆች ላይም እየተለመደ መጥቷል።

አንዳንዶች የዓመቱን ሰው በህዝብ ምርጫ ላይ ተመርኩዘው ይፋ ሲያደርጉ ፣ ሌሎች ደግሞ በራሳቸው መመዘኛ የዓመቱን ምርጥ ሰው ይሰይማሉ። እንደ ታይም ያሉ መገናኛ ብዙሀን ደግሞ በዓመቱ በበጎም ይሁን በክፉ ወይም በሌላ መልኩ ጎልተው የወጡ ሰዎችን ይሰይማሉ።

ታይም መጽሄት እ.ኢ.አ. በ1927 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ የዓመቱ ሰው አድርጎ የሰየመው ከኒውዮርክ /አሜሪካ ወደ ፓሪስ/ፈረንሳይ በቀጥታ የበረሩትን ቻርልስ ሊንድበርግን ሲሆን፣ በ1930 ዓ.ም. ማህተመ ጋንዲን፣ በ1935 ዓ.ም. ደግሞ ንጉስ ኃይለ ሥላሴን የዓመቱ ሰው በማለት የመጽሄቱ ሽፋን አድርጓቸዋል። የጀርመኑ አዶልፍ ሂትለር በ1938 ዓ.ም. የዓመቱ ሰው ተብሎ ሲሰየም ፣ የቀድሞው የሶቪየት ህብረት መሪ ጆሴፍ ስታሊንም እንዲሁ በ1939 ዓ.ም. የታይም የዓመቱ ሰው ሆኖ ተመዝግቧል።

እነዚህን ሁኔታዎች መነሻ በማድረግ ኢሳት (የዓመቱ ሰው ሳይሆን) "የ2006 ዓ.ም. የዓመቱ ምርጥ ሰው ማነው?" በሚል ለህዝብ ላቀረበው የምረጡ ጥሪ ወደ 3ሺ የሚጠጉ ሰዎች ምላሽ ሰጥተው ተሳትፈዋል። ከመራጮቹ መሀል ከ93% በላይ የሚሆኑት በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ሲሆኑ፣ ከአውሮፓ አገራት ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ታላቋ ብሪታንያና ስዊዘርላንድ ቀጣዩን ከፍተኛ የተሳታፊዎች ቁጥር ይዘዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአውስትራሊያና ደቡብ አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንም ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን ከኢትዮጵያም እንዲሁ ምርጫቸውን በኢሜል ያደረሱ ዜጎች ተመዝግበዋል። ጥቂት የማይባሉት ምርጫቸውን ከነምክንያታቸው የዘረዘሩ ሲሆን አንድ የዋሽንግተን ነዋሪ በዘጠኝ ሰከንድ ውስጥ ሀሳባቸውን መግለጽ በመቻላቸው  በአጭር አስተያየት ሰጪነት ቀዳሚውን ስፍራ ይዘዋል።

እጅግ በርካታ መራጮች በድምጽ መልዕክት ፣ በኢሜይልና በፌስ ቡክ የተሳተፉ ቢሆንም በፌስ ቡክ የተሳተፉ ሰዎችን አስተያየት በተገቢው ሰብስቦ ለማቀናበር ከጊዜ አንጻር ከአቅም በላይ በመሆኑና ማሰባሰቡም አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ በድምጽና በኢሜይል መልዕክቶች ላይ ማተኮሩ ተመርጧል።

በዚህም መሰረት በጽሁፍና በድምጽ ለኢሳት የ2ሺ 862 መራጮች ድምጽ ደርሶታል። በላቲን ፊደል ቅደም ተከተል መሰረት በትንሹ አስርና ከዚያም በላይ ድምጽ ካገኙት መሀል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።- ጋዜጠኛ አበበ ገላው፣ የአረና ፓርቲ አመራር አባል አብርሀ ደስታ፣ የግንቦት 7 ዋና ጸሀፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ የቀድሞው የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትር ዲኤታ አቶ ኤርሚያስ ለገሰ፣ የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል ወጣት ሀብታሙ አያሌው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ረዳት አብራሪ ሃይለመድህን አበራ፣ አቶ አባንግ ሜቶ፣ ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ፣ አክቲቪስት ታማኝ በየነና ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ አንጻራዊ ከፍተኛ ድምጽ አግኝተዋል። ከእነዚህም መሀል አክቲቪስት ታማኝ በየነ ከአጠቃላዩ ድምጽ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የመራጮች ድምጽ ያገኘ ሲሆን አበበ ገላውና ኃይለመድህን አበራ በተቀራራቢ ቁጥር ተከትለውታል።

ከ2ሺህ 862 ተሳታፊዎች መሀል 2ሺ 376 ድምጽ ወይም የመራጩን 83.02%  ድምጽ በማግኘት የኢሳት የ2006 ዓ.ም. የዓመቱ ምርጥ ኢትዮጵያዊ ሆነው የተመረጡት ሰው፤ የፊታችን ጥር 2007 ዓ.ም. 60ኛ ዓመታቸውን የሚይዙት፣ በ1960ዎቹ የተማሪዎች ትግል ተሳታፊ የነበሩት፣ ባለፈው ሰኔ 16 ቀን 2006 ዓ.ም. የመን ሰንዓ አየር ማረፊያ ላይ የታገቱት የግንቦት 7 ዋና ጸሀፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ሆነዋል። ኢሳት ለዓመቱ ምርጥ ሰው ያዘጋጀው ሽልማት ባልታወቀ ቦታና ባልታወቀ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙት ለአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ -በተወካይ አማካኝነት ተሰጥቷል።

# አንዳርጋቸው ጽጌ - ልዩ የኢትዮጵያ አፈር

ከጺጋዬ ገብረ መድህን አርአያ

በ1950 ዓ.ም. ደብረብርሀን በሚገኘው የሀይለ ማርያም ማሞ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስገባ የዓጼ ዘርአ ያዕቆብ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ጽጌንና ባለቤታቸውን በየቀኑ አያቸው ነበር። ወይዘሮ አልታዬ ዘወትር በቀኝ እጃቸው እየደገፉት እሱ ድክ ድክ የሚልም ትንሽ ልጅ አይረሳኝም። የየዕለቱ ትርኢት ስለነበር . . . . ብዬ አልፈዋለሁ።

ከዘመናት በኋላ እኔም አድጌና በመንግስት ስራ ኃላፊነት ቆይቼ ይህቺን አገር የሚያናውጡ ሰዎች ወደ ፖለቲካው መድረክ ሲመጡ በመጥረጊያ ከተጠረጉት የጥንት ጋዜጠኞችና የሚዲያው አመራር አባላት ጋር እዳሪ ስንጣል ያ ልጅ ይመስለኛል ከጦቢያ ቢሮ ያገኘኝ። አንዳርጋቸው ጽጌ ከመቼው በወያኔ መርከብ ተሳፍሮ ፣ ከመቼው ወርዶ፣ ከመቼው ወደ ተቃዋሚነት እንደተሸጋገረ የፖለቲካው ጉዞ ቅፅበት አልገባኝ አለ። የተቀላቀለው ቡድን አካሄድና ይልቁንም "አማራ" በተባለው የህብረተሰብ ክፍል ላይ ያለውን ግልጽ አቋም በመረዳት "የአማራው ህዝብ ከየት ወዴት?" የሚል መጽሀፍ ጽፎ ለህዝብ ሲያቀርብ እኔም ሆንሁ ብዕሩ እልፍ የሚጥለው ጓደኛዬ ሰውነት መልካሙ ጥርጣሬ ውስጥ ወድቀን ነበር። ስለዚህ ሰውነት (በብዕር ስምነት ይቆይና) "በኢትዮጵያዊነት ላይ የተወረወረ ቦምብ" በሚል ርዕስ የራሱን ቦምብ አፈነዳ። አንዳርጋቸው አስተያየት የመስጠት መብታችንን እየጠቀሰ በመሰረቱ ግን "አቶ ሰውነት ትክክለኛው ጉዳይ የገባቸው አይመስለኝም" ብሎ ከእኔ ጋር በጦቢያ ቢሮ (አክፓክ ነው እንባል የነበረው) ደስ የሚልና ምሁራዊ ቅባት የነበረበት ሙግት ገጠምን። ድብቁ ሰውነት ወጋችንን በአንክሮ ያዳምጥ ነበር። ሳያቋርጠን። እንዲያውም በዚያን ወቅት ወያኔ "ዴዶች" እየፈጠረ ስለነበር "አንድ ዴድ እንዲያቋቁም የመረጡት ካድሬ ይሆናል" ብለን አማነው። እሱ ከወጣ በኋላ። ምናልባትም እየመጣ የነበረውን የፕሮፌሰር አሥራትን መአህድ ለማኮላሸት - ወይስ ማጨናገፍ ልበለው - ልዩ ተልዕኮ ያለው አድርገንም አማነው። ጠረጠርነው ማለት ይሻላል።ይሁን እንጂ ያሸተተው አንዳች ግም ነገር ኖሮ አንዳርጋቸው የፖለቲካውን መድረክ ገልብጦ ወደ መንፈሳዊ ቤቱ ተመለሰ። እንግሊዝ አገር !

" ተዋግቶ የሸሸ ተመልሶ ወደ ትግሉ አውድ (ግንባር) ለመመለስ ሁልጊዜ ዕድል አለው" He who fights and runs away will live to fight another day, but he who is in battle slain will not live to fight again. አስተዋይ ፈረንጅ ነው እንዲህ ያለው። አንዳርጋቸው ወደ ግልጹ ዐውደ ፖለቲካ የተመለሰው ምቹ አየር በማሸተቱና ህልሙን የሚጋሩ ታጋዮች ብቅ ብቅ ባሉበት ሰዓት ነበር። ጠጠር መጣል - እጣነ ሞገር መውገር አላስፈለገም። በዘመነ ቅንጅት!

ከዚህ ልጅ ጋር መወያየት ደስ ይላል። እንደውም አንድ ቀን ለጥቂት ደቂቃዎች ተገናኝተን ወያኔን ፋሽስት በማለቱ ረገድ የተራራቀ አሳብ ማብራራት ጀምረን ነበር። በእኔ በኩል ይህን ድርጅት ፋሽስት ለማለት የፈለግሁት ኢሰብዓዊ አቋሙን ፣ ደም የማፍሰስ ሱሱን፣ ለህይወት አንዳች ዋጋ ለመስጠት ያለመፈለግ ዝንባሌውን . . . ለማሳየት ነበር። አንዳርጋቸው ደግሞ የተማሪው ፖለቲካ ፍሬ እንደመሆኑ ወደ ክላሲካል ትርጉሙ ለመሄድ ነበር የፈለገው። በነገራችን ላይ አንዳርጋቸው በቾኮላ ላይ ስለነበርና ጊዜም ስላልነበረው ስለፋሺዝም ብዙ ሳንወያይ ተለያየን። ጊዜ ቢኖረው ኖሮ "አብዮታዊ ዴሞክራሲ" ከቤኒቶ ሙሶሊኒ "አቫንቲ" እና ከፋሽዝም የተዳቀለ መሆኑን (ያው መጻህፍት በመጠቃቀስ) አስረዳው ነበር። የተማሪ ፖለቲካና የሶቭየት (ኢምፓየር) ቀኖናውያን እንደሚሉት "ቀኝ ክንፍ ፍልስፍና" (ኢዲዮሎጂ) አለመሆኑን ለማብራራት እሞክር ነበር። በነገራችን ላይ ሙሶሊኒ ሮጦ ከሂትለር ክንፍ ሥር ሳይወድቅ የምዕራቡ ዓለም መሪዎች (እነ ሩዝቬልትና የውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሐል) ፋሺዝምን እንደ ታላቅ የዓለም ፖለቲካ የዕድገት ማስረጃ አድርገው ያዩት ነበር። ፋሺዝም የመጣው እንደ ሬቮሉሲዮን ስለሆነ የቀኝ ክንፍ ፍልስፍና አይደለም። ይህ ክርክር ያልተፈጸመና በአጭሩ የቀረ ጭንጋፍ ሙግት ነው። አንዳርጋቸውን በዚህ ዓይነት ሙግት የምዘርር አይደለሁም። እሱ ላቅ ያለ አመለካከትና ትንፋሹ ሳይቀር ሕይወት ያለው ነው። በዓለም አቀፍ የቅንጅት ኮሚቴ ውስጥ አብረውት የሠሩ ዘመዶችና ወዳጆች አሉኝ። ይሳሱለታል። "አንዱ . . አንድዬ . . . አንዳርግ . . ." ይሉታል።

የቅንጅት አመራር አባላት በወያኔ ወጎኒ ዓለም በተወረወሩ ጊዜ በሳምንት ውስጥ ለቢቢሲ ሰባት ቀናት መግለጫ ሲሰጥ ሰምቼዋለሁ። በበሰለ አሳብ ፣ በጠራ ቋንቋና በጨዋ አንደበት። ይህ ብቻም አልነበረም ፤ በወቅቱ የአፍሪካ ህብረት ዓመታዊ ስብሰባ በአክራ ሲካሄድ የጋናን ሚዲያ በተለይ፣ እና የአፍሪካ መገናኛ ብዙሀንን በአጠቃላይ በቁጥጥሩ ስር አውሎ በኢትዮጵያ ላይ እየተካሄደ ያለውን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ ሰዕል በሚያስደንቅ አኳኋን ሲያቀርብ የነበረ ጀግና ነው። አንድ መቶ የፕሮፖጋንዳ ሰራዊት የማይችለውን የአትላስ ሽከም ብቻውን በአስገራሚ ሁኔታ ያከናወነ ልዩ ፍጥረት ነው። እኔ ደግሞ የዚህን ሥራ አስቸጋሪነት በልዩ ልዩ ገጽታው አውቀዋለሁ ባይ ነኝ።

"ተራራ አንቀጠቀጥን . ." የሚሉ የመዛርያ አምላኪዎችና ባሩድ ነካሾች ይህን ታላቅ ነፍስ - የኢትዮጵያ ነፍስና ከኢትዮጵያ ጎን የወጣ ልጅ - ከአስመራ እስከ ዱባይ . . . ከየመን እስከ ደቡብ አፍሪካ .... ከእንግሊዝ አገር እስከ አውስትራሊያና አሜሪካ ወዘተ ባሰማሯቸው የስለላና የአፈና ጓዶች አማካኝነት ዓለምን ሲያካልሉ ከርመዋል። ቁጥር ስፍር የሌለው ገንዘብም አፍስሰዋል። በመጨረሻም ዱባይ ፣ አስመራ፣ ደቡብ አፍሪካ ያሉት የቆስጠ ሴረኞች ... የምስራች ተባብለዋል። እነሆ ውቡ ወፍ ተጠምዷል። የትግሉም ሆነ የዓለምም ፍጻሜ ግን አይደለም። አይሆንምም። አንዳርግ የከፈለው ሰማዕትነት በሚቀጥሉት የኢትዮጵያ ትውልዶች በክብር ይወሳል። ለአዲሱ ዘመን አውራ ጀግና በማግኘታችን ልንኮራ ይገባናል። እግዚአብሄር ይከበር-ስለ አንዳርጋቸው!

አገሮች በታሪካቸው ትልልቅ ፈተና ያጋጥማቸዋል ። ሕዝብ በችግር ሰዓት ይጠራራል። እንደዚህ ላስቀምጠው። - በጭንቅ ሰዓት ፣ በፈተና ጊዜና ቀን የጎደለ በሚመስልበት ወቅት ከማዕበሉ ጋር የሚታገልና ድልን የሚያስገኝ ፤ ካልተሳካም በድፍረቱ ፣ በልበ ሙሉነቱ ይህን ያህል የማይባል ረቂቅ ድልን የሚያቀዳጅ ሰው ይሻል። በደሙና በማይነገር - በማይበገር ጥንካሬው አማካይነት ወጀቡን የዋኘ ፣ ማዕበሉን ጸጥ ያደረገና የሚያደርግ ፤ ለዛሬው ትውልድ የነጻነት ብልጭታ ያሳየ (የሚያሳይ) ፤ ለመጪው ከውስጡ ብርሀኑ ቦግ ያለ የትግልን ችቦ የሚያቀብል (ያቀበለ) ሰው ይሻል።

የህንድ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀዋህርላል ኔህሩ በታላቁ የዓለም ሰው በማህተመ ጋንዲ (በአክብሮት ጋንቲጂ) ሥርዓተ ቀብር (በሂንዱ ልማድ ቀብር ሳይሆን የማቃጠል ሥርዓት ነው ያለው) ላይ ሲናገሩ የተጠቀመበትን አንድ ሐረግ ልሰርቅ አፈልጋለሁ። ለአንዳርጋቸው ጽጌ ለመስጠት! "ጋንዲ ልዩ አፈር ነው። ከእኛም ልዩ የሚያደርገው ልዩ አፈርነቱ ነው።" ብለዋል። እኔ ራሴ መንቀሳቀስ የማይሆንልኝና በማንኛውም የአገሪቱ ታሪክ ላይ ይህ ነው የሚባል አሻራ ለማሳየት የማይሆንልኝ ቧጋች ነኝ። ሰዎችን የማወቅ ዕድል ግን አለኝ። ጀግና ብቻ ሳይሆን ባንዳና ምንደኛም አውቃለሁ። ተነልቼ ይህን

የመሳሰለውን ወግ እጠርቃለሁ። አላጋንንም። አንዳርጋቸው እንደማናችንም ከአፈር - ከኢትዮጵያ አፈር ተፈጥሯል። እእ! ከኢትዮጵያ ልዩ አፈር! ስለዚህ ‹ልዩ ሐረግ› የኔህሩን ሽንት ይባርክ!

የአንዳርጋቸው ጠላፊዎችና አሳሪዎች የጀግና መንፈስ የላቸውም እንጂ በክብር የሚጠብቁት ልዩ እንቋቸው በሆነም ነበር። ሚኒልክ የጎጃሙን ንጉስ ምርኮኛቸውን የተንከባከቧቸው በክብር በመጠበቅ ነበር። ወያኔዎች ከፈሪ ልብ የተቆረጡ ፈሪዎች በመሆናቸው እንጂ አንዳርጋቸውን ያንን ያህል የስጋ ስቃይ ባላደረሱበት ነበር። ለትርሚት መላልሰው ባላቀረቡትና የደስታቸው ምንጭ ባላደረጉትም ነበር። እነሱ ዛሬ የሥጋ ቁስልና የመንፈስ ስቃይ የሚግቱት ሰው ነገ የታሪካቸው ፈርጥ የሚሆን ልዩ አፈር ይሆናል። ሃሌሉያ!

በአጠቃላይ አንዳርጋቸው የነጻነት ተጋድሎውን የተወጣ ፤ ምድራዊ መከራን፣ አካላዊና መንፈሳዊ ቅጣትን ሁሉ የተቀበለ፣ ትግሉን ለሌሎቻቸን በአደራ ያስተላለፈ ታላቅ ነፍስ ነው። ታላቁ ህንዳዊ ጋንዲ "ማሀትማ" ይባላል። "የተከበረ ነፍስ" ማለት ነው። የዓለም ጌታ እንዳለው ነቢይ በአገሩና በዘመኑ አይከበርም ሆነና አንዳርጌ የሚገባውን አክብሮትና አድናቆትን ጠላት በተንጣለለበት አገሩ ለማግኘት ባይችልም በውጪው ዓለም የተበተኑና የውስጡንም የሚወክሉ ወገኖች ሁሉ ህዝብ ለማንም ሰጥቶ የማያውቀውን ክብር ሰጥተውታል። የኢትዮጵያ ጆን አፍ አርከ፣ የኢትዮጵያ ማንዴላና ጋንቲጂ ብለውታል። ጠላቶቹ የአገር አጥፊዎች እየተዘባበቱበት፣ እየሰደቡትና እንደ "ጊኒ ፒግ" መላልሰው በቴሌቪዥን እያቀረቡት ነው። ልዩ ወፋችንን—ናይቲንግሌላችንን ባሰቡ ቁጥር መንፈሳቸውን የሚያሸብር አንዳች ስሜት ተጣብቷቸው ቆይቶ መያዙንና በእጃቸው መግባቱን ያለማመን ችግር ደርሶባቸዋል። "ሶባጅ - ሳቬጅ!"

ፍሬደሪክ ኤንግልስ ወዳጁና ጓዱ ስለነበረው ካርል ማርክስ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ የተናገረው ምስክርነት ትዝ ይለኛል። The best hated man ይለዋል። (ከሁሉ የበለጠ የተጠላ ሰው እንደማለት ነው።) በወቅቱ በተፈጠሩም ሆነ በኋላ በተነሱ ትውልዶች ዘንድ ግን ካርል ማርክስ The best hated man ብቻ ሳይሆን The best loved man ሆኗል። አንዳርጋቸው ጽጌ በእጃቸው በገባ ሰዓት ማራኪዎቹ ወያኔዎች የተሰማቸውን ደስታ ጣኣታቸውና የሴረኞች ሁሉ አባት የሆነው አምባገነን ከሞተበት ዕለት ጎዘን ጋር ማስተያየት ይቻላል። አዎን አንዳርጋቸው በወያኔዎች ለወያኔዎች የቀትር ጋኔን ነበር። የሚያስፈራ ነፍስ - እንኪያስ The most hated man ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ደግሞ The most loved man! ይታደለዋል እንጅ ...በዚህም መሰረት ይቀጥላል። ያ ልጅ ...አበበ አረጋይ ...በላይ ዘለቀና አሞራው ውብነህ፣ ጅማ ሰንበቶ፣ በቀለ ወያ፣ አብዲሳ አጋ ሲደመር ሲደማመር ቅዱስ ያሬድ፣ ዮፍታሄ ንጉሴ፣ ዶክተር ዓለመወርቅ . . . ነው። አላበዛሁበትም። ክብር ሁሉ አልከመርኩ በትም። ቢሆንልኝ ከነጋድራስ ተሰማ እሸቴ ጋር "እንደምን አድርጌ ከፍቼ ላውጣው" እያልኩ አቀነቅን ነበር።

ጀግኖች የኢትዮጵያ ወጣቶችና ጸጥ

> .... እነሆ ውቡ ወፍ ተጠምዷል።
> የትግሉም ሆነ የዓለምም ፍጻሜ ግን አይደለም።
> አይሆንምም። አንዳርግ የከፈለው ሰማዕትነት
> በሚቀጥሉት የኢትዮጵያ ትውልዶች በክብር ይወሳል።
> ለአዲሱ ዘመን አውራ ጀግና በማግኘታችን ልንኮራ
> ይገባናል። እግዚአብሄር ይከበር-ስለ አንዳርጋቸው!....

ወዳለው ዓለም የምትሸጋገሩ አእሩግ! ናፖሊዮንም ተማርኳል።ታላቁ ጄነራልና ጦረኛ መሪ። ያንን ታላቅ የጦር መሪና ገናና የዓለም ገዢ የማረከው እንግሊዝ ደግሞ ጀግንነትን የማድነቅ፣ ሰብዐዊ መብትን የማክበር ባህል - ድንቅ ባህል ባለቤት ስለሆነ አክብሮ ነበር የያዘው። ናፖሊዮን ከሴንት አልባ አምልጦ እንደገና ለመቶ ቀናት ፈረንሳይን መርቷል። ማን ያውቃል የዴስቲኒን አድራሻ! ማን ያውቃል የዴስቲኒን የፍጻሜ ምዕራፍ?

የዚህን ወጣት ታሪክ ከሥር መሰረቱ የሚያወጉ ወዳጆቹና የትግል ተካፋዮች እንዳሉ አያጠራጥርም። በመድረክና እንደኔም በመስኮቱ ንግግር ፣ ራቅ ብሎም በመሄድ የከፈለውን መስዋዕትነት በጨረፍታ ለምናውቀው አንድ መደምደሚያ ላይ እንደርሳለን። አንዳርጌ የሚከበር ፣ የሚወደድና በአእምሮው ትልቅነት ፣ በሰብአዊነቱና በአርቆ አሳቢነቱ - ማናቸውንም የነጻነት መስዋዕትነት ለመክፈል ባሳየው ቆራጥነቱ የሚደነቅ ነፍስ ነው። እንደሱ ያሉ ሰዎች ከጊዜያቸው በፊት መጥተው ፈተናን ሁሉ ይቀበላሉ። መንፈሱንና ስጋውን ለአምላክ እንዳስረከበ ደካማ ሰው እግዚአብሄርን የምለምነው አንድ ነገር አለኝ። ሲድራቅ ፣ ሚሻቅና አብድናጎን ከሚንቀለቀለው እሳት አራት ሰው አድርጎ በፍጹም አቸናፊነት ያወጣቸው አምላክ ምን ይሳነዋል? በወያኔ እስር ቤት የሚንገዋለል አንበሳ በሕልሜም በውኔም ይታየኛል። እናንተስ ጎበዝ! በክርስቶስ ላይ ያሾፉ፣ የሾህ አክሊል በራሱ ላይ የደፉበት ፣ እስኪደክማቸው የገረፉት፣ ጎኑን የወጉት የሰው አራዊትና አራዊት ሰዎች ሥዕል አይመጣባቸሁም? "ሶባጅ! ሳቬጅ!" "አኒማሌ" አል ጣልያን! ለወያኔዎች አንድ ምስጢር ልተውላቸው እወዳለሁ። "አንዳርጋቸው ጽጌ መንፈስ ነው።"

ይህን ትንቢት ተቀበሉኝ። አምላካችን ለዚች ሀገር እንደማዕዘን ድንጋይ ሆነው ሕዝቡን የሚያገለግሉ መሪዎች ይሰጠናል። የሰራዊት ጌታ የምህረት ተስፋ ነው። እንደ ድንኳን ካስማ የሆኑ አስተዳዳሪዎችና እንደ ጦር ሜዳ ቀስት የሆኑ የጦር አዛዦችን ይሰጠናል። ብርቱ የሆኑ ጀግኖችን እንጠብቃለን። ከላይ ከጸባዖት! ከመሬቲቱ ከኢትዮጵያ ማኅጸን።እነዚህ ደግሞ የኢትዮጵያን ጠላቶች ረግጠው ከመንገድ ጭቃ ጋር እንደሚለውሱ ያደርጋል - ማን? የኃያላን ኃያል! የጌቶች ጌታ! ትዕቢተኞች ይዋረዳሉ። ዕብሪተኞች ይንኮታኮታሉ። (ከነቢዩ ኢሳያስ የትንቢት ቃል ያዳቀልሁት ነው።)

የአንዳርግ "ሌጋሲ" - ኑዛዜና ቅርስ ነው። የትውልድ ቅርስ፣ የትግል ቅርስ ... የመስዋዕትነት ቅርስ!

በአንዳርጋቸው ላይ የሚፈጸመውን ኢሰብዓዊ ድርጊት ሁሉ ሳስበው ከጥንት ጀምረው ኢትዮጵያን ከሰለጠነው ዓለም ጋር ለማሰለፍ ብዙ መስዋዕትነትን የከፈሉ ሰዎች እነ ሎሬንዞ ታዕዛዝ፣ ተስፋዬ ተገኝ፣ ተክለ ሃዋርያት ዋየህ፣ ሐኪም ወርቅነህ እሸቴ ቢሞቱ፤ እነ ሐዲስ ዓለማየሁ፣ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረ ሕይወት፣ እነ አማኑኤል አብርሀም... በህይወት ቆይተው ኢትዮጵያ የገባችበትን የኋሊት ጉዞና ቅድመ መሳፍንት ዘመን አገዛዝ አይተውታል። የተጓዙበትን ርቀት ሜዳ ስለሚያስታውሱ (ለምሳሌ የባርያ አስተዳዳሪነትን ለማስቀረት የተደረገውን ያህል) በኢትዮጵያ አዲስ የባርያ ስርዓት የገባ ይመስላል። እንደቀድሞው በዓለም አቀፉ አካል ቁጥጥር ቢደረግ እኮ ከድርጅቱ ከሚባረሩ አገሮች ግንባር ቀደም የምትሆነው የእነ ኃይለማርያም ኢትዮጵያ በሆኑ ነበር። ኢትዮጵያ ዛሬ የእነ ኃይለማርያም ናት። ነገ ነው የደቂቀ አንዳርጋቸው የምትሆነው።

አንዳርጋቸው ጽጌ በወያኔ ዓለም አቀፍ ሴራ ከተያዘበት ዕለት ጀምሮ በተለይ በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ በነቂስ ወጥቶ የትግል ቃል ኪዳን ሲያደርግ ይታያል። ይኽ ደግሞ የሚቀጥል ነው። ሕዝብ በራሱ አነሳሽነት ተንቀሳቅሶ በራሱ መፈክር አቋሙን ሲገልጥ ለማየት የታደልንበት አንድ አጋጣሚ የአንዳርጋቸው ሌጋሲ ይመስለኛል። "እኔ አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ" የሚለውን ከኢትዮጵያ ጋር የተካሄደ መሐላ በግንቦት ሰባቶች በድርጅታዊ አሰራር የመጣ መስሎ ይታይ ይሆናል። አይደለም። ሕዝቡ ጀግንነቱ፣ ወኔው፣ ወንድነቱ፣ የተሟሟቀበትና የተነሳበት ነበር ለማለት ይቻላል። በእኔ በኩል ምርኮ ተብሎ የተጠራውን "ክተት" ለማለት እወዳለሁ።

የአገሬ ሕዝብ ጆሮ ይሰጠኝ ይሆን? ◆

# ቆይታ

# ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታናሽ እህት ከወ/ሮ እስከዳር ጽጌ ጋር

***አሻራ፡*** **እስኪ እንደመነሻ ስለራስሽ እናንሳ።የቤተሰብሽ ስንተኛ ልጅ እንደሆንሽ፣ ስለእድገትሽ ፣ ወደ ውጭ ሃገር መቼ እንደመጣሽና የመሳሰሉትን በመዳሰስ ብትጀምሪልን?**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** በቅድሚያ ስለተሰጠኝ እድል በጣም አመሰግናለሁ፡ እስከዳር ጽጌ እባላለሁ። በአሁኑ ሰአት የምኖረው በአሜሪካ አትላንታ ውስጥ ነው። ከሃገር የወጣሁት ገና የ 12 ዓመት ልጅ ሆኜ ነው። በአውሮፓውያን አቆጣጠር 1982 ዓ.ም. ። እንደሚታወሰው በግዜው በተለይ በወጣቶች ላይ ይደርስ በነበረው በደል ምክንያት ቤተሰብ ባገኘው አጋጣሚ ልጆቹን ወደ ውጭ አገር የሚያሸሽበት ግዜ ነበር። እኔም በተመሳሳይ ምክንያት ወደ ውጭ የመላክ አጋጣሚው ከነበራቸው አንዷ ሆኜ ወደ እንግሊዝ ሃገር ወጣሁ።የቤተሰቤም ስምንተኛና የመጨረሻ ልጅ ነኝ፡፡

***አሻራ፡*** **አቶ አንዳርጋቸውስ የቤተሰቡ ስንተኛ ልጅ ናቸው? እንደታናሽ እህትስ ከልጅነት ትዝታውችሽ መሀል ጥቂት ትውስቶች ልትጠቅሺልን ትችያለሽ?**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** አንዳርጋቸው የቤተሰቡ ሁለተኛ ልጅ ነው።እንዳልኩህ እኔ ስምንተኛና የመጨረሻ ልጅ ነኝ። ወንድምና እህቶቼ እኔን ጨምሮ ማለት ነው ስምንት ነን። አንደኛው ወንድማችን በ1969 ሜይ ላይ በደርግ ተገሏል።የቀረነው እንግዲህ አራት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ነን፡፡

ከአንዳርጋቸው ጋር ስለነበረሽ ቅርርብ ላልከው፡ እኔ በልጅነቴ ስለወጣሁ ወንድሞቼን ብዙም አላውቃቸውም ነበር።እንግሊዝ ሃገር እስክንገናኝ ማለት ነው።

በልጅነቴ ግን ጉልህ ትዝታ ባይሆንም አንዳንድ የማይረሱኝ ነገሮች አሉ።በተለይ ወንድማችን የተገደለበት ቀን ከማይረሱኝ፡ትዝታዎች አንዱ ነው። አንዴ ደግሞ እ.ኢ.አ. በ1969ዓ.ም. በግዜው ወጣቱን የሚያሳድዱት አብዮት ጠባቂዎች ሰፈራችን ውስጥ አንድ ልጅ ከገደሉ በኋላ እናም ቤት አንዳርጋቸውንና አለማየሁ የሚባለውን ወንድማችንን ለመያዝ በአጥር ዘለው ገብተው፤ እናታችን ላይ መሳሪያ ደግነው ቤቱን ሲበረብሩ ትዝ ይለኛል።ፈተሸው አጥተዋቸው ገና ከበሩ እንደወጡ አንዳርጋቸው በግቢው የኋላ በር በኩል ሲገባ እናታችን እንዴት እንደተጨነቀች መቼም አይረሳኝም። እሱ ግን ምንም ሳይመስለው እንደ ቀላል ነገር ነበር ያየው። ይሄ መቼም ከጭንቅላቴ ከማይጠፉት ትዝታዎች አንዱ ነው።

በልጅነቴ ስለ አንዳርጋቸው ትዝ የሚለኝ ከአባታችን ጋር በግዜው ስለነበረው ፖለቲካ፤ (ስለ ሶሻሊዝምና ኮምኒዝም ይመስለኛል) ይከራከሩ እንደነበር ነው። አባቴም ያነብ ነበርና አንዳንዴ እንዲያውም ክርክራቸው ጠንከር ይል እንደነበር ይታወሰኛል።

ሌላ የማስታውሰው እንደማንኛውም ቤተሰብ በታላቅና ታናሽ መካከል ያለው እሰጥ አገባ እኛም ቤት ነበርና እኔንና የኔን ታላቅ ከአንዳርጋቸው የሚያንሱት ወንድሞቻችን ይኮረኳኩሙንና ይጫኑን ነበር።አንዳርጋቸው ካለ ግን አትንኳቸው ስለሚል ነጻነት ይሰማን ነበር። በተለይ እናትና አባታችን ቤት በማይኖሩበት ሰአት የአንዳርጋቸው ቤት ውስጥ መኖር ያስደስተን ነበር።ከኩርኩም ማዳን ብቻም ሳይሆን በግዜው የዩንቨርሲቲ ተማሪ ስለነበር ከሚሰጠው የኪስ ገንዘብ 5ና 10 ሳንቲም ይሰጠን ነበርና አንዳርጋቸውን በጣም ነበር የምንወደው።

***አሻራ፡*** **እንደነገርሽን ሁለታችሁም በተለያየ ግዜ ቢሆንም ወደ እንግሊዝ ሄዳችሁ የተገናኛችሁት እዛው ነው። በእንግሊዝ አገር ቆይታችሁ የነበራችሁ ቅርርብስ ምን ይመስል ነበር?**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** ቀደም ሲል እንደገለጽኩልህ እኔ ወደ እንግሊዝ የሄድኩት በአውሮፓዊያኑ አቆጣጠር በ1982ዓ.ም. በኛ (1974-75) ይመስለኛል ። በዛን ግዜ እሱ እንግሊዝ ሃገር አንድ 2-3 አመት ቆይቶ ነበር። ሌሎችም ሶስት ወንድሞቼ እዛው ነበሩ።ትዝ የሚለኝ እናትና አባቴ እኔን እዛ አድርሰው ሲመለሱ እኔም ተመልሼ ካልሄድኩ ብዬ በጣም አስቸግሬ ነበር።

እሱ እንዲያውም በዚህ እድሜ ልጅ ውጭ ሃገር ያለወላጅ መኖሩ ጥሩ አይደለም! ይዛችኋት ተመለሱ ብሎ፤ ከእናትና አባቴ ጋር ተጨቃጭቆ ነበር። እነሱ ደግሞ ያሰቡበት ነገር ስለነበር ትተውኝ ሄዱ። በዛ ሰአት እንዳሁን ብዙም ስደተኛ ስላልነበረ ለልጅ አስተዳደግ ትንሽ አስቸጋሪ እንደነበር አስቦ ይመስለኛል አንዳርጋቸው።

እናትና አባቴ ከሄዱ በኋላም እንዳይከፋኝ ከፍተኛ እንክብካቤ ያደርግልኝ ነበር። በሀገሩ ህግ ልጅን ለብቻው ቤት ውስጥ ጥሎ መሄድ ስለማይቻል እሱ ከኛ ጋር ባይኖርም በሳምንት 2 ቀን እየመጣ እቤት ውስጥ ይጠብቀኝ እንደነበር ትዝ ይለኛል። መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ምግቤን አብስሎ ያበላኛል፤ ወደ ገበያ እየወሰደኝ የምፈልገውን ይገዛልኛል፤ እያጫወተኝ ስለ ብዙ ነገሮች ያስረዳኝ ነበር።አንዳርጋቸው በተፈጥሮው ረጋ ብሎ ማስረዳት የሚወድ ሰው ነው።ስለሚከትፋት ሽንኩርት እንኳ ለምን እንደሚከትፋት በጥሞና የሚያስረዳ ሰው ነው። ከማንም በላይ አቴንሽን ይሰጠኝ ነበር። ብቻ ምን አለፋህ በልጅነቴ እንዲደረግልኝ የምፈልገውን ሁሉ ሳልጠይቅ የሚያደርግልኝ እሱ ነበር። ነጻነት ይሰጥሃል፤ ሲያናግርህም በትህትና በእርግታ እንጂ እንደዚያ ዘመን ታላቅ ወንድም ቁጣና ኩርኩም አንዳርጋቸው ጋ የሉም።ለዚህም ይመስለኛል ከየትኛውም የቤተሰቡ አባል በበለጠ ከሱ ጋር ያለኝ ቅርርብ ጠንከር ያለ ነው። በዛ ሰዓት ከማንም በበለጠ ከሱ ጋር

የማሳልፋቸው ጊዚያት ደስታ ይሰጡኝ እንደነበር አስታውሳለሁ::

ነፍስ እያወኩ እድሜዬ አስራዎቹ አጋማሽ ሲገባም በሳምንት 50 ፓውንድ የኪስ ገንዘብ መድቦልኝ፤ መጽሃፍ እየገዛልኝ አነብ ስለነበር እንከብካቤውን አልቋረጠብኝም:: የሚገርምህ ለኔ ያደርግ እንደነበረው አሁን ደግሞ ለልጄ(የ13 ዓመት ልጅ አለችኝ፤ እሷም በጣም አንባቢ ነች።) መጽሃፍ ይገዛላታል። የምትፈልገውን እየጠየቀ ያሟላላታል። ያበረታታል።

***አሻራ፡*** **የአንድን ሰው ስብዕና መግለጫ በርካታ ቃሎች አሉ።ለምሳሌ፤ ታታሪ፤ አስተዋይ፤ትግስተኛ፤ ቁጡ፤ እውነተኛ፤ እልህኛ፡ ደፋር፤...ወዘተ የሚሉ። በርግጥ አንድ ሰው ከአንድ በላይ በሆኑ ስብእና ገላጭ ቃላት ሊገለጽ ይችላል።አንቺ አቶ አንዳርጋቸውን በሶስት ወይም በአራት ስብዕና ገላጭ ቃላት ግለጫቸው ብትባዪ የትኞቹን ቃሎች ትመርጫለሽ?**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** አንዳርጋቸውን በቃላት መግለጽ ይከብደኛል። ምን አይነት ሰው እንደሆነ ግን ልንገርህ፡- ያመነበትን ነገር ለማድረግ ወደ ኋላ የማይል። የጀመረውን ነገር ሳይቋጭ ወይም ዳር ሳያደርስ የማያቆም( ፎከሰድ) ።ለሰው በጣም የሚያዝን፤ ሰው ይዋሻል ብሎ የማይገምት ሰው ነው። አንዳንዴ በቀልድ መልክ እኮ ያልሆነ ነገር ፈጥረህ ታወራለህ፤ እቤት ውስጥ ከወንድሞቼ ጋር እንደዚያ አይነት ቀልድ ስናወራ አንዳርጋቸው እውነት አድርጎ ነበር የሚቀበላቸው። ቆይተን እረ ቀልድ ነው ስንለው፤ ለምን እንዲህ ተራ ነገር ታደርጋላችሁ? የሚል ሰው ነው።"ተራ ነገሮች" የሚላት የዘወትር አባባል አለቺው።ቤተሰባችን ውስጥ ሁሉም ተከባብሮና ተፋቅሮ ነው የሚኖረው። በተለይ እሱ ደግሞ እንኳን ከቤተሰብ ከውጭም ሰው ጋር ተጋጭቶ ያየሁበት ወይም የሰማሁበት ግዜ የለም።ብቻ ምን አለፋህ ከአንዳርጋቸው ገር መጣላት ይከብዳል። በፍጹም ለጸብ የማይነሳሳ፤ ምንም ነገር ብትናገረው የማይናደድና ስሜታዊ የማይሆን ውስጡ ነገርና ቂም የማያውቅ ንጹህ ሰው ነው::

***አሻራ፡*** **አቶ አንዳርጋቸው ከወጣትነት ዕድሜ ጀምሮ በትግል ወይም ለህዝብ መብትና ለሃገር ህልውና የሚበጅ ሥራ ለመስራት ሲባዝኑ መቆየታቸው ይታወቃል።በዚህም እንቅስቃሴያቸው በርካታ ፈተናዎች ገጥመዋቸዋል። አሁንም ፈተና ውስጥ ይገኛሉ። ለመሆኑ ይህ ለረዥም አመታት ለሕዝብና ለሃገር ጥቅም የመታገሉ ጽናትና እምነት መሰረቱ ምንድነው ትያለሽ? የቤተሰብ ወይስ ሌላ መገለጫ አለው...**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** እንደሚታወቀው ተፈጥሮ ከሚሰጠው ውጭ ያለውን የአንድን ሰው ማንነት በመቅረጽ ረገድ የቤተሰብ ድርሻ ከፍ ያለ ነው። አንዳርጋቸውም በተፈጥሮ ያገኛቸው የራሱ የሆኑ ኳሊቲዎች እንዳሉት ሁሉ ከወላጆቻችን የወሰዳቸውና ለዛሬ ማንነቱ ግብአት የሆኑ ስብዕናዎች አሉት። ለምሳሌ ለሰው የማዘንና ሩህ ሩህነቱን ከናታችን ያገኘው ይመስለኛል::

እናታችን በጣም ሩህሩህና ለሰው አዛኝ ነበሮች። ቤታችን ውስጥ ከስምንታችን ሌላ በርካታ የዘመድና አሳዳጊ የሌላቸው ወይም የችግረኛ ቤተሰብ ልጆች ይኖሩ ነበር።እኔ የመጨረሻ ልጅ ነኝ ብዬሃለሁ። እኔ ወደ እንግሊዝ በምወጣበት ወቅት ከኔ በታች እንኳ እቤት ውስጥ የሚያድጉ አራት ልጆች ነበሩ።

ሁሉም ልጆች ታዲያ ከኛው እኩል መብት ነበራቸው::ሌላው ቀርቶ በሰራተኝነት የሚቀጠሩትን እንኳ እኛ ቤት ሰራተኛ ሆነው እንዳይቀሩ ስትል ትምህርት እንዲማሩና እራሳቸውን እንዲችሉ ትመክር ነበር። መምህርት ስለነበረች ቡተሊይ እንዲማሩ በጣም ታበረታታ ነበር። በአንዳርጋቸው ለሰው የማዘንና ሰውን የመርዳት ፍላጎት ላይም ታዲያ ይህ የእናታችን አሻራ ያለ ይመስለኛል።

> ..... አሁን አንዳንድ ይሰራቸው የነበሩ ነገሮችን ስሰማ ግን ስለ አንዳርጋቸው ብዙ የማላውቀው ነገር እንዳለ እየተሰማኝ ነው። የበለጠ ባወቅኩት ቁጥር ከዚህ ሰው ጋር ህይወቴ መገናኘቱ አኩርቶኛል። ባጠቃላይ ስለአንዳርጋቸው ሳስብ ፤ ማሰብ የምፈልገው ስቃይ ውስጥ መሆኑን ሳይሆን የሰራውን አኩሪ ስራና ስቃዩም ለነገ ብሩህነት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ ነው:: እህትነቴ ሊፈጥርብኝ የሚፈልገውን የሃዘን ድባብ የማስወግደውም ስለ ስራው እንጅ ስለ ስቃዩ ባለማሰብ ነው።በደረሰበት ነገር ከማዘን ይልቅ በስራው መኩራትን ነው የምመርጠው። .....

በሌላ በኩል ደግሞ አባታችን በጣም ዲሲፒሊንድ የሆነ ሰው ነው:: ሲወራ እንደሰማሁት ለመሾምና ለመሸለም እጅ መንሳትና መኳንኑን መለማመጥ ያስፈልግ በነበረበት በንጉሱ ግዜ እሱ እንዲህ አይነት ነገር ስለማይዋጥለት፤ ጓደኞቹ የደረሱበት ሳይደርስ ቀርቷል።በችሎታዬ እንጂ በእጅ መንሻ የሚገኝ ሹመት ይቅርብኝ ብሎ አብረውት የተማሩት ጓደኞቹ ሲሾሙ እሱ አይሾምም ነበር። ባለመሾሙ ግን አይናደድም።ባለው ነገር በጣም ደስተኛ ነበር ።

አባታችን ለሃገሩ በጣም ፍቅር ያለው፤ ባባቶቹና አያቶቹ ታሪክ የሚኮራ፤ ልጆቹም እንዲሁ ስለሃገራችን እንድናውቅ የሚጥር የኢትዮጵያን ታሪክና የኢትዮጵያዊነትን ትርጉም አውቀን እንድናድግ የተጋ አባት ነው። መጽሃፍ እንድናነብ በጣም ስለሚገፋፋን ቤተሰባችን ውስጥ ሁሉም የንባብ ልምድ ያለው ነው።

አባታችን ስለ ሃገር ያለውን አመለካከት በጥቂቱ የሚያሳይ ነገር ልንገርህ፡- ደርግ አንድ ልጁን ገድሎበታል፤ የኔን ታላቅ የ 14 ዓመት ልጁን ገርፎበታል። የመጨረሻዋ እኔም ሳልቀር አብዛኞቹ ልጆቹ ለስደት ተዳርገዋል፤ ይህ ሁሉ በደል አልበቃ ብሎ የ 14 ዓመት ልጅ ሆኖ የተገረፈው የኔ ታላቅ ወንድም ለመጀመሪያው ዙር ብሄራዊ ውትድርና ተጠራ። በዚህ ግዜ ቤተሰቡ ሁሉ ሲናደድ፤ አባታችን ግን ብሄራዊ ውትድርና የሃገር ጉዳይ በመሆኑ መቅረት የለበትም ነበር ያለው። ለሱ ከልጅም ከቤተሰብም የሚቀድመው ሃገር ነው።

ከዚህ ውጭ አንዳርጋቸው በጣም አንባቢ በመሆኑ ከመጽሃፍትና ከትምህርት የቀሰመው ዕውቀትም ለዛሬው ማንነቱና ለዘመናት ለዘለቀው "ለህዝብ መብትና ለሃገር ህልውና" የመቆም ጽናቱ የበኩሉን አስተዋጾ ያደረገ ይመስለኛል። በአጠቃላይ የአንዳርጋቸው የዛሬ ማንነት ተፈጥሮ የለገሰው፤ ከቤተሰብ የወሰደው፤ ከአካባቢው የተማረውና ከትምህርትና ከመጽሃፍ የቀሰመው..ድምር ውጤት ነው ብዬ አስባለሁ።

***አሻራ፡*** **አሁን ደግሞ ወደ ቅርቡ ዕውነታ ላምጣሽ! ለመሆኑ የመን ላይ ተከታይ አውሮፕላን እየጠበቁ ሳሉ ታገቱ! የሚለውን አስደንጋጭ ዜና ስትሰሚ ምን ስሜት ፈጠረብሽ?እንዴትስ ተቀበልሺው!**

***ወ/ሮ እሰከዳር፡-*** አ!!!!....(ፋታ....ዝምታ) እንደነገርኩህ ካሉኝ ወንድሞች ሁሉ ከአንዳርጋቸው ጋር የተለየ ቀርቤታና ፍቅር ነው ያለን። ያን ደግሞ እኔ ስለፈለኩት የሆነ ሳይሆን እሱ ስለፈጠረው የሆነ ነው። እናም የመን ላይ የደረሰበት እንደጠፋ ስሰማ : በመጀመሪያ ግራ ነው የገባኝ፤ መጥፋት ማለት ምን ማለት እንደሆነም ግልጽ አልሆነልኝም።ጥቂት ቆይቶ "ታፈኖ ተወሰደ!" ሲባል ደግሞ እንደወሰዱት ወዲያው የሚገሉት ነበር የመሰለኝ።አፍነው መውሰዳቸውን እስኪያምኑና በህይወት መኖሩን እስካውቅ ድረስ ዝብርቅርቅ ያለ ስሜት ውስጥ ነበርኩ።

***አሻራ፡*** **አቶ አንዳርጋቸው በቅንጅት ግዜ ታስረው ተደብድበዋል። ግንቦት ሰባትን ከመሰረቱ በኋላ ከሳቸው እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ አባታችሁ ከአመት በላይ ታስረዋል። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ አቶ አንዳርጋቸው ላለፉት 5 አመታት ትጥቅ ትግል እያደራጁ ነበር። ይህ ሁሉ ተደጋጋሚ በደልና ፈተና እየገጠማቸው ዳግም ለትጥቅ ትግል መውጣታቸው ቤተሰቡም ላይ ሆነ በተለይ አንቺ ላይ እንደቅርበታችሁ ስጋት አልፈጠረም?**

*ወደ ገጽ 32 ዞሯል*

**<u>አሻራ፦</u> እንደመነሻ ፦ የኢህአዴግ መንግስት የግንቦት ሰባት ዋና ጸሃፊ የሆኑትን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በየመን ተባባሪነት አሳፍኖ መውሰዱን እንዴት ያዩታል?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***በመርህ ደረጃ ካየነው በኢትዮጵያ ያለው አስተዳደር አቶ አንዳርጋቸውን አፍኖ የወሰደበት ሁኔታ ቦኮ ሀራም ከአራት ወራት በፊት 300 የናይጄሪያ ልጃገረዶችን ካገተበት ሁኔታ እምብዛም የተለየ አይደለም። የተፈጸመው በመንግስት ደረጃ የተቀናበረ እገታ ነው። የየመን መንግስት ወንጀል መፈጸሙ እርግጥ ነው። ከመርህ አንጻር ቦኮ ሀራምና አልቃይዳ በየዕለቱ የሚፈጽሙትን ነው የየመን መንግስት አቶ አንዳርጋቸውን በማገት የፈጸመው።

መንግስታት ማንንም ሰው ሊገደል፣ ቶርችና መሰል ማሰቃያዎች ሊፈጸምበት ይችላል ወደሚያስብል አገር መመለስ እንዳይችሉ የሚያግድ ፍጹማዊ ግዴታ አለባቸው። ይህ ደግሞ ግለሰቡ ማናቸውንም ዓይነት ወንጀል ፈጽሟል ቢባል እንኳን መከበር ያለበት ግዴታ ነው። ቶርቸርን በመቃወም የተደረገው የዓለም አቀፍ ስምምነትም መንግስታት ቶርቸር ሊፈጸምበት ይችላል የሚያስብል መሰረት ወዳለበት አገር ማንንም ሰው አሳልፈው እንዳይሰጡ ይከለክላል። የየመን መንግስትም አቶ አንዳርጋቸውን በኢትዮጵያ ላለው አገዛዝ አሳልፎ ከመስጠቱ በፊት ቶርቸር ሊደርስባቸው እንደሚችል አሳምሮ ያውቅ ነበር: ወይም እንዲያምን የሚያደርጉት በቂ መሰረቶችና በገሀድ የታወቁ መረጃዎች ነበሩት።

**<u>አሻራ፦</u>አቶ አንዳርጋቸው መታገታቸው ከታወቀ በኋላ በገዢው መንግስት የተለቀቁት የተቆራረጡ የቪዲዮ ቅንብሮች ምን ፋይዳ እንዲሰጡ ወይም እንዲያስገኙ ታስቦ የተለቀቁ ናቸው ይላሉ?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***በርግጠኝነት መናገር ባልችልም። ገዢው መንግስት ሁለቱን ተከታታይ የቪዲዮ ክሊፖች የለቀቀው የተለያዩ ፖለቲካዊ ፋይዳዎችን አገኝባቸዋለሁ በሚል እስቤ እንደሆነ እገምታለሁ።

በኔ እምነት ምናልባትም የደህንነት መስሪያ ቤቱ ብቃት ያለው መስሎ እንዲታይለትና የትኞቹንም የአለም አቀፍ ህግጋት ለመጣስ የማይፈራ መሆኑን ለማሳየት የፈለገ ይመስላል።በሌላ በኩል ደግሞ እስረኛውን በሙሉ ጤንነት ላይ እንደሚገኝ በማሳየት ቶርቸር እየተደረጉ ሊሆን ይችላል በሚል ከተለያዩ ወገኖች ሲቀርቡ የነበሩትን ስጋቶች ለማምከን የፈለጉ ይመስላል።በተጨማሪም ድርጅታቸው ግንቦት 7ን የማሳፈር፤ በሁሉም የአገዛዙ ተቃዋሚዎች ላይ ፍርሃት ለማስረጽና ተስፋ ለማስቆረጥ አስበው ነው ብዬ አምናለሁ ።

**<u>አሻራ፦</u> ገዥው አካል አቶ አንዳርጋቸውን በቴሌቪዥን በማሳየት ሊያሳካ ያሰባቸውን ከላይ የጠቃቀሷቸውን ፖለቲካዊ ፋይዳዎች አሳክቷል ማለት ይቻላል?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***ያሳካ አይመስለኝም። በርግጥ የአቶ አንዳርጋቸው መያዝ በድርጅታቸው እንቅስቃሴ ላይ መጠነኛ ጉዳት አድርሶ ይሆናል። አፋኞቹም ለግዜው "በተሳካልን" ስሜት ጮቤ ሊረግጡ ና በደስታ ሊፍነከነኩ ይችላሉ። ነገር ግን ገዥው አካል በአሁኑ ጊዜ በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የፈጸመው አፈና የድርጅታቸውን የግንቦት ሰባትን እንቅስቃሴ ያከሰመዋል ማለት ምክንያታዊ ያልሆነ ድምዳሜ ነው። በበኩሌ ማንም ሰው ቢሆን የአንድ ድርጅታዊ ተቋም ነብስ፣ አካል እና አእምሮ ሊሆን ይችላል ብዬ መቀበል ይከብደኛል (ከመለስ ዜናዊ በስተቀር)። ከዚህ በመነሳት ገዢው ፓርቲ አቶ አንዳርጋቸውን ማፈኑ በድርጅታቸው በግንቦት 7 ላይ የተቀዳጀው ድል ነው ብዬ አልወስድም። የድርጅታቸውንም እንቅስቃሴ ያከሰማል ወይም ይገታል ብዬም አላምንም።

**<u>አሻራ፦</u> የወያኔ መንግስት አቶ አንዳርጋቸውን ማፈኑ ምንም የፖለቲካ ጥቅም አላስገኘለትም፤ ጭራሹኑ ተቃዋሚው ህብረት ፈጥሮ ተቃውሞውን እንዲያጠናክር ሉድርጎታል የሚሉ ወገኖች አሉ። ለዚህ አባባላቸውም በቅርቡ በፕሬዘዳንት አባማ ጋባዥነት ወደ አሜሪካ በመጡት የገዢው መንግስት ባለስልጣናት ላይ የተነሳውን ጠንካራ ተቃውሞ በዋቢነት ይጠቅሳሉ። የእርሶስ አስተያየት ምንድን ነው?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***በእኔ አስተያየት አገዛዙ አፈናውን በማካሄዱ ከጠበቀው የተቃረነ ውጤት ነው ያተረፈው። የወረወረው ድንጋይ ዞሮ እራሱኑ ነው የመታው። የአገዛዙ ዓላማ እርምጃውን በመውሰድ ግንቦት ሰባትን መጥፎ ወይም ደካማ አስመስሎ የማሳየትና ደጋፊ የማሳጣት ጥረት ቢሆንም ውጤቱ ግን ጭራሽ የተገላቢጦሹ ነው የሆነው። ሌላው ቀርቶ በተለያዩ ምክንያቶች ግንቦት ሰባትን የሚሞግት አመለካከት የነበራቸው በርካታ ሰዎች ሳይቀሩ አሁን ድርጅቱን በተለየ ዓይን ማየት መጀመራቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች ነው ያገኘሁት። ለብዙዎች ዲያስፖራ ኢትዮጵያዊያን የተወሰደው እርምጃ አገዛዙ ምን ያህል ግንቦት ሰባትን እንደሚፈራና ስጋት ውስጥ እንደወደቀ ነው ያረጋገጠላቸው።

**<u>አሻራ፦</u> የመን የእንግሊዝ ዜጋ የሆነን ሰው ዜግነት ወደሰጠው አገር ሳይሆን ወደ ሌላ 3ኛ አገር ነው ያስተላለፈችው። ይህን መሰሉ እርምጃ ከዓለም አቀፍ ህግ አንጻር እንዴት ይታያል?**

***ፕ/ር አለማየሁ፦*** ከዓለም አቀፍ ህግ አንጻር የመን የወሰደችው እርምጃ የተለያዩ የህግ ጥሰቶች የታዩበት ነው። ድርጊቱ ህገወጥ መንግስታዊ ጠለፋ (Extraordinary Rendition ) ይባላል። አንድን ሰው አስሮ በህገ ወጥ መንገድ ወደ ሌላ አገር ማስተላለፍ እንደማለት ነው። ሲ አይ ኤ በተለያዩ ጊዚያት በሌላ አገር የተያዙ የሽብር ተጠርጣሪዎችን ቶርች ወደሚፈጸምበት 3ኛ አገር በማስተላለፍ ህገ ወጥ ምርመራዎች እንዲደረግባቸው ያደርግ እንደነበር ይታወቃል።

ኢትዮጵያም በዓለም አቀፍ ደረጃ የተወገዘውን ቶርቸርና መሰል የማሰቃያ መንገዶችን ከሚጠቀሙ አገራት አንዷ ነች። በዚህ ድንበር አቋራጭ የወንጀል ተግባርም በግንባር ቀደምትነት ተሳትፋለች። ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ከሱማሊያና ከኬንያ የተያዙ ከመቶ በላይ ተጠርጣሪዎች ለምርመራ ወደ ኢትዮጵያ ተወስደው እንደነበር ተረጋግጧል። እስረኞቹ በምርመራው ወቅት የህግ አማካሪ የማግኘት መብታቸውን የተከለከሉ ሲሆን አብዛኞቹም በኤሌትሪክ ንዝረት መሰቃየትን ጨምሮ የተለያዩ አካላዊና ስነልቦናዊ ቶርቸሮች ተፈጽመውባቸዋል።

ወደ ዋናው ነጥብ ልመለስና፦ አንድን ሰው ስቃይና ሰቆቃ ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ወደሚታመንበት አገር እንዳይመልሱ ሁሉም አገራት ግዴታ አለባቸው። የህጉ መሰረት ማንም ሰው በመንግስት ከሚታገዝ ቶርቸር ነጻ የመሆን መብት አለው ከሚል የሚነሳ ነው። ይህም በከፍተኛ መርህና ዓለም አቀፍ የህግ ስምምነቶች ስር ዕውቅና ያገኘ መሰረታዊና ዓለም አቀፋዊ መብት ነው። ግለሰቡ(ቧ) ፈጽመውታል የተባለው ወንጀል ምንም ያህል የከፋ ቢሆን ወይም አሁንም አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ናቸው ተብሎ ቢታሰብም እንኳ ተፈጻሚ የሚሆን የመብት ጥበቃ ነው። አገራቱ በዚህ መሰረታዊ መርህ ዙርያ የፈረሟቸው ስምምነቶች ኖሩም አልኖሩ ግዴታው ግን ይመለከታቸዋል።

> ...ዛሬም የጡረታ ጊዜዬን በአሜሪካ አሳልፋለሁ የሚል ሀሳብ ያላቸው የኢትዮጵያው አገዛዝ ባለስልጣናት ካሉ በአሜሪካ ፌደራል እስር ቤት ውስጥ ስለሚጠብቃቸው ረጅም የጡረታ ጊዜ ሊዘጋጁበት ይገባል። የዘረፉትን ሚሊዮኖችም ዩ ኤስ ኤ ውስጥ የማጣጣም ዕድላቸው የመነመነ ነው!።.....

***<u>አሻራ፦</u>ብአለም አቀፍ ደረጃ በሁሉም አገራት መከበር ያለበት መርህ ከመጣሱ ባሻገርስ የመን በዚህ እርምጃዋ ልታከብራቸው ሲገባት ያላከበረቻቸው ውሎች አሉን? ተጠያቂነቷስ እንዴት ነው?***

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***አዎ! ከአቶ አንዳርጋቸው አፈና ጋር በተገናኘ ሌሎችም በፊርማ ሳይቀር የተደገፉ ስምምነቶ ተጥሰዋል።ከተጣሱ በፊርማ የጸደቁ ስምምነቶች መሀል ኢትዮጵያና የመን ሁለቱም ፈራሚ የሆኑበት በምህጽረ ቃል CAT (Convention Against Torture and Other Cruel, Inhumane or Degrading Treatment or Punishment ) ተብሎ የሚታወቀው ሰቆቃ/ ቶርቸርን እና ሌሎች በጭካኔ የተሞሉ አያያዞችን ወይም ቅጣቶችን የሚከለክለው ስምምነት አንዱ ነው። ይህን ስምምነት ኢትዮጵያ በማርች 1994 ፣ የመን ደግሞ በኖቬምበር 1991 ዓ.ም ፈርመውታል። በስምምነቱ አንቀፅ 3 ላይ "ማናቸውም አገር አንድን ሰው ለቶርቸር ሊጋለጥ ይችላል ብሎ ለማመን የሚያበቁ መሰረቶች ወዳሉበት አገር ማባረር፣ አሳልፎ መስጠትም ሆነ አስገድዶ መመለስ የለበትም" በሚል በግልጽ የተቀመጠ አንቀጽ አለ።

ኢትዮጵያ ሰቆቃ/ ቶርቸር የሚፈጸምባት፣ ሚስጥራዊ እስር ቤቶችና የደረሱበት ሳይታወቅ የሚቀሩ ሰዎች ያሉባት አገር መሆኗ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ሳይቀር የተረጋገጠባት አገር እንደመሆኗ በአቶ አንዳርጋቸው አፈና ላይ የመን ሆን ብላ በመተባበሯ የገባችውን ስምምነት በግልጽ ጥሳለች። ከዚህ አንጻር አንድ አገር እያወቀች የዓለም አቀፍ ህግን በሚጥስ ተግባር ሌላ አገርን ከረዳች በግብረአበርነት ተጠያቂ ነች። በተመሳሳይ ሁኔታ የስምምነቱ አንቀፅ 3 ላይ የተያዘው ግለሰብ በሚወሰድበት አገር ሰቆቃ ሊደርስበት እንደሚችልና እንደማይችል ለመገምገም በማናቸውም አግባብ ባላቸው አመላካች መስፈርቶች ዙርያ በጥሞና መመዘን እንደሚገባ ያስገነዝባል። የመን ግን ይህን መሰረታዊ የጥንቃቄ መስፈርት ሳትገመግም እርምጃ ከመውሰዷም በላይ አቶ አንዳርጋቸው ቶርቸር እንደማይደረጉ ለማረጋገጥ የዲፕሎማቲክ ማረጋገጫ እንኳን እንዲሰጣት አልጠየቀችም።

***<u>አሻራ፦</u>ብወቅቱ የእንግሊዝ መንግስት የአቶ አንዳርጋቸውን መታገት እንደማያውቅ መግለጹ ይታወሳል። ከአለም አቀፍ ህጉ አኳያ የመን ለእንግሊዝ ኤምባሲ የአቶ አንዳርጋቸውን መታገት ማሳወቅ አልነበረባትምን?***

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>***በስምምነቱ አንቀፅ 36 ላይ የሌላ አገር ዜጋ የሆነ ሰው በወንጀልም ሆነ በኢሚግሬሽን ጉዳዮች ከተያዘ መከበር ወይም መጠበቅ ያለባቸው መብቶቹ ተዘርዝረዋል። ከነዚህም መሀል አሳሪዋ አገር በአቅራቢያው ላለው የታሳሪው ዜግነት ሰጪ አገር ኮንሱላር ጽ/ቤት ሳይዘገዩ ማሳወቅ፣ ለታሳሪው ኮንሱላሩን የማግኘት መብት አንዳለው ማሳወቅና ታሳሪው በአገሩ ኮንሱላር ኃላፊዎች እንዲጎበኝ ማመቻቸት የሚሉት ይገኙባቸዋል።

ይህ ማለት አቶ አንዳርጋቸው የእንግሊዝ ዜግነት ያለው ከመሆኑ ጋር በተገናኘም እንዲሁ የመን የጣሰችው ስምምነት አለ ማለት ነው። በኮንሱላር ግንኙነቶች ላይ የተፈረመውና በምጽሀረ ቃል VCCR (Vienna Convention on Consular Relations) በሚል የሚታወቀው "የቪየና ስምምነት" ያለጥርጥር ተጥሷል። ይህን ስምምነት የመን በ ኤፕሪል 1986 ዓ.ም. ነበር የፈረመችው።የመን እነዚህን መሰረታዊ ስምምነቶች ባለማክበር ለብሪቲሽ ኤምባሲም ሆነ ሰንዓ ላለው የብሪቲሽ ኮንሱላር ቢሮ ሳታሳውቅ አቶ አንዳርጋቸውን ለኢትዮጵያ አገዛዝ አሳልፋ በመስጠቷ በቪየናው ስምምነት የገባቸውን የኮንሱላር ግንኙነቶች ስምምነት እያወቀችና ሆን ብላ ጥሳቸዋለች። የብሪቲሽ የውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት የመን የአቶ አንዳርጋቸውን መታሰር በወቅቱ እንዳልገለጸችላቸው ከማሳወቁም በላይ በተከተሉት ቀናትም በተደጋጋሚ መወትወቱንና በኢትዮጵያ የሞት ፍርድ ሊፈጸምበት ይችላል የሚል ስጋቱን መግለጹን አሳውቋል። ባጭሩ የመን የተለያዩ ስምምነቶቿን መጣሷ በማያወላዳ ሁኔታ ታይቷል።

***<u>አሻራ፦</u>የገዢው መንግስት ባለስልጣናት አቶ አንዳርጋቸው ከየመን ተይዘው የመወሰዳቸውን ተገቢነት የሚሞግቱት በሌሉበት ተከሰው የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሽብርተኛ ናቸው በማለት ነው፤ እርስዎ ይህን እንዴት ያዩታል?***

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፦</u>*** በተለያዩ ጊዚያት እንደገለጽኩት ሁሉ በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ የጸረ ሽብር ህጉን (ቁ.652/2009) እየተጠቀመበት ያለው ተቀናቃኞቹን በህግ ስም ለማጥፋት ሲል ብቻ ነው። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ 'የአገር ክህደት' እና 'የሽብርተኝነት' ክሶች መንግስት ለስልጣኔ ስጋት ናቸው የሚላቸውን ተቃዋሚዎቹን ለማጥፍያነት የሚገለገልባቸው መሳሪያዎች ናቸው። በካንጋሮ (የዝንጀሮ) ችሎቱ የሚሰጡት የፍርድ ውሳኔዎችም ቢሆኑ ገና ከጅምሩ የታወቁና የተወሰኑ ናቸው።

ይህ ህግ በተለያዩ መንግስታትና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች ሲብጠለጠል የቆየ ነው። የዩናይትድ ስቴትስ የውጪ ጉዳይ መስሪያቤት በተለያዩ ዓመታት ባወጣቸው የሰብዓዊ መብቶች ሪፖርቶቹ ላይ በኢትዮጵያ ያለው የጸረ ሽብር ህግ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን፣ ንቁ አራማጆችን፣ ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን [ወደ ገጽ 30 ዞሯል]

# አርቲስትና አክቲቪስት ታማኝ በየነ

## ስለ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ምን ይላል?

***አሻራ፦*** **ጤና ይስጥልኝ አርቲስና አክቲቪስት ታማኝ በየነ፤ በቅድሚያ ስለ ጊዜህ በአንባቢያን ስም ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ። አቶ አንዳርጋቸውን ለምን ያህል ጊዜ ታውቃቸዋለህ ? እንዴትስ ትገልጻቸዋለህ?**

***ታማኝ፦*** አንዳርጋቸውን የማውቀው ከምርጫ 97 ጀምሮ ነው።በምርጫ 97 ቅንጅትን ተቀላቅሎ በሚንቀሳቀስበት ወቅት ማለት ነው። ያኔ መቼም ሁላችንም ልባችን የምርጫው እንቅስቃሴ ላይ ስለ ነበር በየእለቱ እየደወልን ሁኔታውን እንከታተል ነበር። እኔም ራሴ ሃገሬ ገብቼ እንደልቤ በነጻነት ለመኖር የምችልበት ጊዜ አሁን ነው ከሚል እምነት የመግባት እቅድ ነበረኝ። አንዳርጋቸውን የማውቀው እንግዲህ በዛ ግዜ በነበረን የስልክ ግንኙነት ነው። እስኪታሰር ድረስ ማለት ነው። በነገራችን ላይ ከመታሰሩ በፊት ለመጨረሻ ጊዜ ያናገረኝ እኔን ነበር። ከኔ ጋር አውርተን ስልክ እንደዘጋ ነው የታሰረው።

ከንግግራችን የማስታውሰው እኔ እዚህ ሆኜ በስልክ ብቻ ከምከታተል ልምጣ እያልኩት ነበር። እሱ ደግሞ በዚህ ደረጃ መምጣት የለብህም እዛው ብትሆን ነው የምትጠቅመን እያለኝ ተነጋግረን እንደጨረስን ታሰረ። ከዚያም ተፈቶ ወደ እንግሊዝ አገር ተመለሰ። በኋላም በቅንጅት ኢንተርናሽናል ተመርጦ ሲሰራ በስልክም በአካልም እንገናኝ ነበር። ከአንዳርጋቸው ጋር የነበረን ትውውቅ ይህን ይመስል ነበር፡፡

እንዴት ትገልጸዋለህ? ላልከኝ፡-በጣም አስቸጋሪ በሆነበት ጊዜና መንገድ ህልሙን ሊያሳካ የደከመ ሰው ነው!። በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት የውጭውን ዓለም ዘመናዊ ህይወት የለመዱ ከአውሮፓና ከአሜሪካ እየሄዱ የኢህአፓን ትግል ተቀላቅለው በርሃ የቀሩ ወጣቶች እንደነበሩ አንብቢያለሁ። በንባብ የምታውቀውን ታሪክ በአካል የምታውቀው ሰው ሲያደርግ ስታይ ደግሞ በጣም ከባድ ነው። በአውሮፓና አሜሪካ ህይወት ፤ ምግብ፤ አልባሳት፤መኝታ፤ መዝናኛ፤ ብቻ እያንዳንዱን ነገር በምርጫና በፍላጎት የምታደርግበትን ህይወት ለምደህ በርሃ ገብተህ፤ ድንጋይ ለመንተራስ፤ አሸዋ ለመልበስ፤ ላለመታጠብና ያልታጠበ ለመልበስ መወሰን እጅግ በጣም ከባድ ነው። አስበው ከእንግሊዝ አገር ከንግስቲቷ ከተማ ሄዶ አሸዋ ላይ መተኛት ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ!።

ባጠቃላይ አንዳርጋቸው ከልጅነቱ ጀምሮ ከራሱ ህይወት አልፎ ቤተሰቡ የከፈለውን መስዋዕትነት ሳይ የሚሰማኝ ስሜት ሃዘን ሳይሆን ይህን ሥርዓት በተለያየ መልኩ እንታገላለን ለምንል ወገኖች ትልቅ ምሳሌና አርአያ የሆነ ሰው መሆኑን ነው።

***አሻራ፦*** **የወያኔ መንግስት አንድን ግለሰብ ለመያዝ ይህን ያህል ተጨንቆና ተጠቦ፤ ቀደም ሲል የግድያ ሙከራ ማድረጉ አሁን ደግሞ ከፍተኛ ወጪ አፍስሶ፤ ሁለተኛ አገር(የመን) የተሳተፈችበት ድንበር ዘለል አፈና መፈጸሙ ምን የፖለቲካ ፋይዳ አገኝበታለሁ ብሎ ይመስልሃል?**

***ታማኝ፦*** በመጀመሪያ የአንዳርጋቸውን የዓላማ ጽናት (ኮሚትመንት) አብሯቸው በሰራ ጊዜ አይተውታል። ያውቁታል። ከወጣትነት ዕድሜው ጀምሮ በኢ.ህ.አ.ፓ በኋላም ከነሱ ጋር ሲሰራ ለራሴ የሚል ሰው እንዳልሆነ፤ ስልጣን ይዞ ለመንደላቀቅ፤ ቤት ለመስራት፤ መኪና ... የመሳሰሉት ቁሳዊ ፍላጎት የሌለው ሰው እንደሆነ ጠንቅቀው ያውቁታል። የአንዳርጋቸው የዘወትር ቁጭት ኢትዮጵያ እንደ ሃገር ብዙ ያልተሟሉ ጉዳዮች ስላሏት እነሱን ለማሟላት መሆኑንም ያውቃሉ። ከቅርብ ጊዜው ብናይ እንኳ በምርጫ 97 ቅንጅትን ተቀላቅሎ በአጭር ግዜ ውስጥ ምን ያህል ህዝብን የማሰባሰብና የማደራጀት ስራ እንደሰራ እናስታውሳለን።

ባለፈው አስመራ ድረስ ቅጥር ነፈሰ ገዳይ ልከው ሊያስገድሉት መሞከራቸውን ኢሳት በዘገበበት ጊዜ እንዴት ሊሆን ይችላል?ይሄ የኢሳት ወሬ ነው ያሉኝ ሰዎች ነበሩ። እነሱ(ወያኔዎች) ግን በየት በኩል ጉዳት ሊመጣ እንደሚችል በደንብ ገብቷቸዋል።በኔ ግንዛቤ

አንዳርጋቸው የማስተባበሩን ስራ ጥሩ አድርጎ እንደሚሰራ ስላወቁ ይመስለኛል ይህን ያህል ክትትል አድርገው ሊይዙት የቻሉት።

**<u>አሻራ፦</u> እንዳልከው አቶ አንዳርጋቸውን መያዝ ማለት የተቃዋሚውን አከርካሪ እንደመስበር ሳይቆጥሩት የቀሩ አይመስልም።ይሁንና አቶ አንዳርጋቸውን የመን ላይ ይዘው መውሰዳቸው ለግዜው ጮቤ ቢያስረግጣቸውም፤ ውጤቱ ግን " አሳ ጎርጓሪ...." ሆኖባቸዋል የሚሉ ብዙ ናቸው፡፡ አንተስ በዚህ ሃሳብ ትስማማለህ?**

***<u>ታማኝ፦</u>*** በጣም እንጂ የምስማማው።እኔ እንግዲህ ህወሃት አገሪቷን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ በተቃዋሚነት አብሬ ኖርያለሁ። በውጭው ዓለምም አውሮፓ ፤ አውስትራሊያ ፤ አሜሪካ ...ያለውን የተቃዋሚውን ወገን እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አውቃለሁ እላለሁ። እናም ከቅንጅት በኋላ "የምን ፖለቲካ?...ፖለቲካ በቃኝ!" እያለ የሸሸው ሰው ሁሉ በፈቃደኝነት "ምን እናድርግ?" ብሎ የመጣበት ወቅት ነው አሁን።

የአንዳርጋቸውን ነገር የተለየ የሚያደርገው ደግሞ፦ አንዳርጋቸው በየመድረኩ የሚታይ ሰው አይደለም። ከሱ በበለጠ እኔ በብዙ መድረክ እታያለሁ። እሱ ግን የሚሰራ እንጂ የሚታይ ሰው አልነበረም፡፡ ይሁንና ህወሃት ይህን ያህል ሊያጠፋው የፈለገው አንዳርጋቸው ምን አይነት ሰው ቢሆን ነው? የሚለውን ነገር እንድት ጠይቅና እንድታገናዝብ ያደርግሃል። ለዚህም ይመስለኛል በውጭም በሃገር ቤትም የሚገኘው ህዝብ በሚያስደንቅ መልክ የተንቀሳቀሰው።

ክፋታቸውን ቢያሳይ አንድ ምሳሌ ልንገርህ ፦
የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ፍርድ ቤት ቀርበው በነበረበት ጊዜ፤ በርሃብ ምክንያት መናገር እንኳ አቅቷቸው፤
ለዳኛው ምግብ በልተን አናውቅም ብለው ሲናገሩ፤
ዳኛው ደንግጦ ምግብ አምጡላቸው ብሎ
**ፍርድ ቤት ውስጥ እኮ ምግብ ተበላ!**
እነኚህ ሰዎች እኮ ያሰሩትን ሰው በርሃብ የሚቀጡ ናቸው !
እረ ስንቱን..... ዘርዝሬ እችለዋለሁ። ...

በዚሁ ጉዳይ ላይ ከአንድ ኢትዮጵያዊ ምሁር ጋር ስንወያይ "በታሪክ ውስጥ አንዳንድ ሰዎች ለለውጥ ምክንያት ይሆናሉ" ነበር ያለኝ። እኔም አንዳርጋቸው የለውጥ ምክንያት እንደሆነ ነው የሚሰማኝ። በርግጥ በዚህ መልክ መሆኑና እየደረሰበት ያለውን ስቃይ ስታስብ ቢያምህም በህዝብ ውስጥ የፈጠረው የመተሳሰብና የአብሮነት ስሜት ግን ቀላል አይደለም። ፊት ለፊት የማይተያዩና መነጋገር የማይፈልጉ ተቃዋሚዎች ያወጡትን ተመሳሳይ ቁጭት፤ እልህና ንዴት የተንጸባረቀበትን መግለጫ ስታየው ህወሃቶች እራሳቸው ምነው በቀረብን ሳይሉ የሚቀሩ አይመስለኝም። አንዳርጋቸውን መያዛቸው በርግጥም "አሳ ጎርጓሪ.." ሆኖባቸዋል በሚለው ሃሳብ እስማማለሁ።

**<u>አሻራ፦</u> አሁን ደግሞ በቅርቡ ለእይታ ወዳቀረብከው "ተላላኪው ማነው?" ወደሚለው የምስል ዘገባ ልመልስህ፦ ይህን ስራ ለማቅረብ ምክንያት የሆነህ ወይም መነሻ ሃሳቡን ያጫረብህ ጉዳይ ምንድነው?**

***<u>ታማኝ፦</u>*** እኔ ...! ሁሌም በአይምሮዬ የሚመላለሱ ጥያቄዎች አሉ፦ የህወሃት መሪዎች ከሚቹ ጠ/ሚንስትራቸው ጀምሮ "እነዚህ የሻቢያ ተላላኪዎች" የሚሉት ነገር አለ። እናም ሁሌ እነኚህ ሰዎች እውነት ሰው አያውቅብንም ብለው ያስባሉ? እያልኩ እራሴን እጠይቃለሁ። አንድ ነገር ኮሽ ባለ ቁጥር "እነኚህ የሻቢያ ...." ሲሉ እየቀለዱ ነው? እላለሁ።

አሁን ደግሞ አንዳርጋቸውን ከያዙ በኋላ ይህንኑ አባባላቸውን ደጋግመው ሲጠቀሙበት .... አልበዛም? የሚል ስሜትና የነሱ መሬት የለቀቀ ውሸት ነው ለሥራው ያነሳሳኝ።

**<u>አሻራ፦</u> አቶ አንዳርጋቸውን ለሁለተኛ ጊዜ በቴሌቪዥን መስኮት ያቀረቧቸው "ተላላኪው ማነው?" የሚለው የታማኝ የምስል-ዘገባ በኢሳት እንደሚቀርብ ከማስታወቂያው በማወቃቸው ሳይቀደሙ ለመቅደም አስበው ነው ሲሉ ብዙዎች አስተያየት ሰንዝረዋል። በተለይ ያቀረቡት የፊልም ዘገባ የሚጀምረው "የሻቢያ ተላላኪዎች" በሚሉ ቃላት መሆኑ የአስተያየቱን ትክክለኝነት ያንላዋል ይላሉ...በዚህ መልክ ታይቶሃል?**

***<u>ታማኝ፦</u>*** እንዳልከው የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ሰምቻለሁ። ምንድነው ከባዱ ነገር መሰለህ ? የኔ ስራ ከመውጣቱ በፊት ለመቅደም ሲሉ አዘጋጁት ብል የኔ ከፍታ ሊጨምር ነው፤ መንጠራራት ሊሆንብኝ ነው። ከኔጋ እየተከራከሩ ነው ማለት በጣም በጣም ይከብዳል። ከተለያዩ ሰዎች የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ስትመለከት፤ የቪዲዮው ያለ ጥንቃቄ ተከታትፎ (በአግባቡ ኤዲት ሳይደረግ) በችኮላ መቅረብ፤ የተጠቀሙበት ቃልና ከኔ ሥራ ጋር በአንድ ቀን መልቀቃቸው እነኚህን ነገሮች እንድታስብ ያደርግሃል። ጥድፊያቸው ደግሞ ከአንዳርጋቸው ቃል ጀርባ ያለውን የጣር ድምጽ እንድንሰማ እስከማድረግ ያደረሳቸው ነው። ይህን ይህን ደማምረህ ስታይ አንተ ከምትለው ጋር ይቀራረባል ። እኔ ግን ለኔ መልስ ሰጡ ብዬ ማለት ይከብደኛል።

**<u>አሻራ፦</u> እንደ መንግስት አስበሃቸው ይሆን ለኔ መልስ እየሰጡኝ ነው ማለት ይከብደኛል ያልከው?**

***<u>ታማኝ፦</u>*** በጭራሽ!! እንደ መንግስት ቢያስቡና እኔም እንደ መንግስት ባስባቸውማ በወደድኩ ነበር። ዋናው ችግር እንደ መንግስት አለማሰባቸው ፤ እንደ መንግስት አለመስራታቸው አይደል እንዴ?እንዴት አድርጌ ነው እንደ መንግስት የማስባቸው? እኔ ይህን የምለው ሕዝብን ከማክበር ነው። በግለሰብ ደረጃ የሰጠሁት አስተያየት ወይም ያቀረብኩት ስራ ሊታይ የሚገባው በዛው ደረጃ መሆኑን ስለማምንበትና ከዛ በራቀ እንዳይታይብኝ ነው።

**<u>አሻራ፦</u> በቅርቡ በጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና አወያይነት አንተ፤ አቶ ኤርሚያስ ለገሰና የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ወንድማገኝ ጋሹ በኢሳት ቀርባችሁ ባደረጋችሁት ውይይት ብዙዎችን ያስገረመ ነገር አስደምጠሃል። ያስደመጥከው ነገር፦ ጥቂት የወያኔ ባለስልጣናት በተገኙበት ውይይት ላይ አቶ በረከትና አቶ አዲሱ የተናገሩትን ነው። ይህ ውይይት በኢሳት መደመጡ ተቃዋሚው ወያኔ ጉያ ውስጥ ለመግባቱ አመላካች ሆኗል የሚሉ ብዙዎች ናቸው። ትግሉ የደረሰበትን ደረጃም ያሳያል የሚሉም አሉ፡፡ እንደ ጥያቄ ማንሳት የምሻው ይህን አይነት ጥብቅ ሚስጥር ኢሳት እጅ ሊገባ መቻሉ የተቃዋሚው የመረጃ ክፍል ጥንካሬ ወይስ ወያኔ ውስጡ ከመቦርቦሩ ጋር በተገናኘ እየሆነ ያለ ...?**

***<u>ታማኝ፦</u>*** ህዝቡ እኮ ታፍኖ የመጨረሻ ግፍ እየተቀበለ ነው ያለው። ደርግ ከፉ ነገሮችን ሁሉ ጨርሶ አድርጓቸው ሄዷል፤ ከደርግ በላይ ማንም ምንም አይነት ግፍ ሊፈጽም አይችልም የሚል እምነት ነበርን፡፡ እነዚህ ግን እኮ ሁሌም የሚሰሩት ግፍና ክፋት እያስደነቀን ነው።

ክፋታቸውን ቢያሳይ አንድ ምሳሌ ልንገርህ፦ የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላት ፍርድ ቤት ቀርበው በነበረበት ጊዜ፤ በርሃብ ምክንያት መናገር እንኳ አቅቷቸው፤ ለዳኛው ምግብ በልተን አናውቅም ብለው ሲናገሩ፤ ዳኛው ደንግጦ ምግብ አምጡላቸው ብሎ ፍርድ ቤት

[ወደ ገጽ 18 ዞሯል]

# የመለስ ጂዮ-እስትራቴጂ "ትሩፋቶች" እና አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት በአፍሪካ ቀንድ

ከዩሱፍ ያሲን (ኖርዌይ - ኦስሎ)

- "የታላቁ ባለራዕይ መሪ" ሁለተኛው የሙት ዓመት ዝክር እየተከበረ ብቻ ሳይሆን፣ ውርስ ቅርሳቸው (ሌጋሲ)ግራ ቀኙን እያወዛገበ ባለበት ባሁኑ ጊዜ፣

- ከኤርትራ መከላከያ ሃይል ጋር በመተባበር የሩሲያ ወታደራዊ ኃይል የጋራ የጦር ልምምድ ለማድረግ አስፈላጊውን ዝግጅት አጠናቅቋል በሚባልበት በአሁኑ ወቅት፣

- የአንደኛው የዓለም ጦርነት ጅማሮ መቶኛ ዓመት በሚከበርበት ባሁኑ ወር፣

- የግብፁ አዲሱ ፕሬዚዳንትና ጠንካራ ሰው ጄኔራል አል-ሲሲ ሩሲያን ጎብኝተው ለአዲሱ ትብብር በር የሚከፍቱ ስምምነቶች ፈርመው በተመለሱበት ባሁኑ ወቅት፣

- የበርሊን ግርግዳ ፈርሶ በሁለቱ ልዕለ- ኃያል መንግስታት መካከል ለአስርተ ዓመታት የተጧጧፈው ቀዝቃዛ ጦርነት ካበቃ 25 ዓመታት ካስቆጠረ በኋላ፣አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት የሚመስል ፍጥጫ በዩክሬን ምክንያት እየተመለከትን ባለንበት ባሁኑ ወቅት፣

- ይህ ጦርነትና ፍጥጫ ወደ ቀይ ባህር ደጃፋችን ድረስ መጥቶ ሰላማችንን ማደፍረስ ይችላል ተብሎ በሚሰጋበት ባሁኑ ወቅት፣

- ከየት መጣ ሳይባል እስካሁን የነበሩትን ዓለም አቀፍና አካባቢያዊ የመንግስታት አወጋገንና ጎራ ለይታዎችን ባንድ ጀንበር አመሰቃቅሎ እንደገና ስሌቶቻቸውን እንዲከልሱ በማስገደድ ላይ ያለው የሙስሊሙ መንግስት (the Islamic State of Iraq & Syria- ISIS or Da'ish) እንደ አንድ የዓለም ሰላምና መረጋጋት ስጋት ተደርጎ በተፈረጀበት ባሁኑ ወቅት፣

ዓለማቀፋዊ አካባቢያዊ አዳዲስ ክስተቶች፣ዕድገቶችና አንደርዳሪ ግፊቶች (ዳይናሚኮች) ጎራ ለይታዎችን ከስረ-መሰረቱ እያናጉ ናቸው። ተለዋዋጭ አሰላለፎችን እያስከተሉ ናቸው። አዳዲስ የሃገራት አሰላለፎችንና የአወጋገን አጠማመሮችንም እየተመለከትን ነን።

ገና በጥንት በጠዋቱ ኢትዮጵያ በዓለም መንግስታት እንደ ወጋኝ፣ አጋርና ሸሪክ በየዘመናቱ "ልዕለ-ሃያላን" ስትፈለግና ስትታጭ ኖራለች። ከዛሬ 800 ዓመት በፊት ከአውሮፓ በዘመቱት የመስቀል ጦረኞች (Crusaders) እና በሙስሊሙ ሃይል መካከል ለ 300 ዓመታት ከዘለቀው ደም አፋሳሹ እየሩሳሌምን ለመቆጣጠር ሲደረግ ከነበረው ፍልሚያ ጀምሮ ማለት ያስኬዳል። አውሮፓውያን ተፋላሚዎች ከደቡብ በኩል እንዲያግዛቸው ተረተ-ቀመስ ትረካዎች የሚነገርለትን ፕረስተር ጆን የተባለው ነጋሲ ቀሲስን (Prester konig) ግዛት ፍለጋ ወደ ምስራቅ አፍሪካና ኤሺያ ልዑካን ካሰማሩበት ዘመን ጀምሮ። በዚያን ጦርነት እንደ አንድ "ክርስቲያን" ሃገር ያሳጫት ተፈላጊነት ዛሬም እንደ አንድ አካባቢ ሃይል ተመራጭነቷን ከፍ ያደርገዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም በዓለም አቀፍ ጸረ-ሽብር ዘመቻ ሸሪክና ወጋኝ አጋር ፍለጋው ከሌሎቹ አስበልጦ አሳጭቷታል።

ኢትዮጵያ ለዚህ አሰላለፍ የሚያበቃት ግን ይህ እሳቤ ብቻ አይደለም። የቀይ ባህር ዳርቻነቷ፣ የአባይ ውሃ አመንጪነቷ፣ የህዝቧ ብዛት፣ የመሬቷ ስፋትና እምቅ ሃብቷ ጭምር እንጂ። ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ በመስቀል ጦርነት ተሳትፋለች ወይስ አልተሳተፈችም የሚለውን ክርክርና እሰጥ-አገባ ወደጎን ትተን ለጊዜው በተፈላጊነቷ እናስምርበት። ሌላም መሰመር ያለበት ነጥብ አለ። የሃገሪቱን የስልጣን መዘውር ማን ያዘ ማን የሚለው ከግምት ሳይገባ፤ በአፍሪካ ቀንድ ባላት ጂዮ ፖለቲካው ስፍራ ምክንያት ትናንትም ዛሬም ተፈላጊ ናት። እንደነሳውዲ አረቢያ የነዳጅ ሃብት አምራች ሳትሆን፣ የምትለዋንም ሃረግ ልጨምር መሰለኝ።

የቱርክ ዑስማኖች የምዕዋ የባህር ጠረፋችንን በተቆጣጠሩበት በ1517ዓ.ም. ላይ የመስቀል ጦርነቶች አብቅተው ነበር። ነገር ግን የራሳችን ሃይማኖትን ምርኩዝ ያደረገ የርስ-በርስ መሻኮት ነበረ። ከ1529 -1543 በተደረገው ውጊያ። ቱርኮች በአህመድ ግራኝ ከሚመራው ከሙስሊሞች ኢትዮጵያውያን ኃይል፣ ፖርቲጊዞቹ ደግሞ ከክርስቲያኑ ንጉስ ጎን በመሰለፍ ባዕድ ሃይሎች የእርስ በርስ ጉዳያችን ውስጥ እጃቸውን ጣልቃ አስገብተዋል። በኋላ ይህን ተከትሎ ወደ ሃገራችን የገቡት አውሮፓውያኑ ካቶሊክ ሚሽነሪዎች ስለ ኢትዮጵያ በመጽሃፍቶቻቸውና በጉዞ መዛግብታቸው ሃገሪቷንና ህዝቧን በእርግጥ አስተዋውቀዋል። "የሮማን ኤምፓየር ማሽቆልቆልና ውድቀት" በተባለው ባለ ብዙ ቅጾች መጽሐፉ የሚታወቀው የእንግሊዙ የታሪክ ጸሃፊ ኤድዋድ ጊቦን (Edward Gibbon 1737-1794) "ኢትዮጵያ የረሳትን ዓለም ረስታ ላንድ ሺ ዓመት አንቀላፍታለች" ያለው የሃገሩቷ የታሪክ ምዕራፍ ካከተመ በኃላ መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ በመስቀል ጦርነት ማንንም ወግና አልተሳተፈችም መባሉ ተቀባይነት የሚያገኘው ምናልባት ከዚህ የመገለል ትረካ ጋር መገጣጠሙ ሊሆን እንደሚችል እሙን ነው። ሌላ አከራካሪ ነጥብም ያቀርባሉ - አልተሳተፈችም ባዮቹ። ሣላሓዲን አል አዮቢ የተባለው የሙስሊሙ መሪ ዛሬ በእየሩሳሌም የሚገኙትን የዴር አል ሡልጣን አቢያተ ክርስትያን ለኢትዮጵያ ምዕመናን ያበረከተው በጦርነቱ ባለመሳተፉም ጭምር ነው የምትለዋን እሳቤ።

ይህንን ያህል በታሪክ ትዝታ ወደ ኃሊት መጓዙ ያስፈለገበትን ምክንያት ማግኘቱ አይገድም። የእዚያን ጊዜው አወጋገን ለይታ፤ የሃይል አሰላለፎችና የቃል ኪዳን አጠማመሮች ከዛሬው ጸረ ዓለም አቀፍ ሽብር ኢጋርነትና ሽርክና በመሰረቱ በሁሉም መመዘኛዎች አይመሳሰልም። ዛሬ፣ ዛሬ ካርል ማርክስን መጠቃቀሱ ከጊዜ ጋር የሚሄድ የዕውቀት ማሳያ መመጻደቂያ ባይሆንም ቅሉ፤ "ታሪክ ራሱን ይደግማል ቢባልም፣ በተመሳሳይ አግባቦች አይደለም" ማለቱ አንከን የማይወጣለት ዛሬም ለጥቅስ የሚበቃ አባባል ነው።

ዛሬም ወደ አካባቢያችን ቱርኮች እየመጡ ናቸው። ዛሬም እውቅ የፖርቱጋል ተወላጆች በሃገራችን ጉዳይ እጃቸውን እያስገቡ ናቸው። ቱርኮች ዛሬ ወደ አስመራ፣ ሞቃዲሾና አዲስ አበባ ወጣ ገባ የሚሉት የዕምነት ተጋሪዎቻቸው የሆኑት ሙስሊሞችን ለማገዝ አይደለም። እንደ ነዋይ አፍሳሾች ኢንቬስተርና የእንዱስትሪ እቃ ሻጭ እንጂ። ዛሬ ጆሴ ማኑኤል ባሮስ (Jose Manuel Barrso) እና አና ጎሜዝ የአውሮፓ ኮሚሽንን እና የአውሮፓ ፓርላማን ወክለው ነው ከኢትዮጵያውያን ባለስልጣናት ጋር ስለ ሰው ልጅ መብት የሚከራከሩት። ቱርክ የእርስ በርስ ጦርነት ለሚያንገላታት ሶማሊያ እርዳታ ትሰጣለች። ቱርክ አይሮፕላኖቿም ሁሉም አየር መንገዶች የተጠየቁትን የአስመራ በረራ እንዲጀምሩ በቅርቡ ስምምነት መፈርሟን ነው የዜና አውታሮች የዘገቡት።

በቀይ ባህር "ጠረፋችን" ዛሬ ኢራኖችም እስራኤሎችም አሉ ተብሏል። አጃኢብ! የሚያሰኘው ግን ኤርትራ ሁለቱን ተፈላላጊ

ጠላቶች ጎን ለጎን ማስተናገድ መቻሏ ነው። በዳህላክ ደሴቶች እስራኤሎችን አስፍራለች፣ በአሰብ አቅራቢያ ደሴቶች ደግሞ የኢራን ወታደሮችን በማስተናገድ ላይ ናት መባሉ ነው። እሳትና ውሃ በማደባለቅ። ለማንኛውም ኢራንም ሆነች አይሁዳውያን ለአካባቢያችን አዲስ አይደሉም። ከአረቦች ጋር በጉርብትና ጎን ለጎን ለብዙ ብዙ ምዕተ ዓመታት ኖረዋል። በመካከለኛው ምስራቅ ቀጠና ይካተቱ እንጂ ሁለቱም አረቦች ያልሆኑ ሃገራት ናቸው። ኢራን የሺዓ እስልምና የምትከተል ሃገር ስትሆን እስራኤል አይሁዳዊ ናት። ኢራንና ቱርክ ግን ሙስሊም ቢሆኑም አረብ ያልሆኑ የመካከለኛ ምስራቅ መንግስታት ናቸው። በሃይማኖታቸው ሙስሊም ቢሆኑም በረዥሙ ታሪካቸው ከአረቦች ጋር ከግጭት የጸዳ ጉርብትና ኑሯቸው አይውቅም። በተለያዩ ምክንያቶች። ባንጻሩ ልክ እንደ ኢራንና ቱርክ ለአካባቢው ጸጉረ ልውጥ (አረብ ያልሆነችው) አይሁዳዊት እስራኤል በዚህ አካባቢ ከተመሰረተች 66 ዓመቷ ነው። አይሁዶች እንደ ህዝብ ግን ከአረቦች ጎን ለብዙ ሺ ዓመታት የኖሩ ናቸው። ሃገራችን ኢትዮጵያም ሌላዋ ጸጉረ ልውጥ ወይ "ዓጅም" የሆነች ሃገር ናት።

አረቦች አረብ ያልሆኑትን "ዓጀም" ይሏቸዋል። ልክ አይሁዶች፣ አይሁድ ያልሆኑትን "ጎይ" ወይም "ጎይም" ብለው እንደሚጠሯቸው ሁሉ። እኛ ለአረቦች "ዓጅም" ብቻ ሳንሆን "ሓበሻ" ነን። አረቦች ለኢትዮጵያ እንደ ሃገር፣ ለኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ የሚሰጡትና የሚያውቁበት ስያሜና አጠራር ነው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ እነሱ ዘንድ ምንም ዓይነት አሉታዊ ቃናም ሆነ ቅላጼ የለውም። እነዚህ አራት አረብ ያልሆኑት ሃገሮች ማለት እስራኤል፣ ቱርክ፣ ኢራንና ኢትዮጵያ መካከለኛ ምስራቅ በተሰኘው አካባቢ ከአረቦች ጋር በታሪክ ሂደትና በአሰፋፈር ንክኪነት የነበራቸው ዘርፈ ብዙ የወዳጅነትም ሆነ ጠላትነት ትስስር በዛሬ ግንኙነታቸው ላይ ራሱን የቻለ ተጽዕኖና አሻራ አሳርፏል።ይህ ታሪካቸው የዛሬ መስተጋብራቸውን ያወሳስበዋል። አንዱ ህዝብ ስለ ሌላው በልበ-ልቦናው በታሪክ ሂደት የቋጠረው አመለካከት የራሱን ድርሻ ያበረከታል ለማለት ፈልጌ ነው። የዚህ አተያይ ምንጩ በገሃድ የሚታወቅ ዕውነት ሊሆን ይችላል ወይም ለእነሱ የሚመስላቸው መላምትም (Perception) ሊሆን ይችላል። ያንድ ሃገር የደህንነት ፖሊሲና የውጭ ግንኙነት አግባቦች በመሰረቱ ከዚህ የጸዱ ናቸው ባይባልም ቅሉ ግቡ ብሔራዊ ጥቅም ማስከበር ነው፤ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ።

እነዚህ አራት አረብ ያልሆኑ የመካከለኛ ምስራቅ ተካታች ሃገራት ባንድ በኩል ከአካባቢው አረብ ሃገራት፣ በሌላ በኩል ከዚያን ጊዜ ልዕለ- ሃያል ከአሜሪካ ጋር የነበራቸው ግንኙነት (በአቋም አወሳሰዳቸው ላይ) ወሳኝ ድርሻ ነበረው ለማለት ያስድፍራል - አፍ ሞልቶ። በተለይም ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በነበረው አወጋገንና አሰላለፍ። ምክንያቱም እነዚህ ሃገራት ምንም እንኳን "ዓጀም" ወይም አረብ ያልሆኑ ተብለው ቢፈረጁም መካከለኛው ምስራቅ በተሰኘው ጂዮ-ፖለቲካዊ ቀጣና የሚካተቱ ናቸው፤ በአብዛኛዎቹ አጥኚዎች ዕይታ።

ከአሜሪካ ጋር የነበራቸው መስተጋብርና ትስስር ደግሞ እርስ በርሳቸው በመሰረቱት ማለፊያም ሆነ የተበላሸ ግንኙነት ላይ በተራው የራሱን ተጽዕኖ ማሳረፍ መቻሉ አሌ የማይባል ነው። የሚገርመው ግን አራቱም አረብ ያልሆኑ ሃገራት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት

'ተዛወሪ መኪና ሞስኮን አስመራን ኮይኑ መዛወሪዬ"ማለታቸው የት ይቀራል። ድሮ ኢትዮጵያ ወይም ሞት ባሉበት ጊዜ "ሸዋን አስመራን ኮይኑ መዛወሪያዬ" እንዳሉት ማለት ነው። የጋራ የባህር ላይ ወታደራዊ ልምምዱ የዓላማቸው ፈንጣቂ መልዕክት ነው።

የአሜሪካ መራሹ የ"ነጻ ዓለም" ጎራ ወጋኞች ነበሩ። አንዳንዶቹ የአሜሪካ ወዳጅ ወታደራዊ ቃል ኪዳን ትብብሮች አባላትም ጭምር ነበሩ።ለምሳሌ ቱርክ የናቶ ( NATO) ቃል ኪዳን ሃገሮች አባል ብቻ ሳትሆን፣ የዛሬውን አያድርገውና በደቡብ ሽንጥ የሶቭየት ህብረት ብቸኛ ድንበርተኛ ነበረች። ልክ በሰሜኑ ሽንጥ ኖርዌይ እንደ ነበረች፤ አሁንም እንዳለች ሁሉ። አዲሱ የኖቶ ዋና ጸሓፊ ኖርዌጂያዊ ሊሆን ነው ፤ በቅርቡ።

ዛሬ በአለም አቀፍ መድረክም ሆነ በአካባቢያችን በርካታ አዳዲስ ጎር ለይታና የሃገራት የአወጋገን አሰላለፎች እንመለከታለን። በኢራኑ ሻህ ዘመን (1941-1979) ወዳጅ የነበሩት ኢራንና እስራኤል ለህልውናቸው ወሳኝ በሆነ ትንቅንቅ ተጠምደዋል። በኢራን የኑክሌር ሃይል ባለቤትነት ዙሪያ ባጠነጠነ ግብግብ። የቱርክና የእስራኤል ግንኙነትም ሻክሯል። ዛሬ ሰልጆ ከእስራኤል ጋር ከመሆኑ ይልቅ ላለፉት 66 ዓመታት የራሷን ህልውና ከተፈታተኑት ፍልስጠማውያ ጎን ነው መባሉ እምብዛም ሚጋነን የለበትም። በተለይም የዛሬ አራት ዓመት የእስራኤል ኮማንዶ ወደ ጋዛ ሰርጥ በማምራት ላይ በነበረው የቱርክ መርከብ ላይ ጥቃት ካደረሰ ወዲህ። የሁለቱም መንግስታት ወዳጅ ተብሎ የሚገመተው የአሜሪካ መንግስት የማስታረቅ ሙከራዎችም ብዙ የፈየዱ አይመስሉም።

ኢትዮጵያ ልክ እንደነዚያ አሜሪካ ወጋኝ ሃገራት (ኢራን፣ ቱርክና እስራኤል) ሁሉ በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ ተካታች ሃገር ብቻ ሳትሆን በአፍሪካ ቀንድ ማዕከላዊና እስትራቴጂያዊ ስፍራ የተቆናጠጠች ታሪካዊ ሃገር ናት። ዛሬ በሃገሪቷ ስልጣን ላይ ያለው የወያኔ/ኢህአዲግ መንግስት ለምዕራባውያኑ መንግሥታት የአሜሪካ የዓለም አቀፍ ጸረ-ሽብር ዘመቻ አጋርና የልማት ሽሪክ ሆኖ የሚቀርበው በዚህ ዓለም አቀፍና አካባቢያዊ ሁኔታ ውስጥ ነው። እንዲያውም አሁን አሁን «የሙስሊሙ መንግስት» (ካሊፌት) የተባለው ቡድን የቆዩ ጎራ ለይታዎችን ከስረ መሰረቱ ያናጋበት ምስቅልቅል ሁኔታ ነው ያለው።

ኢትዮጵያችን የአፍሪካ ቀንድ ዋነኛዋ ተዋናይ ናት፤ በሁሉም መመዘኛዎች። በአፍሪካ ቀንድ አሉ ከሚባሉት ህዝቦች አብላጫው ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ ነው። ኢትዮጵያ በራሷ ነጻነቷን አስጠብቃ የኖረች ሃገር ስትሆን፣ ሌሎች በቅኝ ግዛትነት ተይዘው የነበሩ ሃገራት ተራ በተራ ነጻ በወጡበት ጊዜ አዳዲስ አጎራባችም ድንበርተኛም አገኘች ማለት ነው። የመጨረሻዎቹ አዳዲስ አጎራባቾቿ ከሱዳን የተገነጠለው ደቡብ ሱዳናና ከራሷ ከኢትዮጵያ የተገነጠለችው ኤርትራ ናቸው። በ1977 ነጻ የወጣችው ጂቡቲም በዚህ ስር ትካተታለች። በ1964 እና 1956ዓ.ም. በተከታታይ ነጻነታቸውን ከእንግሊዝ የተቀዳጁት ኬኒያና ሱዳን አሉ። የሶማሊያ ሪፐብሊክም በ1960ዓ.ም. ነጻ ወጥታ ጸብ ጫሪ ጎረቤት ሆና መዝለቋ የሚታወቅ ነው።

በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ባለስልጣናት ምንም እንኳን ደጋግመው ከ "ኤርትራ በስተቀር ከሁሉም አጎራባች ሃገራት ጋር የመልካም የጉርብትናና የትብብር የወዳጅነት ግንኙነት" አለን ቢሉም ቅሉ በነዚህ አጎራባች ሃገራት የተረጋጋ ሁኔታ እስካልሰፈነ ድረስ አርፎ እንቅልፉን የሚለጥጥ መንግስትምሆነ አገዛዝ አይኖርም። በደቡብ ሱዳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሶማሊያ ደግሞ

ወደ ገጽ 28 ዞሯል

AFRICAN TOWN
አፍሪካን ታውን
CAFE BAR & RESTAURANT

Gezahagn Yedete
Manager
Mobile : 0401 331 652

161 - 163 Nicholson Street
Footscray, Victoria 3011

Phone : (03) 9689 1599
Phone : (03) 9689 9660
Fax : (03) 9689 9490
gezahagn@africantown.com.au
www.africantown.com.au

AFRICAN TOWN RESTAURANT

Doro Wat $10
(Chicken)
Lega Tibes $10
(Roasted Lamb)
Kitfo $10
(mince meat seasonal with herbed butter and hot red pepper)
Gored gored $10
(Chunks of raw, fresh beef seasoned with special butter mitmita and pepper)
Zil Zil Tibes $10
(Grilled meat)
Key Wot $10
(Beef stew)
Minchet Abish $10
(minced beef stew)
Kurt $10
(Raw meat)
Vegetarian $10
(Lentils, Yellow split peas, beans, chick peas, beetroot, potato)

Vegetarian & non-vegetarian combination

SHININGFRESH
carpet :: tile & grout :: upholstery

0412 646 621

Our Services

- Residential Carpet Cleaning
- Commercial Carpet Cleaning
- Tile and Grout Cleaning
- Upholstery Cleaning
- Pet Odor Control and Removal
- Stain Removal
- Natural Stone, Limestone...

Carpet

Tile & Grout

Upholstery

We provide all our customers in Melbourne (especially in Bundoora or Northen Western and Eastern area) by professionally quality to clean your carpet, tile & grout and upholstery. Our team have been trained by Jena Dyco which is approved by Australian government. Every single service will be completed step by step. There is many things you do not know about your carpet but our experience will help you to understand how to deal with your carpet problems.

Hot Promotion

Cleaning Specials

Deluxe Carpet Cleaning
Only $35 per room
*standard room 10sqm.

Carpet and Upholstery Cleaning
Tile and Grout Cleaning
For $5.50 p/sqm*

Address : 8 Riley Court
Burnside/ Caroline Springs
VIC 3023

Email : admin@shiningfresh.com.au ---www.shiningfresh.com.au

# 2007

## መልካም አዲስ አመት ይሁንልዎ!

አዲሱ ዓመት ለሰላም ለፍትህና ለዲሞክራሲ
የሚደረገው ትግል ፍሬያማ የሚሆንበት
ዓመት እንዲሆን እንመኛለን!!!

ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር!

# ሰቆቃ በወያኔ እስር ቤቶች

ከወንድማገኝ ጎሹ

ባለፉት 23 ዓመታት ውስጥ በህወሀት/ኢህአዲግ የጸጥታ ኃይሎች ተይዘው ወደ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራና ወደ ሌሎችም የማሰቃያ ስፍራዎች በተወሰዱ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ላይ እጅግ ዘግናኝ በደሎች ሲፈጸምባቸው ቆይቷል። በድብደባ ብዛት ህይወታቸውን ያጡ፣ ጤነኛ ሆነው እንዳልታሰሩ ሁሉ ዓይናቸው ታውሮ፣ ጆሯቸው ደንቁሮ ወይ መራመድ እየተሳናቸው ከእስር በክራንች የሚወጡ ንጹሀን ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው።

በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ ስለሚፈጸመው ሰቆቃ የሚያጋልጡ የተለያዩ ሪፖርቶች በየዓመቱ ይወጣሉ። ሪፖርቶቹ ሁሉ ግን እንደናሙና ማሳያነት የሚወሰዱ እንጂ ጠቅላላውን መሪር ዕውነት ለማሳየት የሚበቁ አይደሉም። እኔም በዚህች አጭር ማስታወሻ ሰፋ ያለ ዳሰሳ የማድረግ ሀሳብ የለኝም። የመጽሄቷ አዘጋጆች ከማስታውሳቸው ሰለባዎች መሀል ጥቂት አብነቶችን እንዳነሳ በጠየቁኝ መሰረት ነው በሰብአዊ መብቶች መርማሪነት ዘመኔ እየተዘዋወርኩ ጉዳዮቻቸውን ከተከታተ ልኳቸው ሰለባዎች መሀል ጥቂቱን ላነሳሳ የፈለኩት። ምጥን ናሙና አድርጋችሁ ውሰዷቸው።

❁ ❁ ❁

ሁሌም ከማስባቸው ሰለባዎች መሀል የሰባት ቤተሰብ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶ አበራ ሄይ አንዱ ናቸው። እኚህ የ40 ዓመት አባወራ በወረዳ 19 ቀበሌ 55 በቤት ቁጥር 631 ነዋሪ ነበሩ። አቶ አበራ ለ16 ዓመታት ካገለገሉበት ከንፋስ ስልክ ክር ፋብሪካ በ1990 ዓ.ም. ከስራ ቢቀነሱም ሰባት አባላት ያሉበትን ቤተሰብ የጉልበት ስራ እየሰሩ ሲያስተዳድሩ የቆዩ ታታሪ ሰራተኛ ነበሩ። ባንዲት የፋሲካ ዋዜማ ግን የመላው ቤተሰቡ ህይወት ተቀየረ።

በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ቅዳሜ ሚያዚያ 18፣ 1995ዓ.ም ከንጋቱ 12 ሰዓት ላይ የህወሀት የደህንነት ኃይሎች ከወረዳ 19 ፖሊሶች ጋር በመሆን ከአቶ አበራ መኖርያ ቤት ተገኙ። በወቅቱ አቶ አበራ በማግስቱ እሁድ ለሚከበረው የፋሲካ በዓል በአካባቢው ልማድ መሰረት ከወዳጅ ዘመድ ባሰባሰቡት ገንዘብ የቅርጫ ስጋ ለማከፋፈል ተዘጋጅተው እየተጠባበቁ ነበር። እንዳሰቡት ግን አልሆነም። ታጣቂዎቹ የለሊት ልብሳቸውን እንዲቀይሩ እንኳን ሳይፈቅዱላቸው ወደ ወረዳ 19 ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷቸው።

ባለቤታቸው የታሰሩበትን ምክንያት ለማወቅና ስንቅና ልብስ ለማቀበል ወደ ጣቢያው ቢሄዱም የሚያስተናግዳቸው አልነበረም። ጭራሽም ከ20 ደቂቃዎች በኋላ እስረኛው ባለቤታቸው በያዟቸው ሁለት የህወሀት ታጣቂዎች ታጅበው ኮድ ሁለት በሆነች በባለ ሁለት ጋቢና ፒክ አፕ መኪና ተጭነው ሲወሰዱ ታዩ። በስቃይ ማዕከልነቱ የገነነ ዝና ወዳተረፈው ወደ ማዕከላዊ ወንጀል ምርመራ እስር ቤት።

ቤተሰቦቻቸውም በራሳቸው መንገድ ወደዚያው አመሩ። ከብዙ ሰዓታት ጥበቃ በኋላም ከሩቁ የማየትና ዳቦ የማቀበል ዕድል አገኙ። በማግስቱ እሁድ የፋሲካ ዕለት ጠዋትም እንዲሁ ቤተሰቡ በማዕከላዊ የተገኘው ገና ከጠዋቱ 3:30 ላይ ነበር። መርማሪውን ለማናገር ባይሳካላቸውም የዕለት ሁኔታ መዝጋቢው ሰው ስልክ ቁጥራቸውን ተቀብሎ መርማሪው ሲመጣ እንደሚደውልላቸው ቃል በመግባት ነበር ያሰናበታቸው።

በማግስቱ ሚያዚያ 20 ቀን ግን ያልተጠበቀ ዜና ተሰማ። መርማሪዎቹ የአቶ አበራን አጎትና የእህታቸውን ባለቤት ነጥለው ወደ አንድ ቢሮ በማስገባት "እስረኛው ባልታወቀ ምክንያት ራሱን ገድሏልና አስከሬኑን ከምኒሊክ ሆስፒታል 47.00 ብር ከፍላችሁ ውሰዱ" አሏቸው።

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በምርመራው ወቅት በአካል ሄዶ እንዳረጋገጠው ከሆነ አቶ አበራ የሞቱት በደረሰባቸው ድብደባና ማሰቃየት ነበር። የቀይ ዳማው ሰው ጠቁረዋል። አገጫቸው ተሰብሯል። ጥርሳቸው ወላልቋል። በግራ ጎናቸው ላይ ‹ሰምበር› ተጋድሟል። የዘር ፍሬ ከረጢታቸው አካባቢ ዕብጠት ይታያል። ፈሳሽም ነበረው። በአፍና አፍንጫቸው አካባቢም እንዲሁ ደም ፈሷቸዋል። . . . "እራሳቸውን ሰቅለው ገደሉ" የተባሉት የአቶ አበራ አስከሬን ያረጋገጠው አሟሟት ይህን የመሰለ ነበር። ጭካኔያቸው ወደር ባጣ የህወሀት ገራፊዎች ከተቀጠቀጡ በኋላ ቤተሰባቸው አስከሬን እንዲገዛ ታዘዘ።

በወቅቱ በእጃችን የገባው የአስከሬን ምርመራ ውጤትም አስደናቂ ነበር።

የሆስፒታሉ ሪፖርት አሟሟቱን "ፖሊስ በሰጠን ቃል መሰረት አቶ አበራ ሄይ ራሳቸውን ሰቅለው ገድለዋል" ይላል። ያነጋገርነው የሜዲካል ዳይሬክተሩም ይህ ነው የሚባል ማብራርያ ለመስጠት ሳይቻለው ነበር የቀረው። ፖሊስ ገዳይ፣ እራሱ ፖሊስ መስካሪ፣ ሆስፒታል ደግሞ የፖሊስ ቃል ላይ ማረጋገጫ ፈራሚ የሆነባት የህወሀት ዘመኗ ኢትዮጵያ!

በማዕከላዊ እስር ቤት የሚገኙ ወገኖች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታቸው ይህን በመሰለበት ሁኔታ በአገዛዙ የጸጥታ ኃይሎች የተያዘን ሰው በማሰቃየትና በማስገደድ በተደበቁ ካሜራዎች እየቀረጹ የተቆራረጡ ቃላትን ለፕሮፖጋንዳ ማቅረቡ የሰቆቃውን ልክ ደብቆ ሊያስቀረው አይችልም። ሞት ምርጫ ሆኖ በማይቀርብበትና የጨለማው ገዢዎች ያሻቸውን በሚያደርጉበት በዚያ የስቃይ ጉረኖ ውስጥ ላሉ ሰለባዎች ሁሉ ከምር ማዘንና መጨነቅ፣ አሳር ቀማሾቹን ለማዳን የሚደረጉ ጥረቶችን ማጠንከሩም ወሳኝነቱ አያጠያይቅም። በሁሉም ስፍራ መሬት የወረዱ እንቅስቃሴዎች ማድረጉን ጊዜው ግድ የሚለው ዕውነታ ሆኗል። ጥቂት አብነቶች ልጨምር። . . .

❁ ❁ ❁

ተስፋዬ ተካልኝ ይባላል። ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ በሶሲዮሎጂ ተመርቆ ቱሪዝም ኮሚሽን ውስጥ ይሰራ የነበረ የ28 ዓመት ወጣት ተስፈኛ ነበር። አንድ ለናቱ። እንጨት በጀርባቸው እየተሸከሙና ጠላ ሸጠው ያሳደጉት እናቱን "ደረስኩልሽ። ቀን ላወጣልሽ ነው።" የሚልበት ምዕራፍ ላይ መድረሱ ነበር። ምን ዋጋ አለው? ተስፋው ሁሉ በአገዛዙ ግፈኞች እጅ እንደዋዛ መከነ እንጂ።



ወደ ገጽ 29 ዞሯል )

የፈረንሳዩ አንባገነን ገዥ የነበረው ናፖሊዮን ቦናፓርት በአንድ ወቅት ስለ ነጻ ፕሬስ ሲናገር "ከአንድ ሺህ ሻምላዎች ይልቅ አራት ጋዜጦች የበለጠ መፈራት አለባቸው።" ነበር ያለው።

አንባገነኖች ፕሬስን ይፈራሉ። ይጠላሉም። የህዝብ መሰረት የሌላቸው፤ በራሳቸው የማይተማመኑ ሁሉ ነጻ ሃሳብን ይጠላሉ። ነፍጥን ብቻ ተማምነው በሕዝብ ጫንቃ ላይ የሚቀመጡ፤ እንደምን ነጻ አመለካከትን ሊቀበሉ ይችላሉ? ፍጹም አንባገነናዊነት በሰፈነባቸው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች፤ ህግ አውጭው ህግ አስፈጻሚውን፣ ህግ አስፈጻሚው ደግሞ ህግ ተርጓሚውን እርስ-በርስ የሚቆጣጠሩበት እና የሚያስተከክሉበት አካሄድ የለም። ይህንን ቁጥጥር በጥቂቱም ቢሆን ይሰራ የነበረው ነጻው ፕሬስ ነው። ከዚህም አልፎ ሕዝቡ መብቱን እንዲያውቅና መብቱንም እንዲያስከብር ብዙ ሰርቷል ፕሬሱ። ሙስናን አጋልጧል፣ እንደ እንባ ጠባቂም የህዝብን በደል ይፋ አድርጓል። ይህን ማድረግ እንደወንጀል፤ ጠንከር ሲል እንደ ሽብርተኛ የሚያስቆጥርበት ሃገር ሆናለች የዛሬይቱ ኢትዮጵያ።

ሙብትን ማወቅ እና ማሳወቅ፤ ህዝብ ለጦርነት እንዲነሳ ማድረግ ነው ተብሎ ከተተረጎመ ደግሞ ጋዜጠኛን በአሸባሪነት መፈረጁ ብዙ ሊደንቀን አይገባም።

ኢትዮጵያ ላለፉት አስርት-አመታት ጋዜጠኞችን በማሰር ከአፍሪካ በቁጥር አንደኛ ደረጃ ላይ ነበረች። አሁን ይህንን ደረጃዋን ለቃለች። እድገትና ትራንስፎርሜሽኑን ተከትሎ ከመጡት ለውጦች አንደኛው መሆኑ ነው። ኢትዮጵያ የአንደኝነት ደረጃዋን ያጣችው ታዲያ ትራንስፎርሜሽኑ ይዞት በመጣው መሻሻል አይደለም። ነጻ ፕሬሱ ከሃገሪቱ እንዲጠፋ በተደረገ ሁለገብ ጦርነት እንጂ። አብዛኛው ጋዜጠኛ ተሰድዷል፣ ጥቂቶቹ ታስረዋል፣ አንዳንዶቹም አቅማቸው ተሟጦ አልቆ፤ ዝም ብለው እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ለነጋሪ የተረፉትንም እስከዛሬዋ እለት ድረስ እያሳደዷቸው ይገኛሉ።

ከጅምሩ በፕሬሱ ላይ የተከፈተው የጎሠሮው ፓርቲ ውግያ ቀላል አልነበረም። እለት ተዕለት የሚያርፍበትን የአንባገነኖች ጡጫ ችሎ ብዙ ተጉዟል። እየተንገዳገደ፤ እየወደቀና እየተነሳ የህዝብ ንቃት-ህሊና እንዲሰፋ ከማድረጉም ባሻገር የማንበብ ባህል እንዲዳብር ነጻው ፕሬስ ተግቶ ሰርቷል።

የህትመት ዋጋ እስከ 500% እንዲጨምር ቢደረግም ፕሬሱ አልቆመም ነበር። ጋዜጠኞች እንደጥጃ እየታሰሩ፣ እየተደበደቡ፣ እየተሰቃዩም ስራቸውን ላለማቋረጥ መትጋታቸውን አላቆሙም። በካድሬ ዳኞች ፍርደ-ገምድል ፍትህ ሲሰጣቸው፤ አለአግባብ በእስርና በገንዘብ ሲቀጡም ሰራቸውን አላቋረጡም.... የአሜሪካው ፍሪደም ሃውስ በተከታታይ ባወጣቸው ዘገባዎች የኢትዮጵያን ፕሬስ ስታተስ ኖት ፍሪ "ነጻ ያልሆነች" ሃገር ሲል ፈርጆታል። የፕሬስ አዋጁንም ፍጹም አፋኝ ሲል ፈርጆታል። የፈረንሳዩ ሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስ፣ የኒውዮርኩ ሲ.ፒ.ጄ. እና የብራስልሱ አይ.ኤፍ.ጄ. በሽብር ክስ የተያዙ የጋዜጠኞችን ሰነድ እያከታተሉ አሳፋሪነቱን ቢገልጹም አፍ እንጂ ጆሮ ከሌለው ስርዓት ያገኙት የስድብ ምላሽ ብቻ ነው። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂዩማን ራይትስ ዋች ይፋ ማድረጉን ተያይ ዘውታል።

ከምርጫ 97 በኋላ ግን የህሠሃት እድገት እና ትራንስፎርሜሽን፤ ጫን ያለ ነገር ይዞ ብቅ አለ። ሽብርተኝነት!

ከዚህ በኋላ ጋዜጠኛ በህገ-መንግስት ሳይሆን፤ ህጉን በሚጻረረው በአዋጅ መዳኘት እንዳለበት ተነገረ። ስርዓቱም በባሩድ ሳይሆን ይልቁንም በብእር ጫፍ እንደሚሸበር አረጋገጠ።

ይህ የሽብርተኝነት አዋጅ ቃል በቃል የተቀዳው ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ መንግስታት ሰነድ መሆኑን ሃይለማርያም ደሳለኝ ለቢቢሲ ሲናገሩ ተደምጠዋል። ድንቅ ነው። ሰውየው ግን ምን እየተናገሩ እንደሆን የሚያውቁት አይመስልም። በዚህች በሙት መንፈስ የምትመራ ሃገር ሌላም ብዙ እንግዳ ነገር እንሰማለን።

የቡሽ አስተዳደር ከቶኒ ብሌየር ጋር አልቃይዳ የተባለውን አደገኛ ሽብርተኛ ለማጥፋት የነደፉት ይህ ሰነድ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኞችን ለማጥፋት እየተጠቀሙበት እንደሆነ ነው የሚነግሩን። በሽብርተኝነት ተወንጅለው በየእስር ቤቱ የተጣሉት የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች፤ የትኛውን አውሮፕላን እንዳስጠለፉ፣ የትኛውን ህንጻ እንዳፈረሱ፣ የትኛውን ንጹህ ዜጋ እንደገደሉ ግን አልተነገረንም።

እርግጥ ነው። የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች እየተቹ ይጽፋሉ። ትችቱ ታድያ ለውጡ ላይ አይደለም። የለውጡ አቅጣጫ ላይ እንጂ። አቅጣጫው ትክክለኛ መስመር መያዝ እና አለመያዙን መተቸት ወንጀል ሲባል ለቀረው አለም አዲስ ነገር ነው። ከዚያ የባሰም አለ። ገዢውን ፓርቲ መተቸት እና ስለ ለውጥ አስፈላጊነት መጻፍ በሽብርተኝነት ያስከሰሰ ወንጀል ሆኖ ሰማን። አስቂኙ ነገር፤ አዋጁ ለኦሳማ ቢን ላደን ሽብር በም እራባውያን ሀገሮች የረቀቀ የጸረ-ሽብር ህግ መሆኑ ነው።

ጋዜጠኞች በሽብርተኝነት ሲፈረጁ ነው ነጻው ፕሬስ በኢትዮጵያ አፈር የለበሰው። ይህ የመጨረሻ ጥይታቸው መሆኑ ነው። አለማቀፍ የጋዜጠኞች ተሟጋች ተቋማት ሳይቀሩ ተስፋ የቆረጡ እስኪመስል ድረስ በዘንድሮ አመታዊ ዘገባቸው የኢትዮጵያን ጉዳይ ችላ ብለውታል። እነዚህ ተቋማት በየአመቱ ስለኢትዮጵያ ፕሬስ ሁኔታ የሚያወጧቸው ዘገባዎች የሚዘገንኑ ነበሩ። ወያኔን የማይማር፣ የደነዘዘ እና የማይለወጥ ስርዓት አድርገው ስላዩት ችላ ያሉት ይመስላል። ሃያ አመት የማይሰማ፣ ሃያ አመት የማይሻሻል፣ ሃያ አመት የማይማር ስርዓት ውሃ ቢወቅጡት እንቦጭ ሆነባቸው።

በምርጫ 97 ሰሞን በርካታ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች ቃሊቲ ተወርውረው ነበር። በጉዳዩ ላይ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ዲያሬክተር ከነበሩት ዶ/ር ማርቲን ሂል ጋር ስናወራ አንድ ጥያቄ አነሱልኝ።

"ለመሆኑ ሰርካለም ፋሲል ላይ ለምን እንዲህ ጨከኑባት? " የሚል ነበር የማርቲን ጥያቄ። እኅህ ታላቅ ሰው ይህን ጥያቄ ለምን እንዳነሱልኝ አሁን ነው የተገለጠልኝ።

የሰርካለም ፋሲልን ጉዳይ ማንሳቱ የኢትዮጵያን ፕሬስ የሰቆቃ ጉዞ በከፊልም ቢሆን ይገልጸዋል።

ሰርካለምን ከባለቤትዋ እስክንድር ነጋ ጋር አፍነው ወደ ቃሊቲ ሲወስዷት ነፍሰ-ጡር ነበረች። የመውለጃዋ ቀን ሲደርስም ከእስር አልለቀቅዋትም። በምጥ ስቃይ፣ ነብስ ውጭ፤ ነፍስ ግቢ ሁኔታ ውስጥ ሆና እንኳን አሳሪዎችዋ ርህራሄ አላሳዩዋትም ነበር። በመጨረሻ እዚያው ቃሊቲ እስር ቤት ናፍቆትን ተገላገለች።

በዚያ የጭንቅ ወቅት የሚይዘውን እና የሚጨብጠውን ያጣ ስርዓት ምን እያደረገ እንደነበር እንኳን በውል አያውቀውም። "የመንግስት ጠላት" የሚል ታፔላ ተለጥፎለት የሚንቀሳቀስ ጋዜጠኛ፤ ሊወድቅ ከሚንገዳገድ ስርዓት ከዚህም በላይ ሊደረግበት እንደሚችል ለማስረዳት ሞከርኩ።

[ወደ ገጽ 36 ዞሯል

# ... ታማኝ በየነ

## ስለ አቶ አንዳርጋቸው ....? ከገጽ 11 የዞረ

ውስጥ እኮ ምግብ ተበላ! እነኚህ ሰዎች እኮ ያሰሩትን ሰው በርሃብ የሚቀጡ ናቸው ! እረ ስንቱን..... ዘርዝሬ እችለዋለሁ?

የህዝብን ስሜት በጥቂቱም ሊያሳይ ከቻለ አንድ ነገር ልንገርህ፡- በቅርቡ ለኢሳት አራተኛ አመት ወደ ጀርመን ሄጄ ነበር፡፡ በዝግጅቱ ላይ አንድ ሰው እጁን አውጥቶ እንዲህ ሲል ተናገረ፡- “ በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ሄጄ ነበር፡፡ በክፍለ ሃገር ቤተሰቤ በሚገኝበት አካባቢ ለሚኖሩ አንድ አዛውንት ለቡና መግዣ ብዬ 50 ዩሮ ሰጠኋቸው። ተቀብለው ካመሰገኑኝ በኋላ፤ ሰማህ ወይ ልጄ ከዚህች 50 ብር ላይ ዘርዝርና 10 ብሩን ለዛ ለታማኝ በእጁ ስጥልኝ፤ ለኢሳት ገቢ እንዲያረግልኝ ብለው ሰጥተውኛል።” ነበር ያለው፡፡ ተመልከት በዚህ አይነት የኑሮ ደረጃ ያሉ ኢትዮጵያዊ እንኳ ከተሰጣቸው 50 ዩሮ 10 ለኢሳት ይሰጥልኝ አሉ።ይሄ እኮ ሌላ ምንም ማለት አይደለም። ህዝቡ ምን ያህል ነጻነት እንደናፈቀ የሚያሳይ ነው። የሰውን ፍላጎት ነው የምነግርህ፡፡

በመረጃ በኩልም ህዝቡ ለትግሉ የሚጠቅም መረጃ ለመላክ በሚገርም መልኩ ፍቃዱና ፍላጎቱ አለው። ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ሳይፈራና መስዋዕትነት ከፍሎም ቢሆን መረጃዎችን ለመላክ ይፈልጋል።

ኢሳት አሁን አብዛኛውን መረጃ የሚያገኘው ከህዝብ ነው። እኔ በግለሰብ ደረጃ ነው መረጃዎቹ የሚደርሱኝ፡፡ አንድ ጠንካራ ድርጅት ተፈጥሮ በዚህ ረገድ ስራ ቢሰራ ደግሞ ምን ያህል እንደሚተባበር መገመት ከባድ አይሆንም።

**<u>አሻራ፡-</u> ወደ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ልመልስህ፡- አቶ አንዳርጋቸው ላይ አፈናው በተፈጸመበት ሰሞን በለንደን በተደረገ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተህ በነበረበት ወቅት አቶ አንዳርጋቸው የአንበሳ ምስል በልዩ ሽልማት መልክ ሲሰጡህ ከሚያሳይ ክሊፕ ጋር አዳብለህ “ አንዳርጋቸው አንበሳውን መልሰህ ተቀበለኝ፤ ለኔ አይገባኝም!” የሚል መልዕክት አስተላልፈሃል። ይህን ያዩ ሰዎች ለአንድ ሃገር አንድ አንበሳ ብቻ ነው የሚያስፈልጋት እስካልተባለ ድረስ ታማኝም አንዳርጋቸውም ለሃገራችን አንበሶች ናቸውና ታማኝ ለምን ያንን አደረገ? ሲሉ ይጠይቃሉ። በርግጥ ለአቶ አንዳርጋቸው ያለህን ክብር ለመግለጽ የተጠቀምክበትን አገላለጽ ብዙዎች ወደውታል ። እስቲ ይህን ልትል ያስቻለህን .... ግለጽልን፡፡**

<u>ታማኝ፡-</u> ያንን ያልኩት በስሜታዊነት ወይም በግብታዊነት አይደለም። ከልቤ የተሰማኝንና የሚሰማኝን ነው የተናገርኩት። አንዳርጋቸው አንበሳውን ለኔ ሲሸልም ስለኔ የተናገረው ራሱ በጊዜውም ከብዶኛል። እኔ ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩልህ ራሴን የማየው እንደ አንድ ለህዝብ ነጻነትና ለሃገሩ ሰላም ፤ ....የሚናፍቅ ዜጋ ነው። አንዳርጋቸው በዚህ እድሜው ለህዝቡና ለሃገሩ ሲል የወሰደው እርምጃ በጣም ያስደንቀኛል። ሊከፍል የተዘጋጀው መስዋእትነት ሳያንስ እንደገና አፈናው ሲፈጸምበት አንበሳው የሚገባው ለሱ ነው የሚል ስሜት ፈጥሮብኛል። ይህ ደግሞ አሁንም እውነተኛ ስሜቴ ነው።

**<u>አሻራ፡-</u> አሁን ደግሞ ወደ አገር ቤት ልመልስህ፤ ገዢው ፓርቲ “ምርጫ መጣ ጥሬስ ውጣ!” የሚል መሪ ቃል የሚከተል እስኪመስል የነጻው ጥሬስ ጋዜጠኞችንና ጦማሪያንን የማጥፋት ዘመቻ ከፍቷል። ይህን ቃለ ምልልስ በምናደርግበት ሰሞን ብቻ 12 ጋዜጠኞች ሃገር ለቀው ወጥተዋል። ስድስት ጦማሪያንና ሶስት ጋዜጠኞችም ከታሰሩ 4 ወራት አልፏቸዋል። ይህን እና ሰላማዊ ትግሉን፤ አያይዘህም መጪውን ምርጫ በተመለከተ ያለህን አስተያየት ብትገልጽልን?**

<u>ታማኝ፡-</u> እነዚህ ሰዎች እኮ ማንም መንግስትን ተቃውሞ መተንፈስ የማይችልባት ሃገር ለመፍጠር እየሰሩ ነው ያሉት፡፡ እነኚህም ጋዜጠኞች የቻሉትን ሁሉ አድርገዋል፡፡ ከአቅም በላይ ሲሆንባቸው ደግሞ ምን ያድርጉ? ስደትን መርጠዋል፡፡ ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች የከፈሉት መሥዋዕትነት በኢትዮጵያ ታሪክ ግዙፍ ቦታ ይዞ እንደሚኖር ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ይህ ሲሆን ታዲያ እኛም በውጭ ያለን ኢትዮጵያዊያን እነኚህን ወገኖች አለንላችሁ ልንላቸው ይገባል፡፡

እነሱ (ገዢው ፓርቲ) በፍርሃት ዓለም ውስጥ ስለሆኑ ሁሉንም ነገር ለመቆጣጠር ነው ሩጫቸው፡፡ ወደፊት መቼም ቻይና የማትሰራው ነገር የለምና አገር ስትገባ ኤርፖርት ላይ ለመንግስት ክፉ -ልብ ያለውን ስካን የሚያደርግ መሳሪያ ሁሉ ሊያሰሩ ይችላሉ ....(ሳቅ)። ምርጫውንም ቢሆን ከዚህ በተለየ አይደለም የማየው። ፍርሃት ውስጥ ያለ አካል እውር ድንብሩን ብዙ ነገር ሊያደርግ ይችላል።

**<u>አሻራ፡-</u> አንዳንድ ሰዎች ታማኝ አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝን የራራላቸው ይመስላል። አቶ መለስን የተነፈሷትን ቃል ተከትሎ ወዲህ ወዲያ ያደርጋቸው እንዳልነበር ለአቶ ሃይለማሪያም ምነው ዝም አለ ይላሉ?**

<u>ታማኝ፡-</u> ሳቅ.....! ይህን የሚሉ ሰዎች እውነት ከልባቸው እኔ በአቶ ኃይለማሪያም ላይ ግዜ እንዳጠፋ ፈልገው ነው? አይመስለኝም፡፡ አቶ መለስ እኮ የራሳቸው ተረት ፤የራሳቸው ስድብ ፤የራሳቸው፤ ውሸት የራሳቸው ምናምን...የነበራቸው ሰው ነበሩ። አቶ ኃይለማሪያም ደግሞ ሳይዛቸው አልሆን ብሎ እንጂ የአቶ መለስን ልብስ ሊለብሱ የሚፈልጉ ነው የሚመስለኝ።

የአገር መሪዎች ከስራ ውጭ መጽሄት ማገለባበጥ፤ የአለም ዜና መከታተል .... እንዲህ እንዲህ አይነት ነገር እደሚያደርጉ ነው የማስበው፡፡ አቶ ኃይለማሪያም ግን ሌሊት ሁሉ ቁጭ ብለው የአቶ መለስን ቪዲዮ የሚያዩ ነው የሚመስለኝ፡፡ “ እስኪ የ 94ቱን አምጪልኝ የ93ቱን ጨርሻለሁ እያሉ...” እና በእኛህ ሰው ላይ ነው ግዜ እንዳጠፋ የሚፈለገው? ለሳቸው የሚሆን ግዜ እንኳ የለኝም፡፡ በቁምነገር ልወስዳቸው አለመፈለጌ እንጂ አቶ ኃይለማሪያም እንዴት ያለ ኮሜዲ ሊሰራባቸው የሚችሉ መሰሉህ?

አንተ ኮ! ስትኮርጅ የሰውን ሃሳብ፤ ወይም ሻል ያለ ነገር ትኮርጃለህ ።

[ወደ ገጽ 34 ዞሯል]

# ስለ ዞን ዘጠኝ ጦማሪያን ከዞን ዘጠኝ ጦማሪ

*(ከጀማኔህሰ ካሳዬ)*

**በመጀመሪያ፡** ሶሻል ሚዲያ ነበር። በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲወያዩ እና ሲታዘቡ የነበሩ ወጣቶች የሶሻል ሚዲያ ጓደኝነታቸው ተጠናክሮ ለተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች የሚያደርጉት እንቅስቃሴና የሚያስተላልፉት መልዕክት የጋራ መግባባት ቢፈጥርላቸውም መሬት ላይ አውርደው ተግባራዊ እንቅስቃሴ አለማድረጋቸው ያሳስባቸው ነበር። ሁሉም ስሞታዎች መንግስት ላይ ያነጣጠሩ ቢሆንም በአረብ አገር በስራ ላይ እያለች ወደ ኤምባሲ ስትሄድ እንግልት የደረሰባትና በመጨረሻም ለሕልፈት የተዳረገችው የአለም ደቻሳ ሞት ግን የብዙዎችን ልብ የነካ ነበር፡፡

ይሄን አሳዛኝ አደጋ ሰምተን ዝም ማለት የለብንም ያሉ ዜጎች በየፊናቸው የተለያዩ ጥሪዎችን ማድረግ ጀመሩ። በአገር ውስጥ ያሉት ወጣቶች በአንድ ተቀናጅተው የሻማ ማብራት ስነስርዓት እንዲሁም የገቢ ማሰባሰቢያ ሥራ ወደመስራትና ለአለም ደቻሳ ልጆች መቋቋሚያ የሚሆን ገንዘብ የማሰባሰብ ስራ ወደ መስራት ተገባ። በወቅቱ ቀና ትብብር ካደረጉልን መካከል ዛሬ ዞን ዘጠኝን ከሚወነጅሉት መሀል የሆነው አቶ ጌታቸው አሰፋ አንዱ ነበር፡፡

በፌስ ቡክ The Good Ethiopian (ደጉ ኢትዮጵያዊ) በሚል ባቋቋምነው ግሩፕ አማካይነት በዋቢ ሸበሌ ተሰናድቶ የነበረው ዝግጅትም ስኬታማ ሆኖ የተሰበሰበውን ብር ለቤተሰቦቿ አስረክበናል። ይህ ግሩፕ ከብዙ ሕልሙ ጥቂቱን ያሳካ ቢሆንም ዛሬም በፌስ ቡክ «ደጉ ኢትዮጵያዊ» በሚል ይገኛል፡፡

በዚህ ምግባረ ሰናይ ዝግጅት ላይ የተገኘን ልጆች ነን የታሰሩትን ወደመጠየቅና በመጨረሻም መብትና ያገባኛል የሚሉ ነገሮች ውስጥ የገባነው። መንግስት ጥርስ ውስጥ ያስገባናል ብለን ብናስብም፤ ... የቢጤዎቻችን መፍዘዝና ያገባኛል የሚል ትውልድ እየጠፋ መምጣት ቢከነክነን፤ በሙስና በዘረፋና በሌሎች ሕገወጥ ድርጊቶች የሚገኙ ቁሳዊ ድሎቶች

«ሕቡዕ» የሚል ታርጋም ሊለጠፍብን ተሞክሯል። ፎቶ ለጥፎና ስም ተገልጾ በሶሻል ሚዲያ እየታዩ ሕቡዕ ብሎ ነገር የለም። አልያም ሰዎቹ ለሶሻል ሚዲያ ያላቸው ግንዛቤ ደካማ ነው ማለት ነው፡፡

ማህበረሰብ ውስጥ የማያሳፍሩ እየመሰሉ መምጣታቸው ቢያንገበግበን፣ "ዜጋ እኮ አለፈለት፣ እንደሱ ጠጋ በል እንጂ . . ." የሚሉ አይነት አሳዛኝ ምክሮች መሰማት መጀመራቸው ቢቆረቁረን፣ አንዳች ነገር ማድረግ እንዳለብን አመንን።

ህልማችን መብትና ግዴታውን የሚያውቅ ዜጋ ሲበራከት ማየት ሆነ ።በስድብና ብሽሽቅ ጊዜውን የሚያሳልፈው የሶሻል ሚዲያ ወጣት ወደስልጡን ውይይት ሲሸጋገር ለማየትም ጓጓን። እናም ህልማችን ዕውን ይሆን ዘንድ የአቅማችንን ለመፍጨርጨር ወሰንን። በአንዱ ዕለት ከቃሊቲ መልስ መንገዳችን ተጠረገ። ዞን ዘጠኝን መሰረትን፡፡

**የሰብዓዊ መብት ተቋማትና ዞን 9**

ይህ ሁሉ ሲሆን ዞን ዘጠኝና አርቲክል 19 አይተዋወቁም ነበር፡፡ ስለዚህ በኛ አመሰራረት ላይ የእኛ የዘጠኞች በጎ ፈቃደኝነት እንጂ የማንም እጅ አልነበረበትም፡፡ ሁኔታውን ከአጀማመራችን ጀምሮ የሚያውቁት ቢኖሩም መንግስት የሚሳሳት የማይመስላቸውና በምንም አቅጣጫ ወገንተኝነታቸውን ማሳየት ያለባቸው ወገኖች ጥረታችንን እንደማይወዱልን አልጠፋንም። የፓርቲ አባላትም አመለካከ ታቸውን በፖለቲካዊ ውሳኔ ስር ቃኝተው እንደሚያዩን ጠብቀናል። የፕሮፓጋንዳ ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችንን ግን እውነታውን እንዲያውቁት ለማድረግ መጣሩ ግዴታችን ሆነ፡፡

በሕገ-ወጥ መንገድ መደራጀት (እኛ ተሰባሰብን እንጂ አልተደራጀንም) የምትለዋ ውንጀላ ሕገ-ወጥ የሚለውን ቃል እንደስም ማጥፊያና ለማሸማቀቂያነት የሕግ ድጋፍ ያለው ለማስመሰል የገባች እንጂ ሕገ-ወጥ ሆነን አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ በኢንተርኔት የሚደረግ መሰባሰብን በሕግ ለመቆጣጠር በመንግስት ደረጃ ገና እየታሰበበት ያለ ነገር ነው፡፡

«ሕቡዕ» የሚል ታርጋም ሊለጠፍብን ተሞክሯል። ፎቶ ለጥፎና ስም ተገልጾ በሶሻል ሚዲያ እየታዩ ሕቡዕ ብሎ ነገር የለም። አልያም ሰዎቹ ለሶሻል ሚዲያ ያላቸው ግንዛቤ ደካማ ነው ማለት ነው ::

በዚህ ወቅት በማዕከላዊ እንግልት እየደረሰበት ካለ አንዱ ዘጠነኛ ጋር ሃሳብን በነጻነት መግለጽ ዙሪያ ላይ የኢንተርኔትና የሶሻል ሚዲያውን በተመለከተ የሚቆጣ ጠሩበት የሕግ ማዕቀፍ ጥናት ላይ እንደሆኑ አቶ ሽመልስ ከማል የገለጹት እንዲህ በቅርቡ ነበር። ይህ ከሆነ ዘንዳ ዞን ዘጠኝ ባልጸደቀ ህግ ሰለባ ሆኗል ማለት ነው። ኢህአዲግም የተደራጀ የመሰለውን ነገር ሁሉ በእርሱ አምሳያ መቅረጽ ካልሆነም የማፍረስና የማዳከም ሱስ ተጠናውቶታልና ብዕር

*ወደ ገጽ 26 ዞሯል*

## ወ/ሮ ሉሊት መስፍን

ላለፉት አሥር አመታት የማውቀው አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፡- አንደበት ጨዋ፤ በጣም ብልህ፤ አርቆ አስተዋይ፤የሚሰራውን የሚያውቅ፤ በዓላማው ሁልጊዜም የሚጸና፤ መንፈሰ ጠንካራና አገሩን የሚወድ ቆራጥ ኢትዮጵያዊ ነው።

ውድ አገራችን ኢትዮጵያን ከወያኔ ፋሽስት አገዛዝና የጥፋት አላማ አራማጆች ነጻ ለማውጣት የጀመርነውን ትግል ሳንጨርስ፤ ጀግናው ወንድሜ በባንዳ ወሮበሎችና ነፍሰ ገዳዮች እጅ በመውደቁ በጣም ባዝንም፤ ሕይወቱን ሁሉ የሰዋለትንና የቆመለትን የትግል ዓላማ በመከተል የጀመርነውን ለመጨረስ፤ ብሎም ኢትዮጵያን ከወያኔ ነጻ ለማውጣት የማደርገውን ጥረት በአሥር እጥፍ እንዳጠናክረው ያበረታታኛል።

የአንዳርጋቸው መሰዋዕትነት በምንም ተዓምር ከንቱ እንደማይቀር ወያኔና ግብረ አበሮቹ ለአንዲት ደቂቃ እንኳ እንዳይዘነጉት እላለሁ።

ኢትዮጵያዊ መሆኔ ሳይነቃ አልቀረምና ተዘጋሁ። ዶ/ር ብሪ በጣም ቀላ ስለሚል የአረብ ቱጃር መስሏቸው ነው መሰለኝ ዕድል ሲሰጡት፣ በሚያስገርም ሁኔታ ሰውዬው የካበውን ሁሉ በመረጃ በተደገፈ አስተያየት ደርምሶበት አረፈው። ያንን ውርጂብኝ መካድ ስለማይቻል "የራስህን ሀሳብ የመግለጽ መብት አለህ" ተብሎ ሊታለፍ ተሞከረ። አንዳርጋቸው ለመጀመሪያ ጊዜ እጁን አወጣ። አንዳርጋቸው ሲመቸው በኢትዮጵያዊን ካልሆነ በስተቀር በእይታ የትውልድ ሃገሩን ለመለየት አስቸጋሪ ነው። ናይጄሪያዊ ቱጃር ሳይመስለው አልቀረም። ዕድሉን ሰጠው! በቀጥታ እንግሊዞቹ ላይ ነበር አንዳርጋቸው ያነጣጠረው። "እናንተ ብርቲሾች ስትባሉ፣ ሁለት ዓይነት ዲሞክራሲ ነው ያላችሁ። አንዱ ለዜጎቻችሁ ያለገደብ የሚሰጥ ነው። ሌላው በማንኪያ እየተጨለፈ ለታዳጊ አገሮች የሚሰጥ! እንደ ኢሕአዴግ ያለውን አሻንጉሊታችሁንማ፣ ነፍሰ-ገዳዮች መሆናቸውን እያወቃችሁ፣ ዜጎቻቸው ላይ የሚያደርሱት ግፍ፣ ጭፍጨፋ፣ በደልና ፍጅት፣ በተባዮች ላይ የሚፈጽሙት እንጂ በሰው ላይ የሚደርስ ስቃይ መስሎ አይታያችሁም። እኛም ኢትዮጵያውያን እኮ እንደ ብርቲሽ ዜጎች ዲሞክራሲ ይርበናል፣ ፍትህ ይጠማናል፣ እኩልነት ይናፍቀናል። ገዳዩን፣ ወንጀለኛውን፣ አገር አጥፊውን ጉልበተኛ ገዥ እንዲህ አሰማምረው ሲያቀርቡት ትንሽ እንኳን አይሰቀጥጥዎትም?" ሲል ቤቱ ተረበሸ! ሰብሳቢውም ባለሥልጣን ዕቅዱ ሁሉ እንደተኮላሸበት ሲረዳ፣ "ሌላ ስብሰባ አለብኝ" ብሎ ተሰብሳቢውን ጥሎ ውልቅ አለ። ሶስታችን ከፍሉን ተቆጣጠርን። ተሰብሳቢው የበለጠ ዕውነተኛ ማስረጃ ለማግኘት ሶስታችንን ከበበን። የሚያስፈልገውን ማስረጃ ሁሉ ሰጥተን አድራሻ ተቀያይረን እየሳቅን ወጣን። ከዚያች ዕለት

በዚህ ዓምድ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በሥራና በተለያየ አጋጣሚ በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች

# አንዳርጋቸው በኔ

ስለ ማንነታቸው የሰጡት የግል አስተያየት ተስተናግዶበታል።

## ስለ አንዳርጋቸው ከትዝታዎቼ አንዱ

**ዶክተር ወንድሙ(ለንደን)**

አንድ የወያኔ ወዳጅ የብሪቲሽ የፓርላማ አባልና የመንግሥት ባለሥልጣን ወያኔን ለመርዳት በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2005 ዓ.ም ላይ "ለኢንቨስተሮች" እዚያው ፓርላም ውስጥ የምሽት ስብሰባ በምስጢር አዘጋጀ። አንድ ወንድም ሚስጢራቸውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የግብዣ ወርቀትም ማግኘት ቻለ። ያንን የግብዣ ወረቀት "ከእኔ ይልቅ አንተ ብትገባበት ይሻላል" ብሎ ድምጼን አጥፍቼ እንድገባ መከሮ ሰጠኝ። እንዳለውም ተሽሎክልኬ ስገባ፣ አንዳርጋቸውና ዶር ብሪም በዚያው መንገድ ገብተው አገኘኋቸው። ተመሰጣጥረን ተቀመጥን። አልተመካከርንም። ዕድሉን እናገኝ እንጂ፣ ሶስታችንም የአገራችንን ጉዳይ ለመናገር ብቁ ዕውቀት ነበረን።

ያ ባለሥልጣን ለነዚያ "ኢንቨስተሮች" ና በወረንጦ ተለቅመው ለተጋበዙት ታዳሚዎች ፤ወያኔ የሚያስተዳድራት ኢትዮጵያ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ገነት እንደሆነች፣ ዲሞክራሲ በአገሪቱ እንዳበበ፣ ልማት በየቦታው እንደተተከለ፣ ረሀብ ኢትዮጵያ ውስጥ ጨርሶ ጠፍቶ ለታሪክ ምዝገባ ብቻ እንደበቃ ... የወያኔን አስቀያሚ ገጽ "በሜክ-አፕ" ቀባብቶ ያለ ምንም ሀፍረት አቀረበው። በንግግሩ መጨረሻ ላይ ለጥያቄ መድረክ ተከፈተ። ኢንቨስተር ሁሉ በጉጉት ጥያቄውን አዥጎደጎደ። መልስ ተሰጠ። እኔ እጄን ባወጣ፣ ባወጣ ሰርጎ-ገብ ጀምሮ ነፍሴ ከአንዳርጋቸው ጋር ቶቆራኘች! ከዚያ በኋላ የትግል ጓዶች ሆንን። አብረን ብዙ ብዙ ቁም-ነገሮችን ሠርተናል። ብዙ ሰላማዊ ሰልፎችን፣ ሀገራዊ ስብሰባዎችን ተካፍለናል። እሱ ቅንጅቶችን ለመርዳት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከቅንጅት ባለሥልጣኖች ጋር ሲታሠር በለንደን የተቃውሞ ረሀብ-አድማ ከመቱት መሀል አንዱ ነኝ። ዛሬም ወንድሜ ጠላቶቹ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ እጃቸው ሲያስገቡት፣ ከእጃቸው ፈልቅቀን እስክምናወጣው ድረስ ከሚታገሉት መሀል አንዱ በመሆኔ ታድያለሁ። እኔም አንዳርጋቸው ነኝ!

## እንደልቡ (ዳግም)-ቫንኮቨር ካናዳ

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ያለምንም ማወላወል ላመነበት ዓላማ ሁለንተናውን ከመስጠት ወደኋላ የማይል ቆራጥ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ማንም ይገነዘባል ብዬ አስባለሁ። እንዲህ አይነቱ ብርቅዬ ኢትዮጵያዊ በነዚያ ውርጋጦችና ዘረኞች እጅ መውድቁ እጅግ የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ነው።

ይሁንና ኢትዮጵያውያን አንዳርጋቸው ጽጌ በወያኔዎች እጅ መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ እያሳዩ ያሉት ቁጭትና አንዳርጋቸው የቆመለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያላቸውን ተነሳሽነት ስመለከት ከፍተኛ ደስታ እየተሰማኝ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። "ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም" እንደተባለው።

አዎ አቶ አንዳርጋቸው የተከተለውን መንገድ ጠበቅ አድርገን እንያዝ! ህዝባችንን፣ ታሪካችንን እና ሃገራችንን ለማጥፋት ሌትተቀን ለሚባዝኑ

ወደ ገጽ 31 ዞሯል

# ኮሜዲያን ክበበው ገዳ

ክበበው ገዳ በሙያቸው ከፍተኛ ተቀባይነትን ለማግኘት ከበቁ ጥቂት የአገራችን ኮሜዲያን አንዱ ነው። ላለፉት ዓመታት በርካታ ኢትዮጵያዊያን በሚገኙባቸው የተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች እየተዘዋወረ ስራዎቹን ሲያቀርብ ቆይቷል። በተለይም በዚህ ወር በዩናይትድ ስቴትስ የተለያዩ ግዛቶች እያቀረባቸው ያሉት ስራዎቹ በስፋት ማነጋገር ችለዋል። በማህበረሰቡ ውስጥ ሲብላሉ የቆዩትንና አብዛኞቹ የወቅቱ አርቲስቶቻችን ግን በይፋ ለማስተጋባት ያልደፈሯቸውን መሪር ዕውነቶች በቀልድ እያዋዛ ማቅረብ መጀመሩ ለአርያነት የሚያበቃው ነው። ለመሆኑ ይህን መሰል የማህበረሰቡን ቁጭቶችና የአገዛዙን ህጸጾች የሚነካኩ ስራዎች ለማቅረብ ምን አነሳሳው? የህዝቡስ ምላሽ እንዴት ነበር? ወደፊትስ በመሰል ስራዎቹ ይቀጥልባቸው ይሆን? የሚሉና ሌሎችም ጥያቄዎች አቅርበንለታል። ክበበውን ያነጋገረው ተባባሪያችን ጋዜጠኛ አትክልት አሰፋ ነው። ተከታተሉት።

**አሻራ** - ክበበው መጀመሪያ አካባቢ ከቡዙህ ጋር አሁን አሁን ደግሞ ከመስከረም ጋር ከመስራትህ ውጪ ባብዛኛው የግል ስራዎችህን ነበር የምታቀርበው። በግል ካቀረብካቸው በርካታ ስራዎችህ መሀል የተለያዩ ቋንቋዎች ተጻእኖ ያለባቸውን ባህሪያት እየፈጠርክ የሰራህቸው ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ ገ/መድህንና ሽምሱ። እስቲ በገ/መድህን እንጀምር? በህይወት ያለ ሰው ነው?

**ክበበው** - ገ/መድህንን የሰራሁት በገዛ አባቴ ባህሪ ላይ ተመርኩዤ ነው። አባቴ በጣም ከገ/መድህን ጋር የሚመሳሰል ባህሪ ነበረው። ሊያስታርቅ ሄዶ ሙልጭ አድርጎ ተሳድቦ የሚመጣ ዓይነት ሰው ነው። ባልና ሚስት ሊያስታርቅ ሄዶ የገዛ ሚስቱን "የኔዋም አስቸግራኛለች። ምን እነዚህ ምንም አይረቡም!" የሚል ዐይነት ነው። እኔ ገ/መድህንን ስሰራው ይህን የአባቴን ባህሪ ተንተርሼ ነበር። በኋላ ግን ብዙ ትርጉም አመጣ። የተለያዩ ሰዎች "ለምን እንዲህ ትሰራለህ? ይሄ ችግር ሊያመጣብህ ይችላል።" ሁሉ አሉኝ።

እንዴ...!? እኔ እኮ ገጸ ባህሪ ፈጥሬ ነው የሰራሁት። ገ/መድህን የትግራይን ህዝብ በሙሉ ወይም ገዢውን መደብ ሊወክል አይችልም። ደግሞስ ማግለልና አድሎ የሚባል ነገር አለ አይደል? የጉራጌውንና የአማራውን ሰርቼ ይህን ግን አትስራ ካሉ ለነሱም ማግለል ነው የሚሆንባቸው። ስለዚህ እንዳይገለሉና ወቀሳ እንዳይበዛባቸው ለነሱም ቢሆን መስራቴ ጥሩ ነው የሚሆንላቸው። በዚያ ላይ እንደፈለክ መናገርና መጻፍ ትችላለህ የሚል ህግ አለ። እኔም በዚያ መሰረት ሰርቼዋለሁ። የደረሰብኝም ነገር የለም። ግን ያው አለ አይደል? ሁሉም ሊደሰት አይችልም።

**አሻራ** - የሽምሱስ ጉዳይ? ምን ያህል ትናፍቀዋለህ?

**ክበበው** - ሽምሱ በጣም የሚናፍቅ ሰው ነው። እንደውም እኔኑ በልጦኛል ማለት ይቻላል። ሰዉ ሲያገኘኝ ከክበበው ይልቅ ሽምሱ ነው የሚለኝ። ይሄ ምን ያህል ሰው ስሜት ውስጥ እንደገባ ነው የሚያሳየው። ሽምሱ በየሰፈሩ ያለ ሰው ነው። አሁን ግን ባለሱቅ ብቻ ሆኖ እንዲቀር አልፈለኩም። አስተምሬው፣ ድርጅቱን አሳድጎ ሱፐር ማርኬት እንዲያደርገው ወይ ኢንዱስትሪ ነገር ከፍቶ እንግሊዘኛ እየቀላቀለ እንዲያወራ እፈልጋለሁ። ወይም አሜሪካ ይምጣና ሽምሱን በአሜሪካ ማሳየት አስባለሁ።

**አሻራ** - ግን እኮ ሽምሱ የሰፈርህ ሰው ነው ይባላል። ዕውነት ከሆነ በቅርቡ ልታገኘው የሞከርክበት ሁኔታ አለ?

**ክበበው** - ሰፈሬ ሽምሱ የሚባል ባለ ሱቅ ነበር። ዋና ባህሪ አድርጌ የወሰድኩት እሱን ነበር። ግን በጣም የሚገርምህ ሰካራም ሆነና መጨረሻ ወደ አገሩ ገባ። አሁን ሱቅ ውስጥ ያለው ወንድምዬው ነው። ወንድምዬው ግን የሽምሱ ተቃራኒ፣ ዝግት ያለ ኮስታራ ሰው ነው። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር ይባል የለ? ሽምሱ አሁን

[ወደ ገጽ 27 ዞሯል]

## የመጽሃፍ ቅኝት

**የመጽሃፉ ርዕስ** - የመለስ ትሩፋቶች
**ንዑስ ርዕስ** - ባለቤት አልባ ከተማ
**ደራሲ** - ኤርምያስ ለገሰ
**ቅኝት አቅራቢ** - ሳምሶን አስፋው

### "ዛሬ ማታ ኃይለማሪያም ቁንጥጫ አለበት'

ከላይ በርዕሰነት የተቀመጠቸውን አርፍተ ነገር የተናገራት አንድ ወዳጄ ነው። ፈገግ አስኝታኛለች። አንባቢንም እንደኔ ፈገግ የምታስብል ከሆነ በቅኝቴ መግቢያ ላይ ጣል አድርጊያት ማለፈ ወደድኩ።

ሁነቱ እንዲህ ነው፡- የአቶ ኤርምያስን መጽሃፍ ያነበብኩት በወጣበት ሳምንት ውስጥ ቢሆንም ይህን ቅኝት የማቅረብ ሃሳብ ብቅ ያለው ግን ይህች መጽሄት በተጸነሰችበት ማግስት ነው። ቅኝቱን ለማቅረብ ወስኜ በጅምር ላይ እያለሁ፤ የአቶ ኤርሚያስ መጽሃፍ ምረቃ ቪዲዮ ክሊፕ ተለቀቀ። በዝግጅቱ ላይ ከአራት ያላነሱ የኢሳት ጋዜጠኞች በመጽሃፉ ላይ ያላቸውን አስተያየት እንደሚያቀርቡ ቀደም ብሎ ተገልጾ ነበርና የምረቃውን ቪዲዮ ማየት እንደሌለብኝ ወሰኜ (ቅኝቴ ላይ ተጽዕኖ እንዳይኖረው) በራሴ ስራ ላይ አተኮርኩ።

ይሁንና "በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል?" እንዲሉ፡- አንድ ወዳጄ ደወለና "የኤርምያስን የመጽሃፍ ምረቃ አየኸው?" ሲል ጠየቀኝ። እንዳላየሁትና የራሴን ስራ ሳልጨርስ እንደማላየው ነግሬው፤ በዚያ ዙሪያ እንዳናወራ ተከላከልኩ። ወዳጄ ግን የሚያርፍ አልሆነም። ቀጠለ፡- "አይ ባንተ ቅኝት ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ የማይችል ነገር ላይ ማውራት እንችላለን" አለኝ፡፡ እኔም አሁንም ላለማውራት በመከላከል፡- ዝግጅቱ የመጽሃፍ ምረቃ ስለሆነ ሁሉም ሊያወራ የሚችለው ስለ መጽሃፉ ይዘት ስለሚሆን ይቅርብኝ አልኩ። ወዳጄ ግን ሃሳቤን ሊቀበለው አልፈለገምና ቀጠለ፡- "ኤርምያስ ስለ ኃይለማሪያም የተናገረውን ጉድ እኮ ነው የምልህ !" አለና አጓጓኝ!፡፡ አይ!... ይሄ ከመጽሃፉ ጋር ግንኙነት ሊኖረው አይችልም! በሚል ስሜት ሳላውቀው ምን አለ ? ስል ጠየቅኩ ። ወዳጄም ቀጠለ- " በኢንፎርማል ስብሰባ (በሃሜት) ኢትዮጵያ ውስጥ በሙስና ጨረታ እንዲያሸንፍ የተደረገ የቻይና ካምፓኒ የአርከበንና የስብሃት ነጋን ልጆች ቻይና ወስዶ እያስተማራቸው እንደሆነ ለኔና ለሬደዋን የነገረን ኃይለማሪያም ነው ብሎ ኢጋለጠው" አለኝ። ወዲያው አስከትሎም "ዛሬ ማታ ኃይለማሪያም ቁንጥጫ አለበት!" ብሎ አሳቀኝ። የአርከበ ረዥም እጆች በኃይለማሪያም ጭኖች መሃል .... እየታዩኝ ከልቤ ሳቅኩ። ሳይወጣ የወረደ ጠ/ሚር ...!




**<u>ወደ ቅኝቴ ልመለስ፡-</u>**

"የመለስ ትሩፋቶች" በ8 ዋና ክፍሎችና በ23 ምዕራፎች ተሸንሽኖ፤ በ406 ገጾች ተከሽኖ፤ በትረካና በአስረጂነት የቀረበ መጽሃፍ ነው።

በመጽሃፉ የፊት ሽፋን ላይ የዋና ባለታሪኩ (ጠ/ሚሩ) ደብዛዛ ምስል በራስጌ ፤ በመጽሃፉ ንዑስ ርዕስ "ባለቤት አልባ" የተሰኘቺው የአዲስ አበባ ከተማ ከርቀት የተነሳ ፎቶ በግርጌ ለአይን በሚስብ መልክ ተቀናጅቶ ይታያል። የሽፋን ገጹ ከመጽሃፉ ዋናና ንኡስ ርዕስ ጋር ሲዳበል የሚሰጠው ትርጉም የመጽሃፉን የውስጥ ይዘት በጉልህ የሚጠቁም ነው። አዲስ አበባን ባለቤት አልባ በማድረጉ ዘመቻ ፊታውራሪው ጠ/ሚሩ ናቸው የሚል ። ርዕሱንም ምስሉንም ወድጀለታለሁ።

ስለ ውጫዊው ገጽታ ይህን ያህል ካልኩ ይበቃል ። ወደ ውስጥ ልዝለቅ፡-

**<u>የታሪኩ አወቃቀርና ፍሰት ፡-</u>**

በ8 ዋና ክፍሎችና በ23 ምዕራፎች የተከፈለው መጽሃፍ በዋናነት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በገነገው ፓርቲ ድርጅታዊና መንግስታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረ

ሆኖ፡- በውስጡም የ3 ምርጫዎችን ሂደት (ምርጫ 92 ፤ ምርጫ 97ና ምርጫ 2002) በተለያዩ ክፍሎች አሰላስሎ ያቀርብልናል። ከምርጫ ሂደቶች ወጣ ብሎም "የጥፋቱ ቅብብሎሽ ከመመሪያ አንድ እስከ ሁለት" በሚል ክፍል የአዲስ አበባን የመሬት ቅርምት ያስቃኘናል። በተጓዳኝም ለመጽሃፉ ተነባቢነትና የታሪክ ፍሰት አይነተኛ ሚና የተጫወቱ ክስተቶችን ፤ ገጠመኞችን የተለያዩ ባለስልጣናትንና ግለሰቦችን አሳዛኝ፤አስቂኝና አስገራሚ ስብዕና እያዋዛ ያስኮመኩመናል።

ባጠቃላይ ደራሲው ኤርምያስ ይዞት የተነሳውን ርዕስ ሳይለቅ፤ በንዑስ ርዕሱ እንደጠቆመን በአንድ በአዲስ አበባ ዙሪያ ከትሞ፤ በ3 ምርጫዎች ሂደት ከርሞ ፤ የታሪኩ ቅደም ተከተል እንዳይዛነፍ በ8 ክፍሎች ከሸኖና በ23 ምዕራፋት ሰንሰለትነት ከጅምር እስከ ቁጭት የተጓዘበት አካሄድ እጅግ የተዋጣለት ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

## ተነባቢነት

አቶ ኤርምያስ "የመለስ ትሩፋቶች" በሚል ለንባብ ያቀረበልን መጽሃፍ ፤ ገዢው ፓርቲ የሃገሪቷን ዋና መዲና "ባለቤት አልባ" ያደረገበትን የተጠና የጥፋት ዚቅ ነው። ኤርምያስ በጥናት የተመራውን ጥፋት የሚተርክልን በቅርብ ርቀት ላይ ሆኖ ነው።

በዋናው ፊታውራሪ የተነደፈውን ጥፋት ከሚያስፈጽሙት ግራና ቀኝ አዝማቾች አንዱ እንደነበር አልደበቀንም:: "ማን ይናገር የነበረ.." እንዲሉ ሁሌም እኔ ....አደረኩ፤ እኛ ...አደረግን። በሚል ማሰሪያ የሚቋጭ ትረካ የተደራሲን ቀልብ ይስባል። በመሆኑም ደራሲው በታሪኩ ውስጥ እንደ ባለታሪክ የተቀመጠበት ወንበር ለዙፋኑ ቅርብ መሆኑ የመጽሃፉን ተነባቢነት አጉሎቶታል።

የደራሲው ጆሮ ለዙፋኑ አንደበት ቅርብ መሆኑ ደግሞ የአንባቢውንም ጆሮ ለደራሲው አንደበት ቅርብ አድርጎታል። በመጽሃፉ ውስጥ ተንሰላስለው የተተረኩት ኩነቶች በአብዛኛው ደራሲው በቅርብ ርቀት የተከታተላቸው ወይም የተሳተፈባቸው ናቸው። እራሱ ያለተሳተፈባቸውንም ቢሆን የሚያቀብለን ቢያንስ ቢያንስ በቅርብ ርቀት ከተሳተፉ ሰዎች አፍ ተቀብሎ ነው::

በስሚ ስሚ ... አይነት ትረካ ከክስተቱ ብዙ እንድንርቅ አላደረገም ። ይህም ተነባቢነቱን አግዝፎታል።

## የትረካ ስልት

ኤርምያስ በገዢው ፓርቲ ውስጥ የነበረው የስልጣን እርከን ለታሪኩ ተነባቢነት ጉልህ ሚና እንደተጫወተ ግልጽ ነው። እንደኔ ምልከታ ግን የመጽሃፉ ትልቁና ጠንካራ ጎን፤ ለማንበብ ጓጉቶ መጽሃፉን አንድ ብሎ የሚገልጠውን አንባቢ ሳይሰለች ከገጽ ገጽ ልብ-አያንጠለጠለ ማስጓዝ መቻሉ ነው። ከዙፋኑ በቅርብ ርቀት የኖረ ሰው መሆኑ የመጽሃፉን ተነባቢነት ማግዘፍ እንጂ መጽሃፉን ለማንበብ ጓጉቶ የገለጠ ሁሉ እስከ መጨረሻው በንባብ ስለመዝለቁ ዋስትና አይሰጥም። የደራሲው ወንበር ምንም ያህል ግዙፍ ይሁን የታሪኩ አፈሳሰስ የአንባቢን ቀልብ መያዝ እስካልቻለ መጽሃፉም ብዙ ጀማሪ እንጂ ብዙ ጨራሽ አይኖረውም። "የመለስ ትሩፋቶች"ን ግን ከጀመሩት ሳይጨርሱት የሚያስቀምጡት አይደለም።

ለዚህ ትልቁ ምክንያት ደግሞ የትረካው ስልት ነው። ደራሲው ቀላልና የልተወሳሰበበ ቋንቋ በመጠቀም አጠገባችን ሆኖ የሚነግረን ያህል እንዲሰማን ማድረግ ችሏል።

...ታሪኩ እንዲህ ነበር
.....እንዲህ ነበር የሆነው...
.... ሌላ ወግ ልጨምርላችሁ.....
..... እንዲህ ነበር ያደረጉት.....

እነኚህን መሰል ቃሎች የወግ ጥረቃው መከፈቻ በማድረግ የአንባቢን ቀልብ ይስባል። ..ታሪኩ እንዲህ ነበር ..ሲለን ድምጹ ይሰማናል። ሳይታወቀን ጆሯችን አንዳች አዲስ ነገር ለመስማት እንደ ጥንቸል ይቆማል። በጉጉት። አይናችን በብርሃን ፍጥነት ወደ ተከታይ ሀረጎች ይወረወራል። በአራት ነጥብ እስኪያስቆመን እንቀጥላለን...። እሱም ይቀጥላል ...ደግሞ ሌላ ... ከገጽ ገጽ እንጓዛለን።

የሚገርመው ደግሞ በሱ ደረጃ የነበረ ባለስልጣን እንዲህ እንደሱ የሆድ የሆዱን አውርቶልን ስለማያውቅ ይመስለኛል የሚነግረን ሁሉ አዲስ ነገር ነው። ቢያንስ ለኔ አዲስ ሆኖብኛል። (መጽሃፉ ምን አዲስ ነገር ይዟል? የሚለው ራሱን የቻለ የመመዘኛ ጥያቄ ስለሆነ ወደ ኋላ እመለስበታለሁ)

ኤርምያስ የተጠቀመው እንደወረደ የንግግር ቋንቋ ነው። ያልተንዛዛ አጭር አረፍተ ነገር ... ። ይህን መሰል ታሪክ በዚህ መሰል የንግግር ቋንቋ ሲገለጽ ታሪኩን ሰው ሰው ያሸተዋል። ሲሆን፤ነገር ግን ፤ ቢሆንም፤ የሆነው ሆኖ፤ አይነት አያያዥ ቃሎች በተደጋጋሚ መጠቀምና ረዥም አረፍተ ነገር መዘርጋት አንባቢን ያሰለቻል። ጭብጥም ሊያስትና ሊያወሳስብ ይችላል። ይህ ችግር በኤርምያስ ስራ ውስጥ አልተከሰተም።

ኤርምያስ የገዢው ፓርቲ ከፍተኛ ካድሬ እንደመሆኑ በበኩሌ በታሪኩ ውስጥም ከስብሰባ ስብሰባ እያጓጓዘ ሊያደክመን እንደሚችል ገምቼ ነበር። መጽሃፉ የኢህ አዴግ ካድሬዎች ቢኢቲቪና በኢትዮጵያ ሬዲዮ እንደፈንዲሻ የሚንጣጧቸው አስልቺ ኢህአዴግ ፈጠር ቃሎች ሊታጨቁበት እንደሚችሉም ጠብቄ ነበር። ኤርምያስ ሁለቱንም አላደረገም። ከካድሬነቱ ይልቅ ድንቅ ወግ ጠራቂነቱ ጐልቷል።

ኤርምያስ የታሪኩ አካል የሆኑ አስቂኝ ገጠመኞችን ጣል ጣል እያደረገ ቁምነገርን እያዋዛ በማቅረብ ረገድም ተዋጥቶለታል።

በገጽ 151 "ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም" ብሎ በቋጠራት ርዕስ ያስነበበን ቀልድ ከልብ ታስቃለች። ቀልዱ ጨነቀ በተባለው ካድሬ ላይ የተሰነዘረች ትሁን እንጂ በመንግስትነት የተቀመጡትን ሰዎች ማንነትም ፍንትው አድርጋ የምታሳይ ነች።

እኔም የኤርምያስን የትረካ ስልት ልዋስና ነገሩ እንዲህ ነው፡- ብዬ ቀልዱን በራሴ አገላለጽ ላቋድሳችሁ።ነገሩ እንዲህ ነው፡-

ቀደም ሲል የኢህአዴግ አባል ዋና መመዘኛ ለድርጅቱ ያለው/ላት ታማኝነት እንጂ ችሎታ ወይም ትምህርት አልነበረምና ጨነቀ የተባለው ካድሬ በታማኝነቱ ብቻ ከፍተኛ ስልጣን ይዞ በፈላጭ ቆራጭነት ቆየ። ከዕለታት አንድ ቀን ኢህአዴግ ሆዬ ድንገት ተነሳና ዋና መመዘኛው ችሎታና ትምህርት ይሁን አለ።ሆነም። የስልጣን ድልድሉና ምደባውም በችሎታና በትምህርት ሆነ። ጨነቀም ከነበረበት የስልጣን ጣራ ተሸቆልቁሎ ወርዶ ተራ ሰው ይሆን ዘንድ ግድ አለ። ያንን ያስተዋለ ሌላው ካድሬ ትምህርቱን የሙጥኝ ብሎ ቀጠለ።

ኢህአዴግ ደግሞ እንዲሁ ከእለታት አንድ ቀን እንደልማዱ ተነስቶ "ሁሉም ካድሬ ትምህርት ቤት በመግባቱ ስራ ተበድሏልና ትምህርት አቁሙ!" አለ። በዚህ ጊዜ ነበር እንግዲህ አንዱ ካድሬ "ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም" በማለት ትምህርት ማቋረጥ እንደማይበጅ የገለጸው።

ሌላው በኤርምያስ መጽሃፍ ውስጥ ያየሁት የተለየ ስልት፡- ከታሪኩ በተጓዳኝ "የሁለት ምርጫዎች ወግ" የሚለውን የአቶ በረከትን

ወደ ገጽ 38 ዞሯል

# የመጽሃፍ ቅኝት .....

*ከገጽ 39 የዞረ*

**<u>በመጽሃፉ ላይ የታዩ እንከኖች፡-</u>**

በለቀማ ስራ ላይ ሳይታዩ ከተዘለሉ የፊደል ግድፈቶች በስተቀር ይህን መጽሃፍ እንደ ምርጫ 97 "እንከን አልባ" መጽሃፍ ብዬ ባልፈው ደስ ይለኛል።

**<u>ላላነበቡት እንደ ምክር</u>**

ቅኝቴን የምቋጨው ይህን መጽሃፍ ላላነበባችሁ ወገኖች ምክር ቢጤ ጣል በማድረግ ነው። ምክሬ ደግሞ በተለይ የወያኔ መንግስትን ሃገር የማጥፋትና ሕዝብን የመበተን ተልእኮ እናውቃለን! ስለምናውቅም እንታገላለን! ለምትሉንና በተለያየ ምክንያት ይህን መጽሃፍ ላላነበባችሁ ወገኖች ነው።

እውነት! እውነት! እላችኋለሁ ይህን መጽሃፍ ስታነቡ እየታገላችሁት ስላለው መንግስት ከምታውቁት የማታውቁት እንደሚበልጥ ትረዳላችሁ። በርግጥ ለዘመናት የዘለቀውን የአገዛዙ ጥፋትና ግፍ ዓለም ያወቀው ጸሃይ የሞቀው ነው። የመለስ ትሩፋቶች ደግሞ ይህ አለም ያወቀው ግፍና በደል እንዴት ለምንና በማን እንደተቀመረ ከነቀመሩ ያስረዳል። ሳትውሉ ሳታድሩ አንብቡት።

ከገጽ ወደ ገጽ ስትጓዙ ቁጭታችሁም በዛው ፍጥነት በደም ስሮቻችሁ ዋሻ ሲሸሎኮሎክ ይታወቃችኋል። ህዝባችን በተምች ተወርሮ ሲሰቃይ ይታያችኋል።

ሌላው ቀርቶ መዲናችን አዲስ አበባ እንደሰው ታሳዝናችኋለች። ባጠቃላይ ወያኔ ማለት.....! ..... ነው። ብላችሁ ድምዳሜ ላይ ለመድረስ እንኳ የእኩይነት ተምሳል ታጡለታላችሁ። ዛሬ አንድ ነገር ማድረግ ካልተቻለ ነገ ራሱ አለመኖሩም ይታያችኋል። ለማንኛውም አንብቡት።

ደራሲው አቶ ኤርምያስ ጊዜውን ወስዶ ይህን መሰል መጽሃፍ ስላስነበበን ምስጋና አቀርባለሁ።መርጃ ኃይል ነውና የምታውቀውን ለህዝባችን አሳውቀህ ኃይሉን ያጠናክር ዘንድ ማሳሰብ ይጠበቅብሃል።

በመጨረሻም ቀጣዩን ስራህን በጉጉት እንጠብቃለን በርታ እያልኩ የወፍ በረር ምልከታዬን በዚሁ እቋጫለሁ። ◆

# የኢትዮጵያን ኮሚኒቲ አማርኛ ሬድዮ ፕሮግራም

855 AM

ዘወትር ዓርብ ምሽት እንደ ኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ 3 ሰዓት እስከ 4 ሰዓት ከ3CR ሬድዮ ጣቢያ በ855 ኤ ኤም ላይ በአማርኛ ቋንቋ ይተላለፋል።

ከየትኛውም የአውስትራሊያ ስቴት በስልክ ቁጥር

1300-769-801

በመደወል ማድመጥ ይችላሉ



# ስለ ዞን ዘጠኝ ጦማሪያን ከዞን ዘጠኝ ጦማሪ

ከገጽ 19 የዞረ

የጨበጡ ንጹህን ሲሰባሰቡ ሳይቀር እንቅልፍ ያጣል ማለት ነው።

ከሁሉ የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ ምንም ነገር በቀላሉ በማያመልጠንና ነገሮችን በቀላሉ ልንረዳ በምንችልበት በዚህ ዲጂታል ዘመን፤ ዜጎች እኛ ብቻ የምንላቸውን ነው የሚሰሙት፤ ሌላ እውነት የላቸውም ከሚል ራስን አላዋቂ የሚያስደርጉና ግምት ውስጥ የሚከቱ አስተያየቶችን በብዕር ስም ከሚጠቀሙ ባለስልጣኖቻችን መስማቴ ነው። ይህ አሳዛኝም ብቻ ሳይሆን አሳፋሪም ነው። ነገር ግን እንደፈለጉ የሚያዙበት ፖሊስና የፍርድ ስርዓቱ በእነሱ እጅ ነውና በትዝብት የምናልፈው አይደለም።

### ዞን ዘጠኝ እነማንን ይወክላሉ?

የተለየ ውክልና የላቸውም። እንደማንኛውም የአገሬው ወጣት ሆነው ፖለቲካን ደፈር ያሉ ናቸው። ሻይ ቡና እየተባባልን አስሩን እያነሳን ስንጥል 30ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አንድ አርቲክል ዱብ የሚያደርገው ታታሪው በፍቃዱ ኃይሉ አለልህ።...ለምትጠይቀው ጥያቄ መልስ የማያጣው፤ የማይረሳው፤ ከነማስረጃዎቹ ጎልጉሎ የሚሰጥህ አስገራሚው ዘላለምም አለልህ።..."አካሄድ" የምትል ተንከባካቢና አራሚ መስመር አስያዥ፤ ጽሁፎች ጽንፍ እንዳይዙ የምትከላከል ሶልያና ሽመልስም አለች።....ፍቅር የሆነች፤ የተለያዩ ጽንፎችን ለመረዳትና ለማወቅ የማትሰለች፤ በገባትም መጠን የምታስረዳ ሁሉን ቻይ ገራሚ የሆነች ምርጥ ልጅም አለችበት! ማህሌት ፋንታሁን።...ስለሰላማዊ ትግል አውርቶ የማይጠግብ፤ ሃይማኖተኛ፤ ታጋሽ ግን ያልመሰለውን ለመቃወም ለይሉኝታ ቦታ የሌለው፤ ልባምነቱ የሚያስቀናህ አቤል ዋበላም አለልህ።...ቢዚ እየሆነ የሚያስቸግረን፤ ሲገኝ ደግሞ እንደ ብዙ ሰው የሆነ፤ በባለሙያ እይታ የሚመራን፤ ከፍታ የሚታየው እንዳልካቸው ኃይለ ሚካኤልም አለበት። ...እንጀራ ሆኖበት የሰው ኃይል ኃላፊ የሆነው፤ ስለ ኢኮኖሚክስ አውርቶ የማይጠግብ፤ ስለ አፍሪካ መዋሃድ የበለጠ የማወቅ እቅድ የነበረው፤ የመንግስት ለውጥ ባይመጣ እንኳ ኢሕአዴግ ራሱ ይለወጣል የሚለው ተስፈኛው ናትናኤል ፈለቀም አለ።.. አሰልቺ ቁምነገሮችን ወደ ቀልድ መቀየር የሚችል ታዛቢ፣ ፈጣንና በአማኝና ኢ-አማኞች መሃከል በሚፈጠሩ ክርክሮች ሙድ የሚይዝ፤ ለለውጥ የሚታትርና ለውጥ የተራበው አጥናፍ ብርሃንም ሌላው ነው ። .. እኔ? እኔማ እየጻፍኩ ነው::

በአጠቃላይ ጉብዝናው ስንፍናውም ቢኖርም መናበባችንና መግባባታችን ኮሽ ሳይልብን አብረን እንደተፋቀርን አዝልቆናል። ዴሞክራሲ አለ የሚለው የዋህነታችን ብዙዎችን ለእስር የተወሰኑትን ለስደት ዳርጎን

አገር አልባ አድርጎናል:: በዚህ መከራ ውስጥም ተስፋ መቁረጥ የሚባል የለም::

### የከትትል ሀሁ!

ከአመታት በፊት ነው፤ አንዳንድ ‹ምጡቅ› ደህንነቶች በሶሻል ሚዲያ እንቅስቃሴው ፊትአውራሪ የሆነውንና የኢህአዴግ ደጋፊም ተደጋፊም ያልሆነውን ወዳጃችንን ‹በልዩ የምርመራ ውጤታቸው› አፋጠጡት። ባለበት ክልል የአካባቢ ደህንነቶች ተጠርቶ ቢሯቸው ሲገባ ሁለት ደህንነት ተብዬዎች እየጠበቁት ነበር። አንደኛው እንዲቀመጥ ከጋበዘው በኃላ ስለልማቱ ያለውን አመለካከት እና የፖለቲካ አቋሙን ጠየቀው። ሌላው ከፊት ለፊቱ የተቀመጠው ደግሞ ሽጉጡን አውጥቶ ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ስለልማቱ ኢቲቪን ከደገመለት በኃላ ጸረ-ልማት ከሆኑ ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያቆም አስጠነቀቀው።

በተለይም ፌስ ቡክ ከሚባለው ሰውዬ ( አዎ "ፌስ ቡክ የሚባለው ሰውዬ" የሚለው ቃል ከደህንነቱ ሰው የተሰማ ነው) ጋር ያለውን ግንኙነት በአስቸኳይ እንዲያቆም፣ አለበለዚያ (ሽጉጡን በአይኑ እያሳየ) እንደፈለጉ እንደሚያደርጉትና ምንም እንደማያመጣ አስረግጦ በመንገር አሰናብቶ ታል::

እሱም ሶሻል ሚዲያን ከሰው መለየት እንኳን የማይችሉ ኃይሎች ሰለባ እንዳይሆን በመስጋቱ በጊዜው ከፌስቡክ ተሰውሮ ነበር። ይህም በወቅቱ ብዙዎችን በስጋት ያነጋገረ ሊሆን በቃ።

### ፍረጃና ዞን ዘጠኝ

መንግስት ከሰሞኑ የዞን 9 እስር ጋር አያይዞ ከሚኮንናቸው ድርጅቶች አንዱ አርቲክል 19 ነው። ምንም እንኳ መንግስት ስሙን ብቻ ጠርቶ ቢያልፈውም አርቲክል 19 በዩ ኤን ከጸደቀውና ኢትዮጵያ ጭምር ከተቀበለችው ቻርተር ውስጥ አንቀጽ 19ኝን ስሙ አድርጎ የመናገርና ሃሳብን መግለጽ ነጻነት ላይ የሚሰራ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተቋም ነው:: ይህ ተቋም ዛሬ ብር ከሰጡት ጋር ተባብሮ ለጥፋት (ሃሳብን በነጻነት ስለመግለጽ) ከዞን9 ጋር ይሰራል ተብሎ መንግስትን ያስገመተ ክስ ከመከፈቱ በፊት ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ይሰራ እንደነበር ስንቶቻችን እናውቅ ይሆን? . .አርቲክል 19 ለጋዜጠኞች ይሰጣል በሚል መንግስት ህገ ወጥ አስመስሎ ከሚኮንነው ስልጠና አንዱ የኢንተርኔት ደህንነትን ይመለከታል። ይህ ስልጠና ጭቆና ባለባቸውም ሆነ በሌሎች አገሮች ውስጥ ማንኛውም ጋዜጠኛ እና ከኢንተርኔት ጋር የተያያዘ ስራ የሚሰራ ሁሉ ሊሰለጥነው የሚገባ መሰረታዊ ትምህርት ያለው ነው። ጋዜጠኞች ምንጮቻቸውን ለመጠበቅ እንዲችሉ፣ ራሳቸውንም ከቫይረስና ከማልዌር እንዲከላከሉ ብልሀቱን የሚያመላክት፤ አማራጭ ድረ ገጾች በሚታፈኑባቸው አገራት ውስጥም እንዴት የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት እንደሚችሉ የሚያሳውቅ ነው:: ይህ በነጻ ምድር ላሉ በተለይም ለአይ ቲ ሙያተኞች ተራ ጉዳይ ሊመስል ይችላል። ሙያቸውን የሚያሻሽሉበትና የሚያዘምኑበት በቂ አማራጭ በማይገኝባት ኢትዮጵያን በመሰለች አገር ውስጥ ላሉ ዜጎች ግን እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው::

# ኮሜዲያን ክበበው ገዳ

*ክንጽ 121 የዞረ*

አገር ቤት በምን ሁኔታ እንዳለ አላውቅም። በባህሪ ደረጃ ግን በጣም የሚያስቅህ ሰው ነው። እኔ በበቂ ሁኔታ አልሰራሁትም። በተለይ ዱቤ ሊጠይቅ የሚመጣን ሰው እንዴት አድርጎ በአሽሙር እንደሚናገርና ትርኢት እንደሚያደርግ ብትይ የሚገርምህ ሰው ነው።

**አሻራ** - ክበበው በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ተለያዩ አገራት እየተጓዝክ ስራዎችህን በማቅረብ ላይ ትገኛለህ። የዲያስፖራው አቀባበል እንዴት ነው? የተለዩ ገጠመኞችስ ነበሩህ?

**ክበበው** - አሁን አሁን ብዙ ልምድ አግኝቻለሁ እንጂ በተለያዩ አውሮፕላን ጣቢያዎች የሚያጋጥሙ መደነጋገሮች አሉ። ኤግዚት የሚለውን ሳላውቅ ልገባበት ሞክሬ አላርም የጮኸብኝ ጊዜ ሁሉ ነበር። ያው "ኖ እንግሊሽ፣ ኒው ካመር . . ." እያልኩ ባለችኝ እንግሊዘኛ አስረድቼ ተገላግያለሁ።

በውጪ ያለው ኢትዮጵያዊ አቀባበል ግን ሁሌም የተለየ ነው። አገሩን የናፈቀ፣ የአገሩን ቀልድ የሚፈልግ ነውና በጣም ያስደስታል። የውጪው ነገር አይደንቃቸውም። ማሲንቆ እንጂ ሳክስፎን ይዘህ ብትሰራ ጉዳያቸው አይደለም። እኔም ታዲያ ይገር የምመጣት ቀልድ የአገር ቤቷን ነው። ስለዚህ በሄድኩበት ቦታ ሁሉ ያለው አቀባበል ያስደስታል። አሜሪካ ሄድኩ አውሮፓ፣ አረብ አገር ሆነ እስራኤል ወይም አውስትራሊያ አበሻ አበሻ ነው። ሁሌም ተሰብስቦ ስቆ ነው የሚሄደው።

እንዴ? ....እግዚአብሄር አንደበት የሰጠህ እኮ ዓይንህ የሚያየውን ዕውነት እንድትናገርበት ነው። እኔም ኮሜዲያን እስከሆንኩ ድረስ አሁንም ሆነ ወደፊት የሚታየኝን ከመስራት ወደኋላ አልልም።

**አሻራ** ሰሞኑን በአሜሪካ ባቀረብከው ሾው ላይ የኃይሌ ገ/ስላሴን ጉዳይ ጨምሮ የተለያዩ ምርጥ ወቅታዊ ቀልዶችን አቅርበሀል። ያገኘኸው ምላሽ እንዴት ነው?

**ክበበው** - የተለያዩ የግለሰብ ዛቻዎችም እየተጻፉልኝ ነው። የግለሰብ ያልኩት መቼም መንግስት ታች ወርዶ ከግለሰብ ጋር አይለፋለፍም በማለት ነው። ዋናው ነገር እኔ ኮሜዲያን እንጂ ፖለቲከኛ አይደለሁም። በኮሜዲያንነቴ የሚሰማኝን፣ የሚታየኝን ነው የገለጽኩት። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን ነገር ነው የሰራሁት። ሌላ ምን ነበር እንድሰራ የሚፈለገው? ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ላይ ኮሜዲ ካልሰራህ እንደገና ተመልሰህ ስንዝሮና ለማ በገበያ ላይ አትሰራ?! ወይስ "አንድ ሰውዬ ነበር " ብዬ ላቀርብ ነው? ይህን ዐይነቱ ነገር ነው የመስራት መብታችን አስከምን ድረስ ነው የሚያስኘኝ። አይደለም መንግስትን ደጋፊዎቹን ሳይቀር ይህን መሰሉ ስራ በጣም ያንገሸግሻቸዋል። "ለምን እንዲህ ትሰራለህ?" ይላሉ።

እንዴ...?! እግዚአብሄር አንደበት የሰጠህ እኮ ዓይንህ የሚያየውን ዕውነት እንድትናገርበት ነው። እኔም ኮሜዲያን እስከሆንኩ ድረስ አሁንም ሆነ ወደፊት የሚታየኝን ከመስራት ወደኋላ አልልም። በፊትም ቢሆን እኮ ማንም ያልደፈራቸውን ብዙ ስራዎች ሰርቼ ነበር። ያሁኑ ግን . . . ምናልባት ምርጫው ስለደረሰ እንደሁ አላውቅም የሚያንገበግብ ነገር ነው የሆነው። መጨረሻውን እናየዋለን ነው የምለው። የሰራሁት የመሰለኝን ነው። ባጭሩ ኮሜዲያን ነኝ። ኮሜዲ ነው የሰራሁት።

**አሻራ** - ሙያው እራሱ እኮ በማህበረሰቡ፣ በመንግስትም ሆነ በተለያዩ ሙያዎች ውስጥ ገብቶ የመፈተሽ የኃላፊነት ስሜትም የሚጠይቅ ነውና . . . እንዴት ነው ወደፊትስ እነዚህን መሰል ስራዎች ላይ ለመቀጠል የተዘጋጀህበት ሁኔታ አለ ይሆን?

**ክበበው** - አዎ! ብዙ ስራዎች አሉኝ። ስታንድ አፕ ኮሜዲ ነው የምሰራው፤ በሚታዩኝ ነገሮች ላይ ሁሉ ከመስራት ወደ ኋላ አልልም። ስታንድ አፕ ኮሜዲ ደግም እንዳልከው ሁሉም ነገር ውስጥ እየገባህ ያየኸውንና የተሰማህን በኪነጥበብ መልኩ አቀናብረህ ለህዝብ የምታቀርብበት ነው። ግዴታህም ነው። እኔም በማቅረቡ እቀጥላለሁ።

**አሻራ** - ሙያውን በሚመለከት ከመንግስት፣ ከማህበረሰቡም ሆነ ከራሳችሁ ከኮሜዲያኑ በኩል ቢስተካከል ወይም ይህ ቢሆን ጥሩ ነው የምትለው ምንድን ነው?

**ክበበው** - በመንግስትም ሆነ በግለሰብ ደረጃ ሙያውን የሚደግፈው አካል የለም። ግንዛቤው ቢኖር ኖሮ እኮ መንግስትም ሆነ ባለስልጣናቱ ከኮሜዲያን በተማሩ ነበር። አሁን እዚህ አገር ‹ኮሜዲያን ምን አሉ?› ይባላል። ስህተቶቻቸውን ለማወቅ ሳይቀር ይጠቀሙባቸዋል። እኛም ጋ ቢሆን ለወደፊቱ መንግስት ለሙያው ትኩረት ሰጥቶ ‹ይህን ለምን ሰራህ? ይህን ለምን አደረክ?› የሚባል ነገር ቀርቶ የመሰለህን እንድትሰራ ቢተውህ ይበጃል። ያለበለዚያ ወደፊት ኢትዮጵያ ውስጥ ኮሜዲ የሚኖር አይመስለኝም። ለምን ቢሉ የሚያበረታታ ነገር የለማ! እኔ ማጥ ውስጥ መቆሜን ያየ ሌላ ማንም መጥቶ ተመሳሳይ ማጥ ውስጥ መቆም አይፈልግም።

**አሻራ** - በተመሳሳይ መልኩ ለምሳሌ በጋዜጠኞች ላይ የተጠናከረ አፈና አለ። ይህን መሰሉ ችግር ወደ ኮሜዲያኑም ሊዘልቅ ይችላል ብለህ ትሰጋለህ?

**ክበበው** - ለምን አይዘልቅም? ተናገርክ እና ጻፍክ እኮ ያው ነው። ጋዜጣ ላይ ስላልወጣ ነው እንዴ? እንደውም ኮሜዲው ከጋዜጣውም የሚበልጥ ይመስለኛል። ለምሳሌ ዲያስፖራው የመንግስት ጠንካራ ተቃዋሚ ስለሆነ እሱን ሰብስበህ ማዝናናትህና ማሳቅህ በራሱ እንኳን የሚያቃጥላቸው ነው የሚመስለኝ። ስለዚህ ለምን አያደርጉም? አያደርጉትም ከማለት ያደርጉታል ማለቱ ይቀላል። ማንኛውም ሰው ላይ እንዳደረጉት ያደርጉታል። ምናልባት ፊት ለፊት አያደርጉት ይሆናል እንጂ።

**አሻራ** - ሌሎች ኮሜዲያንስ የልባቸውን እንዲገልጹ፣ ትክክለኛውን የህዝቡን ስሜት እንዲሰሩ ምን ትመክራቸዋለህ?

**ክበበው** - ሌሎችን እንዲህ ስሩ ማለቱ ያዳግታል። እኔ ማዘዝ አልችልም። የሚሰማቸውን ስሜት፣ የሚቆረቁራቸውን ሁሉ ቢሰሩ ግን በጣም የተሻለ ነው ብዬ ነው የምገምተው።

**አሻራ** - ኮሜዲያን ክበበው ገዳ ለቃለ ምልልሱ ከልብ አመሰግንሃለሁ።

**ክበበው** - እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# የመለስ ጂዮ-እስትራቴጂ "ትሩፋቶች" እና አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት ....

*ከገጽ 13 የዞረ*

ለሁለት አስርተ ዓመታት የሰፈነው ምስቅልቅል ሁኔታ ለኢትዮጵያ መንግስት የጂኦ ፖለቲካ ራስ ምታት ብቻ ሳይሆን የስጋት ምንጭም ነው። ከኤርትራ ጋርም ሰላምም ሆነ ጦርነት አልባ ፍጥጫ አሁንም ቀጥሏል። መቀጠል የማይችል ከበይነ መንግስታት ግንኙነት ያፈነገጠ አካሄድ ነው። አንዱ የአካባቢው አለመረጋጋት ምክንያት ተደርጎም ይጠቀሳል። በዚህም በፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጋባዥነት ከሩሲያ ጋር ወታደራዊ ልምምድ በቀይ ባህር ጠረፍ መታቀዱን ያስቧል። ይህ ወደ ቀይ ባህርና ባቢል መንድብ መተላለፊያ ድረስ የሚዘልቀው አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት ለፕሬዚዳንት ኢሳያስ ሰርግና ምላሽ ነው። ምክንያቱ እምብዛም አያመራምርም። ልክ እንደ በፊተኛው ቀዝቃዛ ጦርነት ወቅት ሁሉ አምባገነን መሪዎቹ ካንዱ ጎራ ካልተሰማሙ የማኩረፊያ መንጠልጠያ ወደሚሆነው ተቃራኒ ጎራ የመቀላቀል ዕድል ይከፍትላቸዋልና ነው። እንዲያውም ከሰማይ የወረደ ማለፊያ አጋጣሚ አድርገው ይመለከቱታል።

'ተዛወሪ መኪና ሞስኮን አስመራን ኮይኑ መዛወሪዬ"ማለታቸው የት ይቀራል። ድሮ ኢትዮጵያ ወይም ሞት ባሉበት ጊዜ "ሽዋን አስመራን ኮይኑ መዛወሪያዬ" እንዳሉት ማለት ነው። የጋራ የባህር ላይ ወታደራዊ ልምምዱ የዓላማቸው ፈንጣቂ መልዕክት ነው። የዛሬ አስራ አንድ ዓመት ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ ባበጃጀው ጸረ ሳዳም ሁሴን የበጎ ፈቃደኞች ጥምረት (Coaliton of Willing) መፈናጠጥ አልተሳካም እንጂ ሳይጠሩ "እኛም አለንበት" ማለታቸው መቼ ቀረና። የሚገርመው በተባለው ጥምረት 46 ሃገሮች ስማቸውን መዝግበዋል። በወታደራዊ ዘመቻው ግን የተሳተፉት ሶስት ብቻ ናቸው። ሌላው አስገራሚው የፕሬዚዳንት ኢሳያስ ሃገር ሳትጠራ "አቤት" ብትልም ጥምረቱን መቀላቀል ሳይሳካላት የቀረ ሲሆን ቋሚ ጦር እንኳን የሌላቸው ማርሻል ደሴትና ሰለሞን ደሴት ግን በበጎ ፈቃደኞች ጥምረት ስማቸው ተካተዋል።

እነዚህ በታሪክ ወደ ኋሊት ፈሰን (የትዝታ አንጎርጓሪዎቹ እንደሚሉት) የዳሰስናቸው ጎራ ለይታዎችና የአሰላለፍ መለዋወጦች ዛሬ

የሚኖራቸው እንደምታዎች ከበፊተኞቹ ለየት ማለታቸው አይቀሬ ነው። ማርክስ እንዳለው "ታሪክ ራሱን ይደግማል" ቢባልም ቅሉ በተመሳሳይ አኳሃን ከቶ ሊሆን አይችልም ነውና። አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት ከዚህ በፊት ከ1948-1989ዓ.ም. ድረስ ከሰፈነው ፍጥጫ ጋር የሚጋራው ገላጫ ባህሪያት ቢኖሩትም እንኳን በይዘትም ሆነ በቅርጽ መቼም ሊመሳሰል አይችልም። የሶቭየት ህብረት መራሹ የምስራቅ አውሮፓው ወታደራዊ ቃል ኪዳን የዋርሶው ጥምረት የለም። በተጻራሪው የቆመው የናቶ (NATO)ቃል ኪዳን ከመኖሩ አልፎ ወደ ሩሲያ ድንበር ካልተስፋፋሁ እያለ ነው። ዩክሬንን ከጠረነፈ ደግሞ የሩሲያ ድንበርተኛ ሆኖ አረፈው ማለት ነው። የዩክሬን ውዝግብ እምብርቱ ይሄው መስፋፋት ነው። የአሁኑ የዩክሬን ፍጥጫ እንደ 2008ዓ.ምህረቱ የጆርጂያ ውጊያ በቀላሉ የሚበርድ አልሆነም።

ዛሬ በዓለማችን ከየት መጣ ሳይባል የሁሉን አሰላለፍና አወጋገን ለይታዎችን ባንድ ጆንበር ያመሰቃቀለ ክስተት ዱብ ዕዳ ሆኖ ዱብ ብሏል። የሰሞኑ መነጋገሪያ ርዕስ የሆነው የኢራቅን ሰሜን ክፍልና የሶሪያን መሬት በከፊል የተቆጣጠረው የሙስሊሙ መንግስት (ካሊፌት -ISIS) መስፋፋትና በወታደራዊ ኃይል የመፈርጠም ጉዳይ ነው። ሁሉም የአካባቢ ሃገራትም ሆኑ ዓለም አቀፋዊ ሃይሎች አሰላለፋቸውን እንዲመረምሩ ያስገደደ ክስተት ሆኖ ይታያል።

የኢትዮጵያ እንደ አንድ ወጋኝ ኣጋር የአካባቢ ሃይል ተፈላጊነትና ተመራጭነት እነዚህ እሳቤዎችን ከግምት ያስገባ አካሄድ ነው። በኢትዮጵያ በኩልም በባዕዳን ሃገራትና ሃይሎች ማለቴ ነው። ይህ መሆን ያለበት አግባብ ነው። እነሱም ማስከበር የሚሹት ብሔራዊ ጥቅም አሏቸው። የኢትዮጵያ መንግስት ሃገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፎ ነው የሚንቀሳቀሰው። በንድፍ ደረጃ ይህንን ይመስላል። ላለፉት 23 ዓመታት በስልጣን ያለው መንግስት ስልጣኑን "በኢትዮጵያ ብሔር፣ብሔረሰብና ህዝብ ስም ጨቦጥኩ" ይበል እንጂ ሃገራዊ ብሔራዊ ጥቅምን ማስጠበቅን መድረሻ ግቡና የፖሊሲ መነሻው አድርጎ አይንቀሳቀስም። ይህንን ለማለት በቂ ምክንያት ማቅረብ ይቻላል።

ማንኛውም የመንግስትን ስልጣን ለመሸከም ብቃት ያለው መንግስት የህዝቡን ደህንነት ከማስጠበቅ ባሻገር የሃገሪቷን ጥቅማ ጥቅሞችን ማስጠበቁ የውጭ ግንኙነቶቹ መነሻዎች ናቸው። በኢትዮጵያ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የህልውና መንስኤና መዳረሻ ግብ ግን ያንድ አካባቢ ጠባብ ቡድንን በስልጣን ማቆየትና ዘላቂነቱን በተቻለ መጠን ማረጋገጥ እስኪመስል ድረስ ላንድ ወገን ያጋድላል። በአካባቢ ደረጃም ሆነ በዓለም አቀፋዊ መስተጋብሩ፣ ትስስሩና የጎራ ለይታ አወጋገኖቹ ይህንን ዕውነታን ያንጸባርቃሉ። በመግቢያዬ ላይ ወደ ኋላ በታሪክ ተጉዘን የተመለከትናቸው የቅርቡም ሆኑ የሩቁ የሃገሪቷ ጎራ ለይታና ጂኦ-ስትራቴጂያዊ አሰላለፎች መሰረታቸው አይዲዮሎጂ ተኮር ነበር ለማለት ያስደፍራል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስትና የአጼ ሃይለስላሴ ከስደት መመለስ በኋላ ኢትዮጵያ ያለጥርጥር የአሜሪካ መራሹ "የነጻ ዓለም" ወጋኝና ኣጋር ነበረች። የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወደ ኮሪያ የዘመተው ምንም እንኳን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት መርሓ ግብርና አዝማችነት ቢሆንም "ነጻ ዓለምን" ከኮሚኒስት ወረራ መከላከል ነው እስትራቴጂያዊ አተያዩ። የደርግ መንግስት በአድሃሪና በተራማጅ አረቦች መሀል ልዩነት ፈጥሮ መንቀሳቀሱም ሌላ ተቃራኒ ኢድዮሊጂ ማቀንቀኑን አመላካች ነበረ። በተቃራኒው የወያኔ/ኢህአዲግ ከአጎራባች ሃገሮች ሁሉ አስተማማኝ መሰረቶች ላይ የተደላደለ መስተጋብርና አግባብ ያለው ከሱዳኑ ከአልበሽር መንግስት ጋር ነው። ሁለቱ መንግስታት ያስተሳሰብ ተጋሪዎች አይደሉም። የሁለቱ መንግስታት ወጋኝ ኣጋርነትና የጠበቀ ወዳጅነት መሰረቱ ሁለቱም ገዥ ፓርቲዎች ያለ ማንም ተፎካካሪ የተቆጣጠሩትን ስልጣን ከእጃቸው ሳይፈተልክ ለዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚተጉ መሆናቸው ነው። ከዚህ በላይ ከተመለከትነው የአካባቢ አወጋገኖችና ጎራ ለይታ አሰላለፎች ይበልጥ የተደላደለ የሚመስለውም በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም የሚል ዕምነት አለ። ይህ ግንኙነት በ1976ዓ.ም. ወይም ወያኔ ከተመሰረተ አንድ ዓመት በኋላ የተጀመረ ነው። በ1995ዓ.ም. በአዲስ አበባ በግብጹ ፕሬዚዳንት ሁስኒ ሙባረክ ላይ የተቃጣው የግድያ ሙከራ ግንኙነቱን ያደፈረሰበት አጋጣሚ ብቻ ነው ከዚህ አግባብ ፈንገጥ ያለው።

የሁለቱን ገዥ ፖርቲዎችና መንግስታት ንፋስ የማይገባበት ወዳጅነት ምስጢር የነገሩን ለበርካታ ዓመታት እንደ አገናኝ መኮንን ያገለገሉት ሜጀር ጀኔራል አል- ፉቲሕ ዓርዋ ናቸው። ጀነራሉ ባለፈው የካቲት የህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ህዝበ ትግራይ (ሕወሓት) 39ኛ

*ወደ ገጽ 37 ዞሯል*

(ከገጽ 16 የዞረ)

ወርሀ ሚያዚያ 2003 ዓ.ም. ላይ ነበር። ወጣት ተስፋዬ ይህ ነው ባልተባለ ምክንያት የህወሀት/ኢህአዲግ የደህንነት ሰዎች አዲስ አበባ ውስጥ ተከራይቶ ከሚኖርበት ቤት ወስደው ማዕከላዊ ወረወሩት። ለተከታዮቹ 23 ወራትም ለህሊና የሚከብዱ ማሰቃየቶች ሲፈጽሙበት ቆዩ። የወጣቱ ጀርባ በኤሌትሪክ ንዝረት ተጠብሷል። የዘር ብልቱ ላይ ውሀ የተሞላ ጠርሙስ እያንጠለጠሉ አሰቃይተውታል። ለረጅም ሰዓታት ቀዝቃዛ ውሀ በተሞላ በርሜል ውስጥ እያስቀመጡም ሰውነቱን ያደነዝዙት ነበር። ተስፋዬ ተካልኝ 23 ወራቱን ሙሉ ‹ምድራዊ ገሀነም ውስጥ አሳለፈ› ማለቱ ይቀላል። ከዚያ ከቆሙት በታች፣ ከሞቱት በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ አፋኞቹ ባንዷ ምሽት በመኪና ጭነው አብዮት(መስቀል) አደባባይ ጋ ጥለውት ሄዱ።

ለአንድ እናቱ ተስፋ መሆን ችሎ የነበረው ተስፋዬ ለራሱ እንኳ የማይበቃ ለዘላቂ የአካልና የዐይምሮ ህመም የተጋለጠ ሰው ሊሆን በቃ። ሽንቱን እንኳ መቆጣጠር ተሳነው። በዘር ብልቱ ላይ በደረሰበት ጉዳት ሳቢያም ዘሩን የመተካት ተስፋ እንደሌለው በህኪም ተረጋገጠ። ተስፈኛው ተስፋዬ በስርዓቱ የጭካኔ ባለሟሎች ተስፋውን ተቀማ። እንዲህ ነች የህወሀት ዘመኗ ኢትዮጵያ። . . .

❁ ❁ ❁

ወ/ሮ መንበረ አበበም የአገዛዙን የጭካኔ ልክ ለማሳየት የምትበቃ አብነት ነች። ዜጎች እንዴት በማያውቁትና በማይገባቸው ውንጀላ ስር እንደሚማቅቁና ማንኛውም ሰው በየትኛውም ሰዓት ለአደጋ ሊጋለጥ እንደሚችል ወ/ሮ መንበረን የመሰሉ ሰለባዎች ህያው አስረጅ ናቸው። ታሪኩ እንዲህ ነው፡-

ወ/ሮ መንበረ ከባለቤቷ ከአቶ ቃለአብ ተስፋሁን ጋር በቀበሌ ፲፩ የቤት ቁጥር 641 ውስጥ በፍቅር የተሞላ የተረጋጋ ሰላማዊ ህይወት ነበር የሚኖሩት። መስከረም 8 ቀን 1990 ዓ.ም. ግን ያልታሰበ ዱብዳ ወረደባቸው።

የህወሀት/ኢህአዲግ ታጣቂዎችና ሲቪል ለባሾች ከለሊቱ ፲፩.00 ሰዓት ላይ ድንገት ቤታቸውን ወረሩት። በራቸውን ሰብረው ገብተው አገር አማን ነው ብለው የተኙትን ጥንዶች በቁጥጥር ስር አዋሏቸው። ወደ ወረዳ 20 ፖሊስ ጣቢያም ወሰዷቸው።

ወዲያውም በወቅቱ የዞን ሁለት ፖሊስ አዛዥ በነበረው ተጋዳላይ አግዓዚ በሚባለው የህወሀት ታጋይ የሚመራው ቡድን ወይዘሮ መንበረን በመደብደብና በማሰቃየት የዕለት ስራውን ጀመረ።

"ባለቤትሽ ሜርኩሪ እንዳለው ደርሰንበታል ። የት ነው ያስቀመጣችሁት?" ይሏታል።

" ሜርኩሪ ምንድነው? " ግራ የገባት መንበረ ትመልሳለች። ዱላው ቀጠለ።

በተለይ መስከረም 27 ቀን ግን የተለየ ነበር። የወይዘሮዋ ሰቆቃ ማብቂያ የሌለው መሰለ። ወታደር ምህረተ አብ፣ ወታደር ጌታሁንና ሌሎችም የጭካኔ ዶፋቸውን አወረዱባት። ጥፊው እርግጫው አላጠገባ ቸውም። በጎማ ለበቅ ጀርባዋንና የውስጥ እግሯን ተለተሉት።

የጨነቃት ወይዘሮ መንበረ " እባካችሁ የሁለት ወር ቅሪት ነፍሰ ጡር ነኝ" እያለች ተማጸነች። "ለምን የ7 ወር እርጉዝ አትሆኝም!" እያሉ ተዘባበቱባት። ህሊናቸው የታወረ፣ ሰብአዊነት ያልፈጠረባቸው ናቸውና በጣዕር ልመናዋ እየተሳሳቁ ማሰቃየቱን ቀጠሉ። ‹አህያ ነሽ፤ አይሰማሽም!› እያሉ የመውረዳቸውን ልክ በሚያሳይ ስድብ ሊያዋርዷት ሞከሩ። እጆቿን ወደ ላይ አስዘርግተውና ግድግዳ አስይዘው ጀርባዋን ያለማቋረጥ ገረፏት። ይሄኔም . . . ደም መታት። አቅፌ እስማለሁ ብላ የጓኝለት ጽንስ ተስፋ ሆኖ ቀረ። ወይዘሮ መንበረን አስወረዳት።

የጭካኔው ብዛት መቋጫ አልነበረውም። በዱላ ብዛት ጽንሷን ያስወረዳት እናት ደሟ ሲፈስ ሰነበተ። ህክምና እንኳን የሚፈቅድላት አልነበረም። ከ3 ተጨማሪ ሳምንታት በላይ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ባለው የህወሀት/ኢህአዲግ ሲኦል ውስጥ እየማቀቀች ቆየች። ህክምና አግኝታ በወቅቱ ማህጸኗ ባለመጠረጉም እስካሁን ህመምተኛ ሆና ቀረች።

❁ ❁ ❁

የ1997 ዓ.ምህረቱን ምርጫ ተከትሎ በብዙ ሺህ ኢትዮጵያን ላይ የደረሰው መከራ የሚረሳ አይመስለኝም። የ፲፩ ዓመቱን ታዳጊ ወጣት ነብዩን ጨምሮ ከ200 በላይ ንጹሀን በግፍ የተገደሉበትና ከ30 ሺህ በላይ በጅምላ የታሰሩበት ያ ወቅት ከህሊና በላይ የሆኑ ሰቆቃዎች የተፈጸሙበት ነበር። ለአብነቱ ያህል ግን የ23 ዓመቱን ማኒከስ ወንድሙን አስታውሼ ጽሁፌን ላብቃ።

በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ ቀበሌ 15፣ በቤት ቁጥር 791 ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር ነበር የሚኖረው። በወርሀ ሰኔ 1997 ዓ.ም. ግን የአግዓዚ ታጣቂዎች ከለሊቱ 7.00 ሰዓት ላይ ከመኖርያ ቤቱ ይዘውት ቤተ መንግስት አካባቢ ወዳለውና በተለምዶ ጥይት ቤት በመባል ወደሚታወቀው ስፍራ ወሰዱት። እዚያም ቦክሰኞች የሚሰለጥኑበት አሸዋ የተሞላ ከረጢት (ሳኮ) የሆነ እስኪመስለው ድረስ አንጠልጥለው ቀጠቀጡት። ከሰባት በላይ ወታደሮች በቦክስና በካራቴ ተቀባበሉት። የረኩ ግን አይመስሉም። ከተንጠለጠለበት አውርደው ወሀ ከነከሩት በኋላ አፈር ላይ እያንከባለሉ በሳንጃ ይወጉት ጀመር። ጀርባው ላይ ብቻ አራት ጊዜ በሳንጃ ተወጋ። የቀኝ እጁን የመጨረሻ ጣት በሳንጃው በመውጋትና በመጠቅጠቅ አሰቃዩት። እራሱን ስቶ እስኪወድቅ ድረስ አላቋረጡም ነበር። ከዚህ በኋላ ነበር ወጣቱ ማኒከስ ከእሱን መሰል ሌሎች ሰለባ እስረኞች ጋር ለቀጣይ ግፍ ወደ ዝዋይ የተወሰደው።

. . . ከላይ በትውስታ ያነሳኋቸው የአገዛዙ ሰለባዎች በየወቅቱ በሺህ በሚቆጠሩ ንጹሀን ወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ስላለው ሰቆቃ ማሳያ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ። አሁን በዚህች አፍታ እንኳን በኢትዮጵያ እስር ቤቶች ውስጥ ለህሊና የሚከብዱ ግፎች የሚፈጸምባቸው ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ አያጠራጥርም። በየምዕራፉ በአገዛዙ የጭካኔ ኃይሎችና ባለሟሎች እየተጠለፉ አሳር የሚያዩ ወገኖቻችን ሰቆቃ የሁላችንም ህመም መሆኑም ዕሙን ነው። አይተው እንዳላዩ፣ ሰምተው እንዳልሰሙ መሆን ከቶም አይቻልም። ግፉ እንዲቆም፣ ሰቆቃው እንዲያበቃ ለማድረግ የበኩሉን የማይጥር ሰው ደግሞ ቢያንስ ከህሊና ወቀሳ መዳን አይቻለውም። በቅርቡ ኢቲቪ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን በቴሌቪዢን ባሳየበት ዝግጅቱ ከጀርባ የሚሰማው የጣዕር ጩኸት ድምጽ ዕረፍት ያልነሳው ወገንም ያለ አይመስለኝም። ቁምነገሩ የመከራውን ጊዜ ለማሳጠር፣ የጽልመቱን መጋረጃ በብርሀን ለመግለጥ፣ የባርነቱን ቀንበር ለመሰባበር እያንዳንዳችን ‹ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?› ብሎ ራስን መጠየቁ ላይ ነው። የየድርሻችንን ከተወጣን የነጻነት ቀን መቅረቧ አይቀርም። የሰብዓዊ መብቶች የሚከበርበት፤ ዜጎች በህገ ወጥ መንገድ ታስረው የማይሰቃዩበትና የማይገደሉበት ስርአት እንዲመጣ የየድርሻችንን እንወጣ።

**ሰብዓዊ መብቶች ለሁሉም!!!**

# ከፕ/ር አለማየሁ ገብረ ማሪያም ጋር የተደረገ .....

*ከገጽ ii የዞረ*

ለማፈን ብቻ እያገለገለ መሆኑን ዘርዝሯል።

ሁሉም ዋና ዋና የሚባሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችም እንዲሁ ጠንካራ ትችቶች ሲያቀርቡበት ነው የቆዩት። በዕውነቱ የጸረ ሽብር ህጉ የጫካ ህግ ነው ማለት ይቀላል። በአሻሚ፣ በተድፈነፈኑና ተለጣጭ አንቀጾች የተሞላ፤ ንግግርና ሀሳብ ሳይቀር በሽብርተኝነት ሊያስቀጡ እንዲችሉ ሆነው የቀረቡበት ነው። የሽብር ተግባሮችን ያበረታታሉ ተብለው የሚታሰቡ ንግግሮችን ያሰማ ወይም ለህትመት ያበቃ፣ ሞራል ወይም ምክር የሰጠ፤ በተደጋጋሚ አብሮ የታየ የሚሉና መሰል ተግባራትን ወንጀል አድርጎ ያቀረበ ነው። በዚያ ላይ እያንዳንዱ የሽብርተኝነት ክስ ገና በመታየት ላይ እንዳለ ባለስልጣናቱ የተከሳሹን ህገ-መንግስታዊ መብት ጥሰው ያልተረጋገጡ ውንጀላዎችን በአደባባይ ያቀርቡበታል። በህግ ያልተፈረደበትን ሰው ሹማምንቱ ፈርደውበት ይገኛሉ።

ኢትዮጵያን በመሰለች የፍትህ ስርዓቷ ከመንግስት ተጽዕኖ ባልተላቀቀባትና ዳኞች በትዕዛዝ በሚወስኑባት አገር ላይ የሚሰጡ የሽብርተኝነት ፍርዶችም ሆኑ የሞት ቅጣቶች ነጻና ገለልተኛ በሆነ አካል ምርመራ ቢደረግባቸው፤ ጸንቶ መቆም የሚችሉ አይደሉም። ባጭሩ የዝንጀሮው ችሎት አገዛዙ በ'ሽብርተኝነት' የከሰሳቸው ሰዎች ላይ የሞት ፍርድ ሰጠ ማለት ኢጋዘን በጅቦች ጉባዔ ላይ ሞት ተፈረደበት የማለት ያህል ነው።

**<u>አሻራ፡-</u>የመንና ኢትዮጵያ ወንጀለኛን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት አድርገናል፣ አቶ አንዳርጋቸውም በዚሁ ስምምነት መሰረት ነው የተወሰዱት የሚል መከራከርያ ያሰማሉ። ይህን እንዴት አዩት?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>***የየመን መንግስት አቶ አንዳርጋቸውን አሳልፌ የሰጠሁት ከኢትዮጵያ ጋር በ1999 ዓ.ም. በተፈራረምኩት ስምምነት መሰረት ነው ብሏል።

እኔ ይህን አለ የሚሉትን ስምምነት አላየሁትም። የየመን መንግስትም ሆነ በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ ለህዝብ እይታ አላበቁትም። በበኩሌ ለማደናገርያነት ያህል በርግጥ ከማለት ባለፈ የፈጸሙት ስምምነት አለ ብዬ አላምንም። አለ በሚል ከጸኑም ይፋ ወጥቶ በዝርዝር ላነበውና ልመረምረው እፈልጋለሁ። የዓለም አቀፍ ህግን በተለይም ቶርቸርን በመቃወም የተፈጸመውን ስምምነት (Convention Against Torture) መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለመሆኑ ሊመረመር ይገባዋል። በኔ በኩል ግን በሁለቱ አገራት መሀል የተፈረመ ስምምነት አለ ብዬ አላምንም።

**<u>አሻራ፡-</u>የሁለትዮሽ ስምምነቶች ከዓለም አቀፉ ህግና ስምምነት ጋር የሚጋጩ ሆነው ሲገኙ ቅድሚያ የሚይዘው (ወሳኙ) የትኛው ህግ ነው የሚሆነው?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>*** ነኖ፣ ቶርቸርን የሚከለክለው ህግ መሰረታዊና ሁሉን አቃፊ ነው። ይህ ማለት የዓለም አገራት በሙሉ ተስማሙበትም አልተስማሙ ለመርሁ ተገዝተው ሰቆቃ ከመፈጸምም ሆነ ሌላ አገር ወይም ግለሰብ እንዲፈጽመው ከማመቻቸት መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ቶርቸርን የሚያወግዘው ስምምነት (CAT) ይህን መሰረታዊ የዓለም አቀፍ ህግ አካል ነው በስምምነቱ እንዲካተት ያደረገው።

በዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ደግም ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አገራት የስምምነቱን (CAT) ማናቸውንም ክፍል የመጣስ መብት የላቸውም። በዚህም በየመንና ኢትዮጵያ ባለው አገዛዝ መሀል ለሰቆቃ ሊጋለጥ የሚችልን ሰው አሳልፎ የመስጠት ማናቸውም ዐይነት ስምምነት ቢኖራቸው እንኳን ያ ስምምነት ዋጋ ቢስና ህጋዊ መሰረት የሌለው ነው የሚሆነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ያን ዐይነቱ ስምምነት በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ስለመኖሩ የማያወላዳ ማረጋገጫ ሆኖ በሁለቱም ወገን ያሉ አባላትን ለክስ ሊያበቃቸው የሚችል ነው። በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ በእርግጥ ከየመን ጋር የተፈራረመው አሳልፎ የመስጠት ማናቸውም ዐይነት ስምምነት ካለው ይፋ እንዲያወጣው እሞግተዋለሁ።

2ኛ፣ በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ አንዳርጋቸው ላይ የወሰደው ማናቸውም "ህጋዊ" ነው የሚለው እርምጃ በዓለም አቀፉ ህግ ዕውቅናም ሆነ ህጋዊ ተቀባይነት የለውም። አገዛዙ ከየመን ጋር ተፈርሟል የሚለውን የህሰት ስምምነት እየጠቀሰ አፈናውን በህጋዊ መንገድ እንደፈፀመው ለመግለጽ መሞከሩ አስቂኝ ነው። ይህ አገላለጥ የሚያረጋግጠውም የዓለም አቀፍ ህግን የሚጥስ ወንጀለኛና ህገ ወጥ አገዛዝ መሆኑን ብቻ ነው። ባጭሩ አፈናውን በተመለከተ በዓለም አቀፍ ህጉ ዓይን ወንጀለኛው ራሱ አገዛዙ ሲሆን አንዳርጋቸው ደግሞ በሁለት ህገ ወጥ አገዛዞች ዓለም አቀፍ እገታ የተፈፀመበት ሰለባ ነው። ወንጀለኛ ማንንም ቢሆን የማሰር ስልጣንም ሆነ መብት የለውም።

**<u>አሻራ፡-</u>አንድ ከህገሩ ውጪ የተያዘ ሰው ወደ ሌላ 3ኛ አገር ተላልፎ እንዳይሰጥ ሊሟገት የሚችልበት መብት የለውም ወይ ? ተላልፎ መሰጠት የሚገባውስ በምን የህግ አግባብ ነው?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>***ከህግ ውጪ የተያዘ ወይም የተከሰሰ ማናቸውም ሰው ቢሆን የቀረቡበትን ውንጀላዎች የመከላከል መብት አለው። ዋናው ጥያቄ ግን አንዳርጋቸው የእስሩንም ሆነ ተላልፎ የተሰጠበትን ሁኔታ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች መሟገት ይችላል ወይ የሚለው ነው። ይህ አገዛዝ እንደሆነ የዝንጀሮ ወይም የጅብ ፍርድ ቤቶችን ነው የሚመራው። ይህን ደግሞ በ2005ዓ.ም. የቅንጅት መሪዎችና ሌሎች ከተከሰሱበት ጊዜ ጀምሮ፣ ወጣት ጦማርያን ለእስር እስከተዳረጉበት እስከአሁኑ ወቅት ድረስ በበርካታ ሂደቶች ያስተዋልነው ዕውነታ ነው። የዝንጀሮ ወይም የጅብ ፍርድ ቤቶች ማለት እንደው ላባባሉ ያህል አይደለም። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ፍትህ በጫካ ህግ ስር መታገቷን ለመግለፅ እንጂ። የአገዛዙ መሪዎች ለስልጣን ሲበቁ የጫካ ህጋቸውንም ይዘውት ነበር የመጡት። እንሆ ከ23 ዓመታት በኋላም እየተጠቀሙበት ነው ያሉት። በዚህ የጫካ ችሎት ደግሞ ጅቦች አቃቢያነ ህጎች ሲሆኑ ዳኞቹ ዝንጀሮዎች ናቸው። በዝንጀሮና ጅብ ፍርድ ቤት ደግሞ ንጹህ ሰው ተስፋም የለው።

**<u>አሻራ፡-</u>የእንግሊዝ መንግስት የአቶ አንዳርጋቸውን ነጻነት ማስከበር ቢፈልግ ምን ዐይነት ተጽዕኖ ማድረጉ ውጤታማ ያደርገዋል ይላሉ?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>***የእንግሊዝ መንግስት ጠንከር ያለ የዲፕሎማቲክ ግፊት ቢያደርግ ውጤት ማግኘት የሚቻል ይመስለኛል። ኢትዮጵያ ላለው አገዛዝ አንዳርጋቸውን የማትለቁት ከሆነ በየዓመቱ የምንለግሳችሁ በሚሊዮናት ፓውንድ የሚቆጠር ርዳታ ችግር ውስጥ ይወድቃል ሊሏቸው ይችላሉ። መቼም በምጽዋት የሚተዳደር አገዛዝን ከድጎማው ዋስትና ማጣት በላይ ቀልቡን የሚጠልፈው ርዕስ አይኖርም። የብሪቲሽ መንግስት አዲስ አበባ ላሉት ርዳታውን ጠባቂ አምባገነኖች አንድ ጠንከር ያለ የዲፕሎማቲክ መልዕክት ቢያሰተላልፍ ውጤት ማስገኘት በቻለ ነበር።

**<u>አሻራ፡-</u>የእንግሊዝ መንግስት እስካሁን ዜጋውን ለመታደግ ማድረግ የሚገባውን ህጋዊ ጥረቶች አድርጓል ብለው ያስባሉ?**

***<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>***የእንግሊዝ መንግስት ያደረገው ይህ ነው የሚባል ጥረት የለም። የአንዳርጋቸው ቤተሰቦችም ይህንኑ ነበር የገለጹት። እውነታው የእንግሊዝ መንግስት መጀመሪያ አካባቢ ጥቂት መግለጫዎች ከመስጠቱ ውጪ በአንዳርጋቸው ጉዳይ ከይስሙላ ያለፈ ጥረት ያለማድረጉ ነው። እንደኔ እይታ ከሆነ የዜጎቹን መብት በማስከበሩ ሁኔታ ላይ የእንግሊዝ መንግስት ሁለት የተለያዩ መስፈሪያዎች ያሉት

*ወደ ገጽ 33 ዞሯል*

# አንዳርጋቸው በኔ

*ከገጽ 20 የዞረ*

የባንዳ ልጆች የትግል ስልት ስንመርጥ መኖር የለብንም! ማንኛውም አይነት ጠላቶቻችንን ሊያንበረክክ የሚችል የትግል ስልት ሁሉ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል።ይህን ማድረግ ከቻልን የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ድካም መና አልቀረም ማለት ነው።

***እንደልቡ (ዳግም)-ቫንኮቨር***

## አንዳርጋቸው የንዋይና የስልጣን ፍቅር የለበትም!

**አቶ ነአምን ዘለቀ-ዋሽንግቶን ዲሲ**

የንቅናቄአችን ዋና ጸሃፊና የትግል ጓዳችን አንዳርጋቸው ጽጌ በየመን ትብብር በፋሽስታዊ ወያኔ አፋኞች እጅ መውደቅ ያስቆጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሳየው ወገናዊነት ልባችን ተነክቷል። የአንዳርጋቸው መታሰር ይቆጨናል፤ እየደረሰበት ያለው ስቃይ ያንገበግበናል፤ የሱን አይነት ብርቱ፣ ቆራጥ፣ አስተዋይና ብቃት ያለው ታጋይ ትግሉ ማጣቱ ይጎዳናል። አንዳርጋቸው በሳል የፖለቲካ ሰውና ቆራጥ የተግባር ታጋይ ብቻ አይደለም። በግል ለማታውቁት በበርካታ የእውቀት ዘርፎች በጥልቀት ያነበበ፤ ፍልስፍና፣ ሊትሬቸር፣ ሲኒማ የሚወድና ህሊናው በዕውቀት በከፍተኛ ደረጃ የበለፀገ ነው። የሰው ልጅ መከራ፣ በደልና ስቃይ እስከ አጥንቱ ይሰማዋል።

ዱባይ ላይ ከአመት በፊት ስላገኛት ኢትዮጵያዊት የነገረኝ ሲቃ እየተናነቀው ነበር።ልጅቷ ሲያገኛት ያለማቋረጥ ታለቅሳለች፤ ምን እንደሆነች ቢጠይቃት ለመናገር ባትፈቅድም አጥብቆ ሲይዛት እንደተናገረችው፤ ተቀጥራ በምትሰራበት የቤቱ ባለቤት ሽማግሌ አረብና አራት ወንድ ልጆቹ በየገዜው ተራ በተራ ደፍረዋታል። የሚያስነባት ይህ ነበር። አንዳርጋቸው "የኢትዮጵያውያን መከራና ውርደት መቼ ነው የሚያበቃው?" በሚል ነበር ሲቃ እየተናነቀው ያጫወተኝ።

አንዳርጋቸው የንዋይና የስልጣን ፍቅር የለበትም። ፍላጎቱ ያ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወያኔ ከሰበሰባቸውና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የወያኔ ሎሌዎች የተሻለ ደረጃ ላይ ባገኘነው ነበር። በምንም መለኪያ በሱ ደረጃ ብቃት፣ ምሁራዊ ብስለትና ስብዕና የተላበሡ እንደሌሉባቸው ግልጽ ነው። አንዳርጋቸው የመረጠው የፍትሕ፣ የነጻነትና የእውነትን መንገድ ሲሆን እሱ የመረጠው ከህሊናው ጋር መኖርን ነው። ለዚህም ነው ስልጣን እና ገንዘብን ገፍቶ፣ የአውሮፓን ምቾት ትቶ፣ በርሃ ወርዶ አፈር ላይ እየተኛ በርካታ ታጋዮችን አስተምሮ ትግሉን ጠንካራ መሰረት ላይ የተከለው - ትግሉን መስመር አስይዞ ዛሬ በፋሺስቶች እጅ ቢወድቅም።

ፋሽስቶቹ ወያኔዎች በተለመደው ድንቁርናቸው ያቀዱትና የአለም አቀፍ ህግን ጥሰው የሄዱበት የብልግናና የውንብድና መንገድ እሱን በማፈን ነጻነትና ፍትህ የጠማውን የኢትዮጵያ ህዝብ አንገት እናስደፋለን፣ ቅስም እንሰብራለን፣ ታጋዮችና ትግሉን እናዳክማለን፣ እናመክነዋለን ከሚል ስሌት ነበር። በተቃራኒው ኢትዮጵያውያን በሀገር ውስጥም በውጭው አለም ከዳር እስከ ዳር በከፍተኛ ቁጣና ቁጭት እንዲንቀሳቀሱ እያደረገ፤ ለመራራ ትግል እንዲዘጋጁና ለመስዕዋትነት እንዲቆርጡ እያነሳሳ ይገኛል። **<<እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ነኝ>>** በሚል በሺህ የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን ትግሉንም ንቅናቄያቸንንም እንዲቀላቀሉ እያደረገ ነው።

ዛሬ ብዙ ሺዎች የአንዳርጋቸው ጽጌን ፈለግ ተከትለዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ሚሊዮኖች የነጻነት፣ የእኩልነት፣ የፍትህ ጠበቆችና ታጋዮች ሆነው የፋሽስታዊውን የወያኔን ስርዓት በሁሉም መንገዶች እንደሚፋለሙ አፍታም ጥርጥር የለንም። በግንቦት 7 በኩል እልሃችን፣ ቁጭታችን፣ ጽናታችን፣ ቁርጠኝነታችን እጥፍ ድርብ እንዲሆን አድርጎናል። እኛም ግንባራችንን ሳናጥፍ የተጀመረውን ትግል ከግብ ለማድረስ በቁርጠኝነት ተነስተናል!።

## ከእርሱ ጋር ስተሰራ የሚባከን ጊዜ አይኖርህም!

**ወ/ሮ ሰብለ ወርቅ ታደሰ—ብሪዝበን (አውስትራሊያ)**

አንዳርጋቸው ቁጥብ እና እራሡን በጣም የገዛ ሰው ነው። ከእርሱ አንደበት ከልክ ያለፈ ንግግር መስማት ዘበት ነው።

ላመነበት ነገር የጨከነና ለትግሉ ያስፈልጉታል ብሎ ያመናቸውን ባህሪያት ሌሎች እንዲያረጉት የሚጠበቅ ሳይሆን እራሱን ሙሉ ለሙሉ በእነዚያ ባህሪያት ያስገዛ እና ጠቅላላ ማንነቱን በእነዚያ ባህሪያት የሚያስወርስ ታላቅ የድርጊት መሪ ነው።

በየትኛውም አጋጣሚ እራሱን ለማረምና ሌሎችን ለመስማት የማይደክም ሰው ነው። ትልቅ ሆንክ ወይም በእድሜም ሆነ በልምድ ( በእውቀት) ከእርሱ አነስክ ሃሳብህን ትኩረት ሰጥቶ በታላቅ አከብሮት ነው የሚያዳምጥህ።

ከሁሉ በላይ ስራ እና ውጤት ተኮር የሆነው ማንነቱ የሚደነቅ ባህሪው ነው። ከእርሱ ጋር ስተሰራ የሚባክን ጊዜ አይኖርህም። በእርግጠኝነት ያለሰራ ከርሱጋር መሆን የማይቻል ነው። ብዙ ማውራት ሳይሆን ብዙ መስራት የባህሪው ዓቢይ መገለጫ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት እጣ-ፈንታ እራሱን እያደከመ የሚያስብና ከጨለማው ይልቅ ብሩህ ተስፋን በሚዋጁ የለውጥ ትግሎች ውስጥ ከመሳተፍ ጀምሮ የትግል አቅጣጫዎቹን በመቀየስ የሚደከም መሪ ነው።

ብሩህ እና የተማሩ የህብረተሰብ ከፍሎች ዋጋ ለመክፈል እራሳቸውን ካላዘጋጁ አገራችን ከገባችበት አዘቅት ትወጣለች ማለት ዘበት ነው ብሎ ስለሚያምን ነው እራሱን ለትግሉ አሳልፎ የሰጠው።

ከሁሉ በላይ የነገዋ ኢትዮጲያ ሁላችንንም ማኖር የምትችለው ከግለሰቦች እና ከፓርቲዎች በላይ የሆኑ ተቋማት ሲኖሯት ብቻ ነው። ይህን መገንባት ደግሞ የእያንዳንዳችን ሃላፊት ነው ። እራሳችንን ለነዚህ ተቋማት ተገዢ ማድረግ አለብን ብሎ በጽናት የሚያምን ሰው ነው። አንዳርጋቸው ላመነበት ቆሞና ታግሎ ክቡር መስዋዕትነትን እየከፈለ ነው። እኛም ሕይወቱን ከመታደግ ጀምሮ ዓላማውን ግብ የማድረስ ሃገራዊና ዜጋዊ ግዴታ አለብን።

**(ሌሎች አስተያየቶች በገጽ 38 ይቀጥላሉ)**

# ቆይታ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታናሽ እህት .....

*ከገጽ 9 የዞረ*

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፦</u>** እውነት ለመናገር እስካለፈው ኖቨምበር ድረስ ምንም አስቤ አላውቅም። ምክንያቱም እንቅስቃሴው ከኢትዮጵያ ውጭ ስለሆነ ምንም ሊያደርጉት አይችሉም የሚል ዕምነት ነበረኝ።ባለፈው ኖቨምበር እዛው አስመራ ድረስ ሄደው ሊገሉት ሞክረው እንደነበር ካወቅኩ በኋላ ግን መስጋቴ አልቀረም።ስጋቴ ያው ሰላዮቻቸው በየሃገሩ ስላሉ ደህና መስለው ተጠግተው ገለውት ቢሄዱስ ብዬ እሰጋ ነበር። እንዲህ አይነት አፈና ያደርሱበታል ብዬ አስቤ ግን አላውቅም::

**<u>አሻራ፦</u> ትግል ትግል እንዳልክ አብዛኛውን የህይወት ዘመንከን አሳለፍክ፤ እስቲ አሁን እንኳ እረፍና ልጆችህን አሳድግ!› የሚል አይነት ከስጋት የሚመነጭ ቤተሰባዊ ተማጽኖ ቀርቦላቸው ያውቃል** ?

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፦</u>** በፍጹም!!!(ጫን ባለ ድምጽ) ማንም የቤተሰቡ አባል ይህን መሰል ነገር አንስቶበት አያውቅም። እንኳን ለሱ ልናነሳበት እኛው እርስ በርስ እንኳን እንዲህ አይነት ነገር ጭራሽ አናነሳም።

ወንድሜ የቤተሰቡ ሙሉ ድጋፍ ነበረው። ሁላችንም በአንድ ቤተሰብ ተቀርጸን መውጣታችንንም አትዘንጋ:: በአላማም ሆነ በአመለካከት ከሱ የተለየ ማንም የለም።

**<u>አሻራ፦</u> በአቶ አንዳርጋቸው ላይ የተፈጸመው እገታ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን በጣም እንዳስቆጣ ሲታይ ነው የሰነበተው። የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን የአገዛዙን ተቃዋሚዎች በተመሳሳይ ስሜት ከማንቀሳቀሱም በላይ በዝምታ ስር የተጠለሉ በርካታ ወገኖችንም ድምጻቸውን ጎላ አድርገው እንዲያሰሙ አብቅቷቸዋል። ከህገርቤት የሚገኙ መረጃዎችም እዚያም ተመሳሳይ ቁጣ መኖሩን አመላክተዋል። ለመሆኑ አንቺ ይህን መሰሉን ህዝባዊ ስሜት ስታዪ ምን ተሰማሽ? አቶ አንዳርጋቸው ይህን ያህል የህዝብ እውቅናና ክብር ሊኖራቸው እንደሚችልስ ገምተሽ ነበር?**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፦</u>** አልገመትኩ! ምክንያቱም በሃገራችንም ሆነ በአፍሪካ ፖለቲካ ግዜ የምናጠፋው ጥሩ ስራን በማበረታታት ሳይሆን ስህተትን እያነሳን በመወቃቀስ ላይ በመሆኑ አንዳርጋቸውም በዚህ መጠን የህዝብ እውቅናና ክብር ይኖረዋል ብዬ አልገመትኩም። የኢትዮጵያዊው ስሜት ቁጣና ቁጭት በጣም አስደንቆኛልም! አስደስቶኛልም።

አንዳንድ ሰዎች ቁጭታቸውን እስከ ማልቀስ በዘለቀ ስሜት ይገልጹልኛል። እኔ ግን ለሱ ማልቀስ አልፈልግም። በኩራት እንጂ በሃዘን ላስበው አልፈልግም። እስከዛሬ በርካታ መስዋዕትነቶችን ከፍሏል ላመነበት ዓላማ ሲል ብዙ ዋጋዎችን ከፍሏል። እኔ አሁን በደረሰበት አደጋ የሚሰማኝ አንዳርጋቸው የደከመበት ሁሉ ከንቱ እንዳልቀረ ነው። እንዲያውም “ሁሉ ነገር ለመልካም ነው!” እንዲሉ በሱ ላይ የደረሰው ነገር የመልካም ነገር መጀመሪያ እንደሆነ ነው የሚሰማኝ።መርሳት የሌለብህ እሱ ላይ የደረሰው አፈና ከዚህ ቀደም ያላየነው አይነት ድንበር ዘለል መሆኑ እንጂ ለየት የሚያደርገው እንደሱ ሁሉ ለህዝብ መብት ሲሉ በእስርና በግርፍ የሚማቅቁ በርካቶች እንዳሉ ነው።

በርግጥ ወንድሜ ነው ላጣው አልፈልግም። በዚህ መልኩ ባጣው ግን ኩራት እንጂ ጸጸት ወይም ቁጭት አይሰማኝም። አንዳርጋቸው የቆመለትን ዓላማ አውቃለሁ።ስለሚሰራው ስራም ግንዛቤ አለኝ ብዬ አስብ ነበር :: አሁን አንዳንድ ይሰራቸው የነበሩ ነገሮችን ስሰማ ግን ስለ አንዳርጋቸው ብዙ የማላውቀው ነገር እንዳለ እየተሰማኝ ነው። የበለጠ ባወቅኩት ቁጥር ከዚህ ሰው ጋር ህይወቴ መገናኘቱ አኩርቶኛል። ባጠቃላይ ስለአንዳርጋቸው ሳስብ ፤ ማሰብ የምፈልገው ስቃይ ውስጥ መሆኑን ሳይሆን የሰራውን አኩሪ ስራና ስቃዩም ለነገ ብሩህነት የተከፈለ ዋጋ እንደሆነ ነው:: እህትነቴ ሊፈጥርብኝ የሚፈልገውን የሃዘን ድባብ የማስወግደውም ስለ ስራው እንጅ ስለ ስቃዩ ባለማሰብ ነው።በደረሰበት ነገር ከማዘን ይልቅ በስራው መኩራትን ነው የምመርጠው።

**<u>አሻራ፦</u> አሁን ደግሞ ወደ ኋላ ልመልስሽ ነው። ወደ 1997 ዓም። አገዛዙ የምርጫውን ውጤት አልቀበል ብሎ ጭራሹኑም ህዝብ የመረጣቸውን የቅንጅት አመራሮች ሰብስቦ ማሰሩ ይታወሳል። አቶ አንዳርጋቸውም እስርና ድብደባ ተፈጽሞባቸው ነበር። ታዲያ አንቺም በዚያው ሰሞን ከምትኖሪበት ሃገር ወደ ኢትዮጵያ በመሄድ አቶ አንዳርጋቸውን በዝዋይ እስርቤት እየተመላለሽ ስትጠይቂ ከርመሽ እንደነበር ነው የተረዳነው። እስኪ አሁን ለአንባቢያን የዚያን ወቅቱን ትውስታሽን አካፍይልን?**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፦</u>** ልክ ነው! አንዳርጋቸው መታሰሩን ስንሰማ እኔና አንዱ ወንድሜ ወደ ኢትዮጵያ ሄደን ነበር። ትዝ ይለኛል እሁድ ቀን ነበር የገባነው:: መታሰሩን እንጂ የት እንደታሰረ ምንም ልናውቅ ባለመቻላችን ስንጠያይቅ ዝዋይ ሳይወስዷቸው አይቀርም የሚል ነገር ሰማን:: ወንድሜ ብቻውን ወደ ዝዋይ ለመሄድ ነበር ያሰበው። ብቻህን አትሄድም ብዬ አብረን ለመሄድ ተነሳን።

በነገራችን ላይ በዛን ግዜ ጠቅልዬ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት እየተዘጋጀሁ ስለነበር ልጄ ቀድማ ሄዳ እዛው እየተማረች ነበር። እንግሊዝ ሃገር ዜግነት መለወጥና ፓስፖርት መያዝ እየቻልኩ ሀሳቡ ራሱ ጥሩ ስሜት ስላልፈጠረብኝ አላደረኩትም ነበር። እስከዚያን ጊዜ ድረስ እኔም ልጄም በኢትዮጵያ ዜግነት ነበር የቆየነው። ያንን ካየሁ በኋላ ግን ወዲያውኑ ሃሳቤን ለውጥኩ።

ወደ ጥያቄህ ልመለስና፦ ዝዋይ እንደደረስን እስር ቤቱ የት እንደሚገኝ ጠይቀን አቅጣጫውን ነገሩን። አካባቢውና ሁኔታው ያስፈራ ስለነበር እንዲሁ በመኪና እያየነው እንለፍ ብለን ወደ እስር ቤቱ አቅጣጫ ነዳን ። በሩ አካባቢ ስንደርስ ግን አይቶ ማለፍ አላስቻለንም ወረድን። ተጠግተን ፖሊሶቹን ጠይቀን። መግቢያ በሩን አሳዩን:: ባጋጠሚ እስረኛ መጠየቅ የተፈቀደበት ቀን ስለነበር እንደማንኛውም ጠያቂ ተፈትሸን መጠበቅ ጀመርን። አንዳርጋቸው ግን ብቅ አላለም።በኋላ አንድ ብርቃየሁ የሚባል እስረኛ (ቅንጅት ጽ/ቤት ይሰራ የነበረ ፣አሁን ሆላንድ ያለ ይመስለኛል) ከውስጥ መጥቶ ማንን ልንጠይቅ እንደመጣን ጠይቆን ነገርነው። ብርቃየሁ ቤተሰቦቹ ያመጡለትን ስንቅ እንኳ ሳይቀበል ቆይ ልጥራላችሁ ብሎ ሄዶ ሳይመለስ በዛው ቀረ:: በኋላ ስንሰማ እንዳይወጣ ተከልክሎ ነው። ትንሽ ቆይቶ አንድ ፖሊስ መጥቶ ጠራን ። አንዳርጋቸውን ማየት እንደማንችልና አካባቢውን ለቀን እንድንሄድ አጥብቆ ተናገረን።እሺ ዛሬ ካልተቻለ መቼ ነው የሚቻለው? ብለን ስንጠይቀው፡ "መቼም!" ሲል መለሰልን። እኛም በሩ እስኪዘጋ ድረስ እዛው ቆይተን ሊዘጋ ሲል ወደ መጣንበት ለመመለስ ተነሳን። ስንገባ የሰጠነውን መታወቂያና ሞባይል ልንቀበልና ልንሄድ ስንል አንዱ ከኋላችን መጥቶ ትፈለጋላችሁ መሄድ አትችሉም ብሎ ወደ ውስጥ ሊያስገባን ሞከረ:: በዚህ ግዜ እዛ የነበረው ህዝብ አትወስዷቸውም ብሎ ታግሎ አስጣለን። በኋላም መታወቂያችንን መለሱልንና ወደ አዲስ አበባ ሄድን።

በማግስቱ ማክሰኞ ቀን ከጠዋቱ 5 ሰአት ገደማ ወንድሜ ደውሎ ዛሬውኑ ሃገር ለቀህ ውጣ ብለውኛል ሲል ነገረኝ:: የሚገርምህ ወንድሜን ዛሬውኑ ውጣ ሲሉት፤ እሱም መልሶ፦ “ነገ ማለትም እሮብ ወደ ሎንዶን በረራ ስላለና መመለሻ ትኬትም ስላለኝ ነገ ለምን አልወጣም?” ብሎ ይጠይቃቸዋል። የለም ዛሬውኑ ወደ ኬንያ መውጣት አለብህ! 8 ሰአት ተኩል ላይ ወደ ኬንያ በረራ ስላለ መሄድ አለብህ ብለው ድርቅ ያለ ትእዛዝ ይሰጡታል። ዋናው የሚገርመው በመሳሪያ አጅበውት ነበር የኬንያውን ትኬት እንዲገዛ ያስገደዱት።በኋላም መቼም ከመሃላቸውም ቢሆን ጥቂት ማስተዋል የተረፋቸው አይጠፉምና፤ ሃገር

*ወደ ገጽ 33 ዞሯል*

# ቆይታ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታናሽ እህት .....

*ከገጽ 32 የዞረ*

ለቀህ ውጣ ካልነው በራሱ ግዜ ትኬቱን ገዝቶ ይውጣ እንጂ በመሳሪያ ማጀብ ምን ያስፈልጋል? ብለው ለቀቁትና ተሯሩጠን ትኬቱን ገዝተን ሸኘነው።

**<u>አሻራ፡</u> ላቋርጥሽና በቅርቡ ታላቅ እህታችሁን ወይዘሮ ብዙአየሁ ፅጌንም በፓስፖርታቸው25 የተሰያዩ ገፆች ላይ ፈርማው እንዳይመጡ የሚል የዲፖርቴሽን ማህተም መትው ከሃገር እንዳስወጧቸው ተገልጿል። በቤተሰባቸሁ ላይ አስገድዶ ከአገር ባሰቸኳይ የማስወጣት እርምጃ ሲወሰድ ይህ ለሁለተኛ ግዜ መሆኑ ነው?**

<u>ወ/ሮ እሰከዳር፡-</u> አዎ! የእሷ ለሁለተኛ ግዜ ነው!

**<u>አሻራ፡</u> ይቅርታ ካቆምሽበት ቀጥይልን፡**

እሱን ወደ ኬንያ ከሸኘሁ በኋላ እኔ ወደ ዝዋይ ሄድኩ፡፤ዝዋይ ወደ ነ0 ሰአት አካባቢ ይመስለኛል የደረስኩት።ወዲያው ወደ እስር ቤቱ ሄጀ ሰልፌን ያዝኩ። የምትጠይቀውን እስረኛ ስም እያስመዘገብክ ነው የምትገባው።እኔም አንዳርጋቸው ጽጌ ሃብተ ማሪያም ብዬ ሳስመዘግብ የሚጽፈው ልጅ ቀና ብሎ አይቶኝ ቆይ አንዴ ጠብቂ ብሎኝ ሄደ። ወዲያው ተመልሶ መጥቶ በቃ ዛሬ ዘግተናል ብሎ ከለከለኝ፡፡ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

በማግስቱ እሮብ እንደገና ተመልሼ ሄድኩ።የዛን ቀን ማንም እስረኛ አይጠየቅም ብለው ከልክለው ስለነበር ምንም ማድረግ አልቻልኩም፡፡ እዛው እንዳለሁ ግን ቅዳሜ መጠየቅ እንደሚቻል ሰማሁ፡፡ ቅዳሜ ተመልሼ ሄጀ አየሁት። ከቤተሰብ ለመጀመሪያ ግዜ ያገኘሁት እኔ ነበርኩ። የነበረበት ሁኔታ ጥሩ አልነበረም።

ስለ መደብደቡ ሰምተን ስለነበር መጀመሪያ የጠየቅኩትም ስለዛ ነው። የሰጠኝ መልስ " እንኳን እኔን ወላጆቻቸው ቆሎ ሸጠው ያሳደጓቸውን ህጻናት ሲገርፉና ሲደበድቡ ነው የሚያድሩት፤ የኔ ምን ያስገርማል?" የሚል ነበር። ይህን መሰል ተመሳሳይ መልስ ለሌላኛውም እህቴ እንደሰጠ ሰምቻለሁ።

ስለ ተመሰረተበት ክስ ስጠይቀው " ክሱ ባንክ ለመዝረፍ ሞክረሃል የሚል ነው።እዚህ በር ዘግተው የሚጠይቁኝ ግን ስለጻፍኩት መጽሃፍና ላፕቶፑ ላይ ስላለ ነገር ነው። ላፕቶፑን ከፈለጋችሁ ውሰዱት፤ ፓስ ዎርዱንም እንካችሁ ለመስበር አትቸገሩ። ውስጡ ያለው ዶክመት ብታነቡት ይጠቅማችኋል። ብዬ ሰጥቻቸዋለሁ" ነበር ያለኝ፡፡

ሌላው የሚያስቅው ነገር ...የሚያሳዝን ልበለው? በማግስቱ እሁድ ልጠይቀው ስሄድ መጽሃፍ አምጭልኝ ብሎኝ ስለነበር አሁን የማላስታውሳቸው በርከት ያሉ መጽሃፍት ይገፍለት ሄድኩ። መጽሃፎቹን አይተው የፖለቲካ መጽሃፍ አይገባም ብለው ከለከሉኝ።

እኔም መልሼ በስርቆት ነው የተያዙት እያላችሁ የፖለቲካ መጽሃፍ የምትከለክሉት ለምድነው? ወይስ የፖለቲካ እስረኞች ናቸው ብዬ ትንሽ ብጥብጥ ተነሳ። በኋላም አንዱ አለቃቸው መጥቶ መጽሃፎቹ የፖለቲካ አለመሆናቸውን እያጣራችሁ አስገቡ ብሎ አዘዘ።የእንግሊዘኛ መጽሃፍት ስለነበሩ መለየቱ አሰቸጋሪ ሳይሆንባቸው አልቀረም መሰለኝ ውስጣቸው ወረቀት አለመኖሩን ብቻ ገላልጠው አይተው አስገቧቸው።

*ወደ ገጽ 35 ዞሯል*

# ከፕ/ር አለማየሁ ገብረ ማሪያም ጋር የተደረገ .....

*ከገጽ 30 የዞረ*

ይመስላል። ጥቁርና ጠይም ዜጎቹን እንደሁለተኛ ዜጋ ነው የሚያያቸው። በአንዳርጋቸው ቦታ ያለው አንድሪው ቶምሰን ቢሆን ኖሮ የብሪቲሽ መንግስት "ታላቅ ወንጀል" ተፈጸመብኝ ብሎ ያዙኝ ልቀቁኝ ባለ ነበር። ታጋቹን ዜጋውን ነጻ ለማውጣትም ማናቸውንም ጥረት ማድረጉ አይቀርም ነበር። ለነገሩ የመንም ሆነች በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ የእንግሊዝ መንግስት ጉዳዬ በሚለው ዜጋ ላይ ቢሆን ኖሮ ይህን መሰሉን ተግባር አይፈጽሙትም ነበር።

**<u>አሻራ፡-</u> የኢትዮጵያዊያኑስ እንቅስቃሴ በምን መልኩ እንዲቀጥል ይመክራሉ?**

<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>ማናቸውም ነጻነት ናፋቂ ነኝ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ በአገሪቱ ዲሞክራሲና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ድምጹን የማሰማትና የበኩሉን አስተዋጽዖ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት። በእኔ በኩል ለውጥ ለማምጣት የተሻለው መንገድ ሰላማዊ ትግል ነው ስል ቆይቻለሁ። በጫካ ትግል ውስጥ ጭካኔና ያልሰለጠነ ባህል ሊጎለብት ይችላል። በርግጥ ብዙ ሰዎች አገዛዙን በሰላማዊ ትግል ማስወገድ ስለመቻሉ ጥርጣሬ እንዳላቸው አውቃለሁ። የሰላማዊ ትግል ከፍተኛ የሆነ አደረጃጀት፣ ዲሲፕሊንና እውቀት ይጠይቃል እንጂ የማይቻል አይደለም። ጋንዲ ብሪቲሽን ያሸነፈው በሰላማዊ ትግል እንደነበርም ማስታወስ እፈልጋለሁ። በህንድና በተለያዩ የአፍሪካ አገራት የነበረው የብሪቲሽ አገዛዝ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የስልጣን ኮርቻው ላይ እንደተፈናጠጠው አገዛዝ ሁሉ በጭካኔው የሚታወቅና የሚፈራ ነበር። ከመሸነፍ ግን አልዳነም። ይሁንና በሰላማዊ ትግል የሚገኘው ለውጥ ባንድ አዳር የሚጨበጥ አይደለም። ጭራሽም ለውጡ ከእያንዳንዱ ሰው የሚጀምርና ወደ መላው ማህበረሰብ የሚስፋፋ ዓይነት ነው። ትግሉ ይቀጥላል። ትኩረቱ ኢፍትሀዊነትን፣ ሙሰኝነትንና የሰብአዊ መብቶች ረገጣን በመቃወም፤ የብሄርም ሆነ የጎሳ ልዩነት ሳይደረግበት ሁሉም ዜጋ ሰብአዊ ክብር እንዲያገኝ በማለም የሚደረግ መሆን ይኖርበታል። ጥያቄውም በቅርብ ርቀት ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ይመጣል ወይስ አይመጣም የሚለው አይደለም። ምን ዐይነት ለውጥ የሚለው እንጂ።

**<u>አሻራ፡-</u>የዲፕሎማቲኮች ያለመከሰስ መብት ወንጀል ለፈጸሙ አምባገነን ባለስልጣናት ከለላ የሚሰጠው እምን ድረስ ነው?**

<u>ፕ/ር አለማየሁ፡-</u>ያለመከሰስ ዲፕሎማቲክ መብት (Diplomatic Immunity) ከለላ የሚሰጠው ተመድበው በሚሰሩበት አገር ውስጥ ወንጀል ፈፅመው ለሚገኙ ዲፕሎማቶች ነው።

ለምሳሌ አንድ ያለመከሰስ ዲፕሎማቲክ ከለላ የተሰጠው(ጣት) የአገዛዙ ዲፕሎማት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወንጀል ቢሰራ(ብትሰራ) አገዛዙ ከለላውን ካልገፈፈው በቀር የመባረር እንጂ የመከሰስ ዕጣ አይገጥመውም(ማትም)። ያም ሆኖ ግን በሰብዓዊነት ላይ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች የሚሰጥ የዲፕሎማቲክ ከለላ የለም። ለዚህም ነው የኬንያው ፕሬዘዳንት ኡሁሩ ኬንያታ ክስ በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት (**ICC**) በመታየት ላይ ያለው። አንድ ቀን ደግሞ የሱዳኑ ኦማር አልበሽር በዚሁ ችሎት ቀርቦ መታየቱ አይቀርም።

**<u>አሻራ፡-</u>የሙበት ረገጣ ተፈጽሞባቸው ወደ ምዕራብ አገር የተሰደዱ ግለሰቦች አሁን በስልጣን ላይ ያሉትን በደል የፈጸሙባቸውን ሹማምንት መክሰስና መፋረድ የሚችሉት በምን የህግ አግባብ ነው?**

*ወደ ገጽ 37 ዞሯል*

## .... ታማኝ በየነ

### ስለ አቶ አንዳርጋቸው ....? ከገጽ 18 የዞረ

ማዛጋት ትኮርጃለህ?.....(ሳቅ) እሳቸው እኮ የአቶ መለስን ማዛጋት ሁሉ እየኮረጁ ነው! (ሳቅ).....! እኔ እንደ መዝናኛና ኮሜዲ ሾው ነው የማያቸው። ከዚህ ባለፈ አላያቸውም። አይ የግድ ይሰራባቸው ከተባለም ለቁምነገር ሳይሆን ለትርፍ ግዜ መዝናኛ ሊሰራባቸው ይችላል።ከዚያ ውጭ ግን በሳቸው ላይ ግዜ ማጥፋት ያለብኝም ያለብንም አይመስለኝም።

ደግሞ ምን መሰለህ..? እኔ ጠ/ሚ/ር ስትለኝ የሚመጣብኝ ምስል እንደ አክሊሉ ሃብተወልድ አይነት ሰው ነው።። ....እና በዚህ ስም ኃይለማሪያም ደሳለኝ ሲጠራበት .....(ፋታ) ልክ አይሆንም።

***አሻራ፦*** **የወያኔን ከፍተኛ ባለስልጣናት በስልክም ቢሆን ለማግኘት ሞክረህ አታውቅም? ሞክረህ ከሆነ ውጤቱ ምን ነበር?**

***ታማኝ፦*** እምምም.. አዎ! አንድ ሶስት ግዜ ሞክርያለሁ። አንዴ የቤንሻንጉል መፈናቀል ጊዜ ...ሌላው ደግሞ አርሲ ውስጥ ሙስሊሞች የተገደሉ ጊዜ ይመስለኛል...አንዱን ዘነጋሁት። ብቻ ለ3 ጊዜ ያህል አቶ በረከት ጋ ደውዬ ነበር።መጀመሪያ የደወልኩ ጊዜ አነሳ፤ ጤና ይስጥልኝ ከአሜሪካ ነው የምደውለው አልኩት። "ማን ልበል? " አለኝ። አይ እኔ የመንግስትዎ ተቃዋሚ ነኝ፤ ነገር ግን አሁን እየሆነ ባለው ጉዳይ መረጃ ይሰጡኝ እንደሁ ብዬ ነው የደወልኩት አልኩት።

እሱም "ማንነትክን ካልገለጽክልኝ ምንም መረጃ መስጠትም ሆነ ማውራት አልችልም" አለኝ።

መልሼም፦ማንነቴን ከነገርኩዎት አያናግሩኝም አልኩት።

"ግዴለህም አናግርሃለሁ!" አለኝ።

ታማኝ በየነ ብዬ ሳልጨርስ ስልኩ ላዬ ላይ ተዘጋ።።በሌላም ጊዜ የሆነው እንዲሁ ነው።። ታማኝ በየነ ነኝ ስለው ስልኬን ይዘጋዋል።

***አሻራ፦*** **ለማነጋገር ፈቃደኛ ቢሆን ኖሮ በምን አይነት ስሜት ነበር የምታናግረው? ምንስ ነበር የምታናግረው?**

***ታማኝ፦*** ለነገሩ በተለይ በመጀመሪያ የደወልኩለት ጊዜ አልተዘጋጀሁም ነበር።። አሁን ስልኩን ሲያነሳ እንዴት ብዬ ነው የማናግረው? ንዴትም ቁጣም ፤ እልህም ይኖራል እና እንዴት እንደማናግረው አላውቅም ነበር።። ሰዎችም አብረውኝ ነበሩ። ለማንኛውም የምለውን ሳልል እሱም ስልኩን ዘጋው። ሁለተኛ ስደውል ግን አስቤበት ነበር።። ግን ምን ዋጋ አለው ስልኩ ይነሳና ራሴን ሳስተዋውቅ ይዘጋል።

***አሻራ፦*** **ምን ትለው ነበር ?**

***ታማኝ፦***ሁሌ ራሴን የምጠይቀውን ነገር ነበር ልጠይቀው የፈለኩት። እንደው መጨረሻቸሁ ምንድነው? እውነት እናንተ ሰዎች የምታደርጉትን ነገር ሁሉ የምታደርጉት የምር!! ለሃገርና ለህዝብ ጥሩ እየሰራን ነው ብላችሁ አምናችሁበት ነው? ልጆቻችሁን ትወዳላችሁ? ልጆቻችሁ ከሌሎች ልጆች ጋር በፍቅር እዲኖሩ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ብዬ ጠይቄ ከራሳቸው አንደበት ብሰማው ፈልጌ ነበር አልሆነም ዘጋብኝ።።

***አሻራ፦*** **ወደ ወቅቱ ጉዳይ ልመልስህ፦ የአቶ አንዳርጋቸው መያዝ ኢትዮጵያዊውን ሁሉ አስቆጥቷል።። በወያኔ መንግስት ላይ ያለው ተቃውሞና ለለውጥ ያለው ተነሳሽነት ከመቼው ጊዜ በተለየ ጠንክሯል። ይህን ተነሳሽነት ወደ ውጤት ለመለወጥ ምን መደረግ አለበት ትላለህ?**

[ወደ ገጽ 36 ዞሯል]

## አሻራ ...

[ከገጽ 17 የዞረ]

ነፍሰ-ጡርዋ ሰርካለም የተከሰሰችው ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በሃይል ለመናድ እና ለማፍረስ፣ ጥላቻን የምታስፋፋ፣ ጥርጣሬን የምትነዛ... ተብላ ነበር። በ"ምህረት" ከእስር

እንደተፈታች ወደ ኬንያ ተሰደደች። በኋላም ሀገር ሰላም የሆነ ሲመስላት ከስደት ተመለሰች። ይህች ወጣት እትብትዋ ወደተቀበረባት ሃገርዋ ብትመለስም እንደዜጋ የመኖር ዋስትናዋ ግን በአንባገነኖች መዳፍ ስር ሆነ። በኑሮዋ እና በትዳርዋ ዙርያ ካለፈው የባሰ ችግር መጣባት። ባለቤትዋ እስክንድር ነጋ በሽብርተኝነት ተከሶ በፍርደ-ገምድል ዳኛ ለአመታት ተፈረደበት። ቤት ንብረታቸውም በግፍ ተቀማ። ከዚህ በኋላ በመኖር እና ባለመኖር የሚደረግ ምርጫ ውስጥ መግባት ግድ ሆነባት። እናም ባለቤትዋን ወህኒ ቤት ጥላ ዳግም ተሰደደች። እስዋም ሆነች በሰቆቃ የተወለደ ልጅዋ በመንገድ ከመወርወራቸው በፊት ያላቸው አማራጭ ይህ ብቻ ነበር። የሚወዷት ሃገራቸውን ጥለው ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ስደተኛ ጋዜጠኞችን ተቀላቀሉ።

በስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ፍርሃት ውስጥ እንዳሉ ግልጽ ነው። ቢጋዜጠኛ የሚናድ ህገ-መንግስት ይዘው ስንት አመት ሊዘልቁ እንደሚችሉ አናውቅም፤ አሁንም ታዲያ ጋዜጠኞችን ሲያስሩ ይህንኑ ዘፈን ይደጋግሙታል። 99.7 በመቶ በህዝብ የተመረጠ መንግስት መራጩን ሕዝብ መፍራት አልነበረበትም። ስላቅ ነው። ይህ ቀልዳቸው የህዝቡን ንቃተ-ህሊና ዝቅ አድርጎ ከመመልከት የሚመጣ ይሁን እንጂ መልሱ ቀላል ነው። እሱንም ናፖሊዮን ቦናፓርት ብሎታል። ከሺ ሳንጃ አንድ ጋዜጠኛ ያስፈራል። የጭቆና እና የአፈና ስርዓት ገንብቶ ለረጅም አመት ይቆየ አንባገነን በታሪክ አልታየም። የፈቀደውን መምረጥ የሚችልን ህዝብ አዲስ ዘመንን ብቻ እንዲያነብ መምከራቸው ብቻ አይደለም ንቀታቸው፤ የፍትህ ስርዓቱን ለበቀል የሚዘረጋ እጃቸው አድርገው ነጻውን ፕሬስ ለማጥፋት ሲጠቀሙበትም እጅግ ያንገበግባል። የህግ የበላይነትን እንዲህ እያደረጉ ናቸው።

ኢሕአዴግ የፕሬስ ነጻነትን ለህዝቡ እንዳንናጸፈ ይመጻደቃል። ይህ ስህተት ነው። መናገር፣ ሃሳብን በነጻነት መግለጽ፣ መጻፍ፣ ... ወዘተ መብት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ጸጋ እንጂ አንድ ስርዓት የሚያጎናጽፈን ጉዳይ አይደለም። በሌላ በኩል ደግሞ ይኸው ስርዓት እነዚሁኑ መብቶች እየጨፈለቀ እነሆ ሃያ ሶስት አመታትን ዘልቋል። እጅግ የሚያሳዝነው ይህ ስርዓት ለፈጸመው ለዚህ ሁሉ በደል ለሸለማት መብቃቱ ነው። ልማታዊው አርቲስት ሰራዊት ፍቅሬ በአርቲስቶች ስም ለሚቹ ጠቅላይ ሚ/ር የወርቅ ብዕር ነበር ያበረከተላቸው። ብዕር ትልቅ ትርጉም አለው። ብእር የሚሸለም ሰው ለፕሬስ ክብር ያለው፤ ፕሬስን የሚያከብር ሰው ነው። ሰራዊት የወርቅ ብዕር እንዲሸልም አርቲስቶች አልወከሉትም ነበር።

ይህንን ሲያደርግ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኞች እስር ቤት ውስጥ ይንገላቱ ነበር። ሰራዊት ይህንን ሲያደርግ የአለም አቀፍ ህብረተሰብ ጠ/ሚኒስትሩን የፕሬስ አፈና በእጅጉ ያወግዝ ነበር። እንደ ሰራዊት ያሉ ሃላፊነት የጎደላቸው ሰዎች ብዙ አይደሉም። ለህሊናቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ሲሉ እንዲህ አይነት ስራ እየሰሩ በሰው በቁስል ላይ እንጨት ይሰድዳሉ። ታዲያ እንደነዚህ አይነቶቹ አድርባዮችም ለፕሬሱ መጥፋት ሚናቸው ቀላል አይደለም። የማያልፍ የለም። ሁሉም ያልፋል። መንግስትም እንደ አንሶላ ተጠቅልሎ ይሄዳል። ይህ ቀን አልፎም ለትዝብት ያበቃናል። ማን ነበር "ፕሬስ የሌለው መንግስት ከሚኖረን መንግስት የሌለው ፕሬስ ቢኖረን እንመርጣለን።" ያለው? ያለ ፕሬስ የሚኖር ህዝብ በጨለማ የሚኖር ህዝብ ነው። ያለ ነጻ አስተሳሰብ እና ያለ ነጻ ፕሬስ፣ እድገት ይመጣል ማለት አሁንም የህዝብን ንቃተ-ህሊና ዝቅ አድርጎ መመልከት ይሆናል።

# ቆይታ ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታናሽ እህት .....

ከገጽ 33 የዞረ

በነገራችን ላይ ጥበቃ ላይ የነበሩት ፖሊሶች በአብዛኞች የህዝብ ወገንነት የሚሰማቸው ነበሩ። አይዟችሁ ይሉን ነበር። ከጥቂቶቹ .. በስተቀር።

እኔም ከነኚህ ከጥቂቶቹ ጋር በየማዜው እጋጭ ነበር። የማይሆን ነገር ሲናገሩ ዝም አልላቸውም። "ተሳዳቢዋ" የሚል መጠሪያ ሰጥተውኝ ነበር። አንዴ እንዲያውም አንዳርጋቸው " ከጠባቂዎቹ ጋር የምትጋጪ ከሆነ ባትመጪ ይሻላል። እነሱ ታዘው ስራቸውን እየሰሩ ነው። ከነሱ ጋር መጨቃጨቅ ዋጋ የለውም " እንዳለኝ አስታውሳለሁ።

በዛ ወቅት የማስታውሰው በተለይ ወጣቱ በግልጽ ነበር የሚቃወማቸው፡ እኔ በምጋጭበት ግዜ ልቀቋት እያሉ በድፍረት ነበር የሚጋፈጡት። በግዜው እዛ ይመጡ ከነበሩት ውስጥ ብዙዎቹን አነጋግሬያቸዋለሁ። በቤተሰቦቻቸው ላይ የተፈጸሙ በጣም የሚዘገንኑ ግፎችን ይነግሩኝ ነበር። ብዙ ብዙ ያለተነገሩ ግፎች ተፈጽመዋል።

**<u>ሰሻራ፡</u> አቶ አንዳርጋቸው በግል ስለደረሰባቸው ድብደባ ዘርዘር አርገው የገለጹልሽ ነገር የለም?**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፡-</u>** አዎ! ስለድብደባው መጀመሪያ የሰማሁት ነገር የደበደቡት እቤት መጥተው ሲወስዱት ነው የሚል ነበርና መቼ ነው የደበደቡህ ሲያመጡህ ነው ወይስ እዚህ ከገባህ በኋላ ብዬ ጠይቄው ነበር።የነገረኝ ሁለት እጁንና እግሩን አስረው እንደ ደበደቡትና ለምን ትደበድቡኛላችሁ ብሎ ሲጠይቃቸው፤ ታዘን ነው፡ እንዳሉት ነበር። ባጠቃላይ የዝዋዩ ጥየቃ ይህን ይመስል ነበር።

ከዚያ የፍርድቤቱ ጉዳይ ቀጠለ።ላሳጥረውና እንዲለቀቁ ተወስኖ የእስረኛ ቤተሰብ ከፍርድቤት የመፈቻ ወረቀት ይዞ በመሄድ የታሰረበትን ቤተሰቡን ሲያስፈታ፤ እኔም የአንዳርጋቸውን መፈቻ ይዤ ሄድኩ። ይሁንና ወርቀቱን ከሰጠኋቸው በኋላ ጠፋ ብለው ሌላው በተፈታበት ቀን ሳይሆን በማግስቱ ነበር የተፈታው።

**<u>ሰሻራ፡</u> ወደ ወቅቱ ጉዳይ ልመልስሽ፡- ሰሞኑን በኢትዮጵያ የእንግሊዝ መንግስት አምባሳደር አቶ አንዳርጋቸውን በእስር ቤት ሄደው እንዳገኟቸው ወይም እንደጎበኟቸው ተገልጿል። ዝርዝር ነገር ባይኖርም። ይህን ዜና እንዴት አየሺው? የእንግሊዝ መንግስት ዜጋውን ከዚህ መሰል ጥቃት በመታደግ ረገድ ያለበትን ሃላፊነት እየተወጣ ነው ትያለሽ? ካልሆነስ ምን ማድረግ አለበት..?**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፡-</u>** በመጀመሪያ አምባሳደሩ አንዳርጋቸውን ጎበኘ የሚለውን ዜና ስሰማ የተሰማኝ ስሜት ፤ ጥሩ ነገር እንደሆነ ነው። የጉብኝቱን ዝርዝር ነገርም ጠብቄ ነበር። በኋላ ግን "ጎብኝተነዋል ደህና ነው።" በሚል አጭር ምላሽ ሲዘጋ ደግሞ የመጣብኝ ሁለት ሃሳብ ነው። አንደኛው፡- ምናልባት ግፊትና ጫናው ስለበዘባቸው ለማለት ያህል ጎበኘነው አሉ እንጂ በትክክል አልጎበኙትም የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው፡- ደግሞ ጎብኝተውት ከሆነም አንዳርጋቸው ላይ ያዩት ነገር ጥሩ እንዳልሆነና ምናልባትም የአካል ጉዳት አድርሰውበት ሊሆን እንደሚችል ነው። ከሁለት አንዱ ካልሆነ በስተቀር ጎበኘነው ብለው ዝርዝር ነገር ከመናገር ሊቆጠቡ የሚችሉበት ሌላ ምንም ምክንያት አይታየኝም። ለሁሉም ግን እግዚአብሄር ይጨመርበት እንጂ የአምባሳደሩ ድፍን ያለ መልስ ምንም አልተዋጠልኝም።

የእንግሊዝ መንግስት የሚጠበቅበትን አድርጓል ወይ? ላልከው መልሴ አላደረገም የሚል ነው። ቢያንስ ቢያንስ ዜጋ እንደመሆኑ የኢትዮጵያ የፍትህ ስርዓት ሰራም አልሰራም የህግ አማካሪ(ጠበቃ) እንዲኖረውና በቤተሰቡ እንዲጎበኝ የማስደረግ ኃላፊነት ነበረበት፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ አቅምም ችሎታም ያለው መንግስት ነው።

**<u>ሰሻራ፡</u> ካልተሳሳትኩ የልጅሽ ስም "ፍትህ" ነው አይደል?ልጅሽ የአቶ አንዳርጋቸውን ነገር ሰምታ ይሆን? ከሰማችስ እንዴት ተቀበለቺው?**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፡-</u>** አዎ ፍትህ ነው የምትባለው። መቼም ኢትዮጵያ ያለው ነገር እያስገደዳቸው የልጆቻቸውን ስም በሀገር ቤት ያለውን ሁኔታ እንዲያመላክት እያደረጉ ስም ያወጡ ብዙዎች ናቸው፡፡ እኔም ከነዚያ አንዷ ነኝ፡፡ የፍትህን እጦት ለማመልከት ስል ልጄን ፍትህ(ጀስትስ) ነው ያልኳት፡፡

ልጄና አንዳርጋቸው የጠበቀ ፍቅር ነው ያላቸው፡፡ ባጋጣሚ ተይዞ ኢትዮጵያ መግባቱ ይፋ በሆነበት ቀን በጣም እየጮህኩ በስፒከር ከቤተሰብ ጋር ሳወራ ሌላ ክፍል ሆነ ሰምታ ወደ አጠገቤ መጣች። ስልኩን ከጨረስኩ በኋላ ምንድነው የሆነው ? ብላ ጠየቀችኝ፡ ነቲንግ ... ብዬ ስመልስላት አማርኛ ብዙ ባትናገርም በደምብ ስለምትሰማ ያልኳትን አልተቀበለችም። "ላዛኛ ዱድ ምን ሆኗል? "ብላ ጠየቀቺኝ ። (አንዳርጋቸው እኛ ጋ በመጣ ግዜ ላዛኛ ስለሚሰራላት፤ ላዛኛ ዱድ ብላ ነው የምትጠራው) በየግዜው ኢሜል ስለሚደራረጉ ደህንነቱን በዛ ታውቃለች። አንዳንዴ በርሃ ሲሄድ ይመስለኛል መልስ ሳይሰጣት ይቆይና ሲጽፍ፡ ወይ ሲደውል የት ጠፋህ ብላ ትጠይቀዋለች፡ እሱም "ፑፍ" ሄጂ ነበር ይላታል። አሁንም ፑፍ ሄዶ ይሆናል የሚል ነበር ግምቷ ።ይሁንና ጥያቄዋን ሸሽት ውጭ ቆይቼ ስመጣ እድሜ ለጉግል ሁሉንም አውቃ ጠበቀቺኝ።

በኋላም ከኢንተርኔት ያነበበቺው ነገር እውነት መሆኑን እንዳረጋግጥላት ጠየቀቺኝ፤ የግዴን ቁጭ አድርጌ አስረዳኋት። የሚገርምህ "አንቱ በመሆኑ እኮራለሁ" ነው ያለቺኝ።

ከሰማችበት ግዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ለፕሬዘዳንት ኦባማ ኢሜል እያደረገች ትገኛለች ።" ምንም አይሆንም። ምንም እንደማይሆን ስሜቴ ይነግረኛል። በቀን ሶስቴ እጻልያለሁ።." እያለች እኔንም ታጽናናኛለች።

**<u>ሰሻራ፡</u> በመጨረሻ፡- ኢትዮጵያዊያን አቶ አንዳርጋቸውን ከሚጥዱበት ችግር ለመታደግ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? የእንግሊዝ መንግስት ዜጋውን ነጻ እንዲያወጣ ጫና በመፍጠሩ ረገድስ ምን መሰራት አለበት ትያለሽ? በጥያቄ ያላነሳነው ነገር ካለ አክለሽ ብናጠቃልል።**

**<u>ወ/ሮ እሰከዳር፡-</u>** በኢትዮጵያዊው ወገን እስካሁን እየተደረገ ያለው ራሱ እጅግ በጣም በጣም የሚያስደንቅና ማንም በኢትዮጵያዊነቱ እንዲኮራ የሚያደርግ ተግባር ነው። በእንግሊዝ መንግስትም ላይ በተያዘው መልክ ጫናው መቀጠል ያለበት ይመስለኛል። እኔ ግን ችግሩን ከሃገራዊ ችግርም ሰፋ ባለ አህጉራዊ ችግር አድርጌ እየተመለከትኩት ነው፡፡ የአፍሪካ መሪዎች በኦባማ ጋባዥነት አሜሪካ በመጡበት ግዜ ያስተዋልኩትም ይህንን ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ ተመሳሳይ የሰባዊ መብት ረገጣና የዲሞክራሲያዊ መብት ችግር ያሉባቸው አገር ዜጎች ትግላቸውን በጋራ የሚያደርጉበት መንገድ መፈለግ ያለባቸው ይመስለኛል።

ይህን አስመልክቶም አንዳንድ ስራዎች ለመጀመር እያሰብን ነው። ባጠቃለይ የሰብአዊ መብት መከበር፤ የፍትህና የዲሞክራሲ ጥያቄዎች እስካልተመለሱ ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ባመነበት መንገድ ትግሉ መቀጠል እንዳለበት ነው ልገልጽ የምሻው፡፡ ዛሬ አንዳርጋቸው ብቻ ሳይሆን በሺህ የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በተመሳሳይ ችግርና ስቃይ ውስጥ ይገኛሉ። ስለዚህ ሁሉም ዜጋ እንደ ዜጋ የሚጠበቅበትን ማድረግ አለበት እላለሁ። እስካሁንም ግዜያቸውን፤ገንዘባቸውንና እውቀታቸውን ለዚህ መሰል የተቀደሰ ተግባር እያዋሉ ላሉ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ክብር ለነሱ ይሁን እላለሁ።ይህን ሃሳቤን እንዳካፍል ለተሰጠኝ እድልም ከፍ ያለ ምስጋና ላቀርብ እወዳለሁ።

## .... ታማኝ በየነ

### ስለ አቶ አንዳርጋቸው ....?

ከገጽ 34 የዞረ

***ታማኝ፦*** አንድ ነገር አለ! በአሁኑ ሰአት በሃገራችን እየሆነ ያለው ነገር በጣም የሚያስፈራ ነው፡፡ እኛ የምንቃወማቸው ስለምንጠላቸው አይደለም፡፡ የምንቃወማቸው እያደረጉ ያሉት ነገር በጣም የሚያስፈራ፤ ሃገራችን እንደ ሃገር ህልውና እንዳይኖራት፤ ህዝባችንም አብሮ መኖር እንዳይችል የሚያደርጉ ሥራዎችን እየሰሩ በመሆኑ ነው። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በተደጋጋሚ የዘር ቅራኔዎችን እያየን ነው። እገሌ ከዚህ ክልል እገሌ ከዚህ ክልል ውጣ እየተባለ ህዝብና ህዝብ እየተቂያቂያም እንዲሄድ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በጣም ያስፈራል፡፡

የህክምና ባለሙያ ባልሆንም አንድ ዶክተር ወደ ካንሰር ሊለወጥ የሚችል በጣም ከባድ የጤና ችግር ያለበትን በሽተኛ ፡ በአግባቡ መርምሮ ዘለቄታዊ መፍትሄ ይፈልግለታል እንጂ ህመም አስታጋሽ (ፔይን ኪለር) የሚሰጠው አይመስለኝም፡፡ የሃገራችን ወቅታዊ ጉዳይም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። ዛሬ አንድ ዘላቂ መፍትሄ ነገር ካላደረግን ችግሩ ሊድን ወደማይችል ካንሰርነት መለወጡ አይቀርም።

ኢትዮጵያን ሃገሬ የምንላት ሁሉ አትሌቶቻችን ባንዲራዋን ለብሰው ትራክ ላይ ሲያሟሙቁ፤ ማን በነዐ ሺህ ተሰለፈ ? ማን ለወርቅ ተስፋ አለው? .... እያልን እንጨነቃለን ። በውጤቱም እንደሰታለን። አሁን ደግሞ አትሌቶቿ ወርቅ ሲያስገኙላት የምንቦርቅላት ሃገር እንደ ሃገር መቀጠሏ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው። ይህ ደግሞ በኛና በኛ ትከሻ ላይ ብቻ ያረፈ ችግር ነው። ስለሆነም ከዚህ በፊት በተቃዋሚነት ሲንቀሳቀስ የቆየውም ሆነ ያልተንቀሳቀሰው ዜጋ፤ ብቻ ሁሉም ሁሉም ባመነበትና ታግሎ ያታግለኛል ባለው በአንዱ መስመር ገብቶ መታገል አለበት እላለሁ፡፡ ዛሬ አንዱ ተመልካች አንዱ ሯጭ የሚሆንበት ጊዜ አይደለም። ማንም ለምንም ጥሪ የሚያደርግበት ጊዜም አይደለም። ዛሬ አንድ ነገር ካላደረግን ለልጆቻችን የምናስተላልፈው "ነገ" የለም፡፡በዚህ ደረጃ ነው መታየት ያለበት የሚመስለኝ።

***አሻራ፦*** **በተነሳንበት እንቋጭና አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለህዝብ ነጻነት በጽናት ሲታገሉ ጠላት እጅ ወድቀዋል ፤ ህዝብስ ለሳቸውም ሆነ ለሃገር ነጻነት በመታገል ረገድ ምን ይጠበቅበታል ትላለህ?**

***ታማኝ፦*** አንዳርጋቸው በወያኔ እጅ እስከወደቀበት ጊዜ ድረስ የራሱንና የቤተሰቡን ህይወት ሰውቶ፤ በርሃ ገብቶ የቻለውን ሁሉ አድርጓል። የአንዳርጋቸው የትግል ጉዞ እዛ ጋ አብቅቷል። ዓለም ላይ ያሉ ሰውን የማስቃያ ቴክኒኮችን ሁሉ በእጁ ያስገባው የወያኔ መንግስት ደህንነት ባለፉት ሁለት ወራት አንዳርጋቸው ላይ ምን ሲፈጽምበት እንደቆየ ለመገመት የካፒቴን ተሾመ ተንኮሉን ቃለ ምልልስ ማድመጡ በቂ ይመስለኛል፡፡ አንዳርጋቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍሏል። እየከፈለም ነው።

የወያኔ መንግስትን ባህሪ መለስ ብለን ብናይ ሕዝብ የሚያከብራቸውን ሰዎች አዋርዶና አቅልሎ ለማሳየት የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ እንረዳለን፡፡

በአቶ አንዳርጋቸው መታፈን የተቆጣውን ህዝብ ተስፋ ለማስቆረጥ በተለመደው መልክ አቶ አንዳርጋቸውን አስገድደው በማናገር ሌላ የፊልም ቅንብር ለመስራት ተፍ! ተፍ! እያሉ እንደሆነ መረጃ ደርሶናል። ዋናው ቁምነገር ግን ህዝባችን ለዚህ መሰሉ የወያኔ ተደጋጋሚና አሰልቺ ህዝብን የማሳሳት፤ ጉምቱ የህዝብ ወኪሎችን የማዋረድ ሴራ አዲስ ስላልሆነ ምንም ይበሉ ምንም ይስሩ ፕሮፓጋንዳው ውጤት እንደማይኖረው አልጠራጠርም፡፡

ዋናው ቁም ነገር የነሱን ፕሮፓጋንዳ ማክሸፍ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ስንታገልለት የቆየነው ዘረኛውን መንግስት ከሕዝብ ጭንቃ ላይ የማውረድ ዓላማ በውጤት እንዲቋጭ ሁላችንም አንድ ሆነን መነሳት ነው!!!።

***አሻራ፦*** ስለ ጊዜህ በድጋሚ እናመሰግናለን!
***ታማኝ፦*** እኔም ስለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ

◆ ◆ ◆

## የመለስ ጂዮ-እስትራቴጂ "ትሩፋቶች" እና አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት ....

ከገጽ 37 የዞረ

በገበያ የምንገበየው ሸቀጥ ነው" በማለት ‹ጥልቅ› አመለካከቱን ለኢትዮጵያ ህዝብ ለመሸጥ ደጋግሞ ሞክረ። ዑስማን ሣሊህ በ1976ዓ.ም. የሻቢያ ካድሬዎችን ስለ ኤደን ሰላጤ በኤርትራና በጂቡቲ መሃል ያለውን ባቢል መንደብ የተባለውን የቀይ ባህር ደቡባዊ ጠባብ ሙተላለፊያ አስፈላጊነት በማስመልከት " አንዲት ታላቅ መርከብ በማስመጥ መተላለፊያውን ከጥቅም ውጭ ካደረግን ዓለም ለኤርትራ ጉዳይ ባንድ ጊዜ ጆሮ ይሰጣል" ብሎ ነበር። ለነገሩ የባቢል መንደብ ወሽመጥ ጠባብ መተላለፊያ መሆኑ ቢታወቅም አንድ መርከብ ስለሰመጠበት ከጥቅም ውጭ አይሆንም። እንኳን እሱ ፓናማ ካናልም በዚሁ ምክንያት መዘጋቱን እርግጠኛ አይደለሁም። ነገር ግን የሁለቱን መሪዎች አካባቢያዊ ጂዮ-ስትራቴጂካዊ አመለካከትን ያንጸባርቃል ብዬ ነው።

"ስለ ሙታኖቻችሁ ደግ ደጉን ዘክሩ" የምትለዋን ሃይማኖታዊ ብሒል በልጅነቴ የተዋሃደኝ ሙስሊማዊ አስተምህሮ አስታውሼ በ‹ባለራዕዩ› መሪ ውርስ ቅርስ ፈልጌ - ፈልጌ 'ደግ' ወይም መልካም ስራ በተለይም ለትውልድ ላወረሱት ጂዮ-ፖለቲካ መቅሰፍትን የሚያካክስ ሌጋሲ አጣሁ። አልታየኝ አለ። ለማንኛውም አፈር ይቅለለው !!

**ማስታወሻ**

ይቅርታና- ምስጋና ለአቶ ኤርሚያስ ለገሰ።ይቅርታው እሱን ሳላስፈቅድ "ትሩፋቶች" የተሰኘውን ቃል በመጠቀሜ። ምስጋናው ሊቃሉም ለመጽሓፉም ይሁንልኝ።

◆

ስለመጽሄታችን አስተያየት መስጠት ለምትሹ

**Email:** quatero@gmail.com
**Email:** abiywork@yahoo.com.au

# የመለስ ጂዮ-እስትራቴጂ "ትሩፋቶች" እና አዲሱ ቀዝቃዛ ጦርነት ....

*ከገጽ 28 የዞረ*

የምስረታ በዓሉን ባከበረበት ወቅት በፕሬዚዳንት ዑመር አልበሽርና በጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማሪያም ደሳለኝ ፊት ባሰሙት መሳጭ የምስጢር ገላጭ የጋራ ተጋድሎ ታሪክ የሁለቱን ፓርቲዎች የጠበቀና የቆየ ትስስር አደባባይ አውጥተዋል። ከሁሉ የውጭ ፖሊሲ አግባቦች የጸና ስለመሆኑ ያደረጉትን የድንበር ስምምነት፣ የድንበሮች ደህንነትና የህዳሴው ግድብ ስምምነቶች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሌሎች በቅርቡ የተፈረሙ አስራ አራት የኢኮኖሚና የንግድ ትብብሮች እንዳሉ ሆነው።

እዚህ ላይ አንድ የህዳግ ማስታወሻ ማከል የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በሙባረክ ግድያ ማግስት ወያኔ ኢህአዲግና ሻዕቢያ ባንድ ላይ ሆነው የዑመር አልበሽርን መንግስት ለማስወገድ የሞከሩበት ጊዜ ነበር። በስልጣን ከነበረው የአሜሪካ መንግስት ጋር በመተባበርና የደቡብ ሱዳን አማጺያንን በማስታጠቅ። ምናልባት የካርቱሙ ስርዓት መንፈሳዊ (ርዕዮተዓለማዊ) መሪ የነበረው ዶክተር ሃሰን አል ቱራቢ ከተማሪው ከአል በሺር ጋር ተጣልቶ ከስልጣን መወገዱ እንደገና ታርቀው ወዳጅነታቸውን በጽናት ለመቀጠል አስተዋጽ አድርጓል የሚል ግምት አለ።

ከሁሉ በላይ ግን በዓለም አቀፍ ወንጀል ፍርድ ቤት (International Court of Crime ) አማካኝነት በሱዳኑ ፕሬዚዳንት ላይ የተቆረጠው መያዣ የሁለቱን የትግል አንድነት የፈተነበት አጋጣሚ ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት አል በሺርን "በጥፍርና በጥርስ" ከመከላከል አልፎ የፍርድ ቤቱ ክሶች ለይተው ያነጣጠሩት በአፍሪካውያን መሪዎች ላይ በመሆኑ የአፍሪካ መንግስት በጋራ እንዲቋቋሙት አስተባብሯል። ይህም ያለ ምክንያት አልነበረም። "የእኩያህ ጸጉር ከተላጨ አንተም ባለተራ መሆንህ ተረዳ" ይላሉ አፋሮች ሲተርቱ። "በጥፍርም በጥርስም ለስልጣን የሚተጋ መንግስት" ያሉት ግን አፋሮች አይደሉም። የተቃዋሚ ጎራ ብቸኛ የኢትዮጵያ ፓርላማ አባል እንጂ። አባባሉ ሁለቱ ገዥ ፓርቲዎች ከስልጣን ጋራ ያላቸውን ተዛምዶ ገላጭ ነው።

ወያኔ/ኢህአዲግ "በጥፍርም በጥርስም" ስልጣን ነው ምኞቴ፣ ወይ ስልጣን ነው ሃይማኖቴ፣ ስልጣን ነው ማተቤ፣ ስልጣን የልብ ጽላቴ የሚል መፈክር ሙጥኝ ያለ ይመስላል።

በተለይ ከሁለት ኩኔቶች በኋላ። አንዱ ሃገራችን ላይ የተካሄደው የ 97ዓ.ም. ምርጫ ውጤት ነው። ሌላው በአካባቢያችን የአረቡ ዓለም ህዝባዊ መነሳሳት ነው። እነዚህ ሁለቱን ክስተቶች ተከትሎ መንግስት በርካታ አፋኝ ህጎችና አተረማመሽ ንድፎች በተከታታይ እንዳሻሽጎደጎደ ይታወቃል። የፕሬስ ህግና የማህበራት ህግ በግንባር ቀደም ይጠቀሳል። በፕሬስና በፕሬስ ውጤቶች በተፈጸመው ዕመቃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ20 ጋዜጠኞች በላይ ሃገር ጥለው ተሰደዋል። በርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች ከህትመት ውጭ ሆነዋል። በተሰደዱት ጋዜጠኞች ላይ በጎረቤት ሃገሮች የወያኔ ደህንነት ክትትል እያደረገባቸው ነው የሚሉ ዘገባዎችም ተመልክተናል።

የግንቦት 7 ዋና ጸሃፊ የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ታግቶ መውሰድም የየመን የደህንነት ሃይሎች በገንዘብ ሃይል በመደለላቸው ብቻ ሳይሆን ከላይ በሰፊው የተመለከትነው የጸረ-ሽብር አጋርነትና ሽርክና ምሳሌ የሆነው የሳንዓ ሃገሮች ትብብር ውጤትም መሆኑ ነው። ጂቡቲም የዚሁ ህብረት አባል ነች። የኢትዮጵያ ስደተኞችን እንደገና ወደ ሃገራቸው በመመለሱ ተግባር ተባባሪ ናት። "በጥርስም በጥፍርም" በስልጣን መዝለቅ የተባለው ፈርጀ ብዙ አተረማማሽ ዕቅድ አንዱ ክፍል ነው። የጸረ ዓለም አቀፍ ሽብር ዘመቻው አጋርነት።

"የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ" በተባለው ግልገል መጽሐፍ የ"አገራችንን" ውስጣዊ ችግሮችና የአደጋ ተጋላጭነታችንን ለአገራዊ ደህንነትና ህልውናችን ያላቸው ትርጉም ተገቢውን ትኩረት ሳያገኙ ቆይተዋል ይላል። መስመሩ የእኔ ነው። ተገቢውን ትኩረት ያላገኘው ባለፉት ስርዓቶች መሆኑ ነው። ተገቢውን ትኩረት ሲያገኝ ምን እንደሚመስል ከላይ በሰፊው ተመልክተናል። ስለ ባህር በር፣ ጂዮ-ስትራተጂካዊ ትርጉም የሁለቱ መሪዎችን አመለካከት ጎን ለጎን አስቀምጬ ይሄንን ጽሁፍ ላሳርግ።

አንዱ የ‹ባለ ራዕዩ› መሪ፣ ሌላው የኤርትራ የግንጠላ መሪ ዑስማን ሣሊ ሕሳቤ አመለካከት ነው። አቶ መለስ "የባህር በርና ወደብ እንደማንኛው ዕቃ

***ወደ ገጽ 36 ዞሯል***

# ከፕ/ር አለማየሁ ገብረ ማሪያም ጋር የተደረገ .....

*ከገጽ 33 የዞረ*

***ፕ/ር አለማየሁ፡-***ይህን ጥያቄ የምመልሰው ከዩናይትድ ስቴትስ ህግ አንጻር ነው። ለምሳሌ አንድ በሰብአዊነት ላይ በተፈጸመ ወንጀል ተጠርጣሪ የሆነ (ች) በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ ባለስልጣን በዩናይትድ ስቴትስ ጥገኝነት ወይ የመኖርያ ፍቃድ ለመጠየቅ፣ ሌላው ቀርቶ ለጉብኝት እንኳን ቢመጣ (ብትመጣ) በወንጀል የመከሰስና በሲቪል ህጉም የመጠየቅ ዕድሉ(ሏ) ከፍተኛ መሆኑን ማወቅ ይኖርበ(ባ)ታል። የቅርብ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ቶማስ ጁኮንቴ ዌዊዩ የተባለውን የላይቤሪያ ባለስልጣን ማንሳት ይቻላል። ይህ ሰው ከ2003 ዓ.ም. በፊት በቀድሞው የላይቤሪያ ወታደራዊ መሪ መንግስት ውስጥ በሚኒስትርነት አገልግሏል።

በቅርቡ ደግሞ በላይቤርያ የርስበርስ ውጊያ ወቅት በተፈጸሙት ወንጀሎች ላይ በነበረው ሚና ምክንያት በጦር ወንጀልና በሰብዐዊነት ላይ በተፈጸሙ ወንጀሎች ለመከሰስ በቅቷል።

ዛሬም የጡረታ ጊዜዬን በአሜሪካ አሳልፋለሁ የሚል ሀሳብ ያላቸው የኢትዮጵያው አገዛዝ ባለስልጣናት ካሉ በአሜሪካ ፌደራል እስር ቤት ውስጥ ስለሚጠብቃቸው ረጅም የጡረታ ጊዜ ሊዘጋጁበት ይገባል። የዘረፉትን ሚሊዮኖችም ዩ ኤስ ኤ ውስጥ የማጣጣም ዕድላቸው የመነመነ ነው።

***አሻራ፡-ስለ ግዜዎት በጣም እናመሰግናለን !!***

***ፕ/ር አለማየሁ፡-*** እኔም ስለተሰጠኝ ዕድል አመሰግናለሁ!

# የመጽሃፍ ቅኝት .....

ከገጽ 23 የዞረ

መጽሃፍ አሉታዊ ገጽታ እያሳየ መጓዙ ነው። ይህ አካሄድ ለወቅቱ አንባቢ ብቻም ሳይሆን መጪው ትውልድም ኢህአዴጋዊ የታሪክ ድርሳናትን ውሸት አመሳክሮ ይደርስበት ዘንድ ትልቅ አስተዋጾ አለው።

እዚህ ላይ አንድ ላነሳው የምሻው ጉዳይ፡- "የቃሊቲው መንግስት" የሚለውን በጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና የተጻፈ የምርጫ 97 ክስተቶችን በነቂስና በማስረጃ የተረከ መጽሃፍ ነው። የቃሊቲው መንግስትንም እንዲሁ ለመቃኘት ሞክሬ ነበር።

በቅኝቴ ካነሳሳኋቸው ነጥቦች ዋናው ፤ የሲሳይ አጌና "የቃሊቲው መንግስት" ምርጫ 97ን አስመልክተው ከተጻፉ ጥቂት የማይባሉ መጽሃፍት በተሻለ ፤ ትርከቱን በበቂ ማስረጃ ያስደገፈ መሆኑን መግለጼ ነው። ለዚህም እንደ ማነጻጸሪያ የጠቀስኩት "የሁለት ምርጫዎች ወግ"ን ነበር። ስለ አንድ የምርጫ 97 ክንዋኔና ሂደት ሁለት ብዕሮች የተለያየ ታሪክ ጽፈዋል። ሲሳይና አቶ በረከት ። የዛሬው አንባቢ የትኛው መጽሃፍ ለእውነታው የተጠጋ እንደሆነ መለየት ላይቸግረው ይችላል። ከዛሬ 30 ና 40 ዓመት በኋላ ያለው ትውልድ ግን መቸገሩ አይቀርም። ሲሳይ መጽሃፉን በሚታይና በሚዳሰስ ማስረጃ ማስደገፉ የአቶ በረከትን መሰል የፈጠራ ድርሳን በነገው ትውልድ ፊትም እንዲመክን አድርጎታል ስል መግለጼን አስታውሳለሁ።

የኤርምያስ አቀራረብም የአቶ በረከትን መጽሃፍ ልቦለድነት (ፖሮፓጋዳነት) ከቅርብ ርቀት በማጋለጥ የነገው ትውልድ በምርጫ 97 ክስተቶች ዙሪያ ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲኖረው የበኩሉን አስተዋጾ አበርክቷል።

ባጠቃላይ የመለስ ትሩፋቶች አጻጻፍ ስልት በኔ ምልከታ ውብ ሆኖ አግኝቸዋለሁና። ኤርምያስ ሆይ ቀጣዩንም በጉጉት እንጠብቃለንና በርታ ብዬ ልለፈው።

## ተዓማኒነት

ደራሲው በሚተርክልን ታሪክ ውስጥ እንደ ባለታሪክ የተቀመጠበት ወንበር ለዙፋኑ ቅርብ መሆኑ ለተነባቢነቱ የሰጠውን ጉልበት ያህል ለታዓማኒነቱም ሊሰጠው አይችልም። የደራሲው ተዓማኒነት የሚመዘነው "እውነቴ" ብሎ ባቀረበው ጭብጥና ጭብጡን እንዲያሳዩ በሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ብቻ ነው። ስለሆነም የደራሲውን "እውነቴ" ካቀረባቸው ማስረጃዎች ጋር አመዛዝኖ የራስ ግንዛቤ መያዝን በተመለከተ ለእያንዳንዱ አንባቢ ልተውና እንደ ቅኝት አቅራቢነቴ የራሴን አንዳንድ ነገር ላንሳ፡-

አንድ ደራሲ የሌላ ሁለተኛ አካልን ታሪክ ሲጽፍ የሚኖረው ነጻነትና ራሱ ተዋናይ የሆነበትን ታሪክ ሲጽፍ የሚኖረው ነጻነት ይለያያል። የሌላ አካልን ታሪክ ሲጽፍ ነጻነቱም ለቀቅ ያለ ጭንቀቱም የሚጽፈው ታሪክ ትክክለኛ/እውነተኛ ስለመሆኑ ብቻ ነው። አንባቢም ከደራሲው የሚጠብቀው በትርከቱ የተካተቱት ክስተቶች በማያሻማ መረጃ መደገፋቸውን ብቻ ነው።በሌላ በኩል አንድ ደራሲ ራሱ ተካፋይ ስለሆነበት ታሪክ ሊጽፍ ሲነሳ አንባቢም ተጨማሪ ጥያቄዎችን ያነሳል ። ሚዛናዊነት፤ ተአማኒነት፤ አድሏዊነት... የመሳሰሉትን። የኤርምያስንም መጽሃፍ የምናየው ከዚህ አኳያ ነው።

ወደ ገጽ 39 ዞሯል

# አንዳርጋቸው በኔ

ከገጽ 31 የዞረ

## አትክልት አሰፋ—ቫንኮቨር ካናዳ

የአቶ አንዳርጋቸውን መታፈን ከሰማሁ ጊዜ ጀምሮ የሚሰማኝን ስሜት ለራሴ ለመንገር ተቸግሬያለሁ። በተለይ በእነኚህ በጭካኔ የተሞሉ ሰዎች እጅ መውደቃቸውን ማሰብ ህመሜን ያጠናብኛል። በአጠቃላይ ግን ለዚህች ሀገር በአመኑበት መንገድ ለመሞት ቆርጠው የወሰኑ ሰው ስለሆኑ ያንን ጽናታቸውን በማሰብ እረጋጋለሁ።

ህወሃት መራሹ ኢህአዴግ ቆራጥና ትጉ መሆናቸውን ስላየ ይመስለኛል እስከማስገደል የደረሰ ሴራ ሲያሴር የነበረውና ጠልፎ በመውሰድ ከሚከተለው ቁጣ ጋር መፋጠጥን የመረጠው። የአቶ አንዳርጋቸው ጉዳይ ኢትዮጵያዊያንን ያስቆጣ ብቻ ሳይሆን የአላማችንን ግብ እንድናጠናና እንድንሰባሰብ ሃይል ሆኖናል። ቆራጥ መሆን ወያኔን እንዴት እንዳስፈራው በግልጽ አይተናል።

አቶ አንዳርጋቸው የበኩላቸውን አድርገዋል። አላማቸው የሆነውን ዲሞክራሲ የሰፈነባት፣ የዜጎች መብት የሚከበርባትና ፍትህ የነገሰባት ኢትዮጵያን ለማየት በሚችሉት መንገድ ሀሉ ተንቀሳቅሰዋል። ተመሳሳይ ህልም ያለው በየትኛውም መንገድ የተሰለፈ ዜጋ ሁሉ ቆራጥና ትጉህ መሆን እንደሚገባው አስተምረዋል ብዬ አምናለሁ።



*ከገጽ 38 የዞረ*

ራሱ ግንባር ቀደም ተዋናይ በነበረበት የተፈጸመን የጥፋት ታሪክ ሊነግረን ሲነሳ ተዓማኒነቱን እንጠይቃለን። ሚዛናዊነቱን እንፈትሻለን።

በበኩሌ ኤርምያስ በመለስ ትሩፋቶች ላይ የነገረኝን ሁሉ ልቀበል ተገድጃለሁ። በሌላ አገላለጽ ለጥርጣሬ የሚገፋፋ ምንም ምክንያት አላገኘሁም። ለምን? ግልጽ ላድርገው፡ ኤርምያስ በዚህ መጽሃፉ ገዢው ፓርቲ በአዲስ አበባ ከተማና ህዝቧ ላይ የፈጸመውን ዝርፊያና ምዝበራ፤ ኢ.ሰብአዊ፤ ኢ.ዲሞክራሲያዊና ኢፍትሃዊ ተግባራት በዝርዝር ገልጾልናል። መነሻውም ለህሊና ወቀሳው ምላሽ ሰጥቶ እፎይታ ማግኘት በመሆኑ ሊደብቀው ወይም ሊሸፍነው ይፈልጋል ብዬ ላስብ የምችለው የኢህአዴግ ህጸጽ አይኖርም። በተካፈለባቸው የጥፋት ተግባራት ሁሉ ሲጸጸት እንጂ ከደሙ ንጹህ ነኝ ሲል አላተስተዋለም። ለ12 እሩብ ጉዳይ ስርዓቱን ከድተው ጲላጦሳዊ መግለጫ ከሚያዘንቡ ባለስልጣናት ለየት ብሎ ፤ ሲቦካም ሲጋገርም አብሬ ነበርኩ ማለቱ ለተዓማኒነቱ ትልቅ ጉልበት ሰጥቶታል። ስለዚህ የነገረንን የማናምንበት ምክንያት አልተወልንም። የማናምነው ያልነገረንን ብቻ ይሆናል።

የነገረኝን ሁሉ አምኛለሁ ስል፡- ጽሁፉን ሳነብ በተደጋጋሚ ብቅ ይልብኝ የነበረ ጥያቄ እንደነበርና ጥያቄው አሁንም ቢሆን ከውስጤ አለመውጣቱን ሳልደብቅ ነው። ኤርምያስ ከጥፋት አራማጆቹ ጋር ጥፋት አስፈጻሚ ሆኖ በዘለቀባቸው 12 ዓመታት ውስጥ በየትኛው ደረጃ ነው መጸጸት የጀመረው? ከመቼ እስከ መቼ ባለው ግዜ "አምኜበት" ነው የሰራሁት ይላል? በጥፋት ባቡር ላይ መሳፈሩን አውቆ ከባቡሩ ለመውረድ አመቺ ጣቢያ ይጠብቅ የነበረው ከመቼ ጀምሮ ነው? እያልኩ መጠየቄ አልቀረም። ያም ቢሆን ግን በዚህ መጽሃፉ ተዓማኒነት ላይ የሚያጠላው ጥላ ያለ አይመስለኝም። ዋናው ስህተቱን ማየት መቻሉ እስከሆነ ድረስ። ወደፊት የምጽፈው አለ ስላለ ለምን ስለዚህ አልጻፈም? በሚል የሚነሳ ጥያቄም ሊኖር የሚችል አይመስለኝም ። ባይሆን ትርከቱን አጠናቆ ብዕሩን እስኪሰቅል ድረስ ልንታገሰው ይገባል።

**<u>የመጸሃፉ ተደራሲ ማነው?</u>**

ጥቂት ስለ ጸሃፊው በሚል ርዕስ በመጽሃፉ መጀመሪያ ክፍል፤ አሳታሚው ደራሲው ኤርምያስ ይህን መጽሃፍ የጻፈው " ኢትዮጵያ የምትባል ትልቅ ሃገር ለመረከብ በትግል ላይ ላሉና በየትኛውም መስመር ለተሰለፉ ወጣቶች ነው" በማለት ተደራሲው ማን እንደሆነ ይነግረናል። ኤርምያስም በተመሳሳይ መልክ በተለይ ኢህአዴግ ውስጥ ላሉ ወጣቶች እንደጻፈው ገልጾልናል። በርግጥም አዲሲቷ ኢትዮጵያ የተፈጠረቺው ግንቦት 20 1983 እንደሆነ በስርዓተ ትምህርት ተቀርጾ እየተነገረው ካደገው ወጣት የበለጠ የኢህአዴ.ግ የጥፋት አካሄድና ውስጠ መርዝነት ሊመሰከርለት የሚገባ የህረተሰብ ክፍል የለም። ተደራሲው ወጣቱ ክፍል በመሆኑ እስማማለሁ ።

**<u>የመጽሃፉ ፋይዳ</u>**

የመጽሃፉ ፋይዳ በአጭሩ ኢትዮጵያን እንደ ሃገር ለማጥፋት የሚሰሩትን ዘረኞች አካሄድ ጠንቅቀን አውቀን፤ አደጋውን ተረድተን ማድረግ ያለብንን እናደርግ ዘንድ ማንቃት ነው።

**መጽሃፉ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ ከተጻፉ መጽሃፍት በምን ይለያል? ምንስ አዲስ ነገር ይዟል?**

በኔ እይታ የኤርምያስ መጽሃፍ ከሌሎች መጽሃፍት የሚለይበት ዋና ይዘቱ፡- ገዢው ፓርቲ ላለፉት 20 በላይ አመታት በተለያዩ ጊዚያት፤ ቦታዎችና ጉዳዮች ላይ እየቀመመ የበተናቸውን መርዞች ከነንጥረ-ነገሮቻቸው ዝርዝር (Ingredients used in Poison recipes) ይዘትና የተቀመሙበትን ዓላማ በግልጽ መያዙ ነው።

ላለፉት በርካታ ዓመታት አገዛዙ በየደረጃው የሚቀምማቸውን ሃገርና ህዝብ አጥፊ መርዞች አደገኝነት የተረዳው ኢትዮጵያዊ የራሱን መከላከል እያደረገ ቆይቷል። መርዞቹ ለምን? በማን? እንዴትና መቼ እንደተቀመሙ ከላብራቶሪው የወጣ መረጃ ያገኘነው ግን አሁን ነው። በደፈናው ከላይ ያስቀመጥኩትን ከኤርምያስ መጽሃፍ አንዳንድ ዋቢ ጠቅሼ ለማሳየት ልሞክር።

**<u>የአዲስ አበባ መሬት ቅርምት</u>**

የጥፋቱ ቅብብሎሽ ከመመሪያ ቁጥር አንድ ወደ ሁለት በሚለው በመጽሃፉ ክፍል ሶስት (ገጽ 103-129) አዲስ አበባ ከተማን የተቀራመቱበትን ሂደት በዝርዝርና በግልጽ ያስረዳል። በዚህ አስረሽ ምቺው ዘረፋ ብዙዎች ተጠቃሚ ቢሆኑም የአንበሳውን ድርሻ የወሰዱት ግን የህውሃት አባላት መሆናቸውን እንዲህ ሲል አመላክቶናል። ***" የድራማው ከፊል ገቢር እንዲህ ነበር ፦ አማረ አሰግዶም የህውሃት ባለሃብቶችን መፍጠርና ማገዝ በሚለው ቡድን ውስጥ ተደራጅቶ ከሚንቀሳቀሱት ቁልፍ ሰዎች አንዱ ነበር። ከመሬት ጋር በተያያዘ ለህውሃት ሰዎች የሃብት ምንጭ ሆነ። ለራሱም አልቦዘነም።.."(ገጽ 116)***

ይህ ድራማ አብይ አላማው ሃብትን ወደ አንድ ዘር ማሸጋገር ነው።

ተጓዳኝ አላማው ደግሞ በየአካባቢው ለዘመናት አብሮ የኖረውን የአዲስ አበባ ህዝብ በታትኖ አብሮ በመኖር የዳበረውን መተሳሰብና መተባበር፤ መተማመንና ጥቃትን አብሮ የመመከት ልምድ ማጥፋት ነው።

አዲስ አበባ ውስጥ የዘር ፖለቲካ እንዳልሰራ መለስ ዜናዊ ራሱ በይፋ እንደተናገር ኤርምያስ ነግሮናል ። ስለዚህ ዘር ያልከፋፈለውን የአዲስ አበባን ሕዝብ ለመከፋፈል ይህን መሰል የጥፋት ቅብብሎሽ አስፈልጓል።

የመለስ ትሩፋቶች በጥቅል የምናውቃቸውን በዝርዝር ከማቅረቡ በተጨማሪ፡- በርካታ አዳዲስ መረጃዎችንም አጭቋል።

በተለያዩ ባለስልጣናት መካከል ያለውን ሽኩቻ ለመጀመሪያ ጊዜ በግልጽ ያስነበበ መጽሃፍ ነው። የበረከትና የአርከበን መዘራጠጥ ልብ ይሏል።

የካሳንችሱን መንግስት ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ ያወቅኩት ከኤርምያስ መጽሃፍ ነው።የጉራጌ አብዮትም እንዲሁ ለኔ አዲስ ታሪክ ነው። ባጠቃላይ "የመለስ ትሩፋቶች" በየትኛውም የመንግስት ሚዲያም ሆነ ነጻ ጋዜጦች ላይ ያላነበብናቸው፤ ልናነባቸውም የማንችላቸው እጅግ በርካታ አዳዲስ መረጃዎችን አካቷል። ይህ መጽሃፍ የኤርምያስን ቀጣይ ስራ ብቻም ሳይሆን ቀጣይ ቃለ ምልልስ ሁሉ በጉጉት እንድንጠብቅ ያደርገናል እላለሁ። ለዚህ ተግባሩም እንሆ የግሌ ምስጋና ይድረሰው ።

*ወደ ገጽ 24 ዞሯል*







እነኚህንና ሌሎችንም መጽሃፍት
ከኢሳት አንላይን ስቶር መግዛት ይችላሉ !!

# Gabriel's
## Family Day Care
Providing the ultimate care & education

Gabriel's
Family Day Care Pty Ltd

Providing the ultimate care & education for families

Don't know where to start & how to start,! don't worry, just CONTACT US NOW

become an educator today

CCB and CCR available via Centrelink

Certificate III in Early childhood & Care, Asthma & anaphlaxis Training

Trained and qualified educators & co-ordinators

Multiculturalism is our identity & corporate culture

Don't miss-out on this great opportunity

ENROL YOUR CHILD TODAY

Now Recruiting Educators & Enroling Children

### Our Services

- Full-time & part-time care
- Before & after school care
- Casual & emergency care
- Weekend & overnight care

### We are

- Approved childcare service provider
- Have the best qualified & skilled educators
- Have the ultimate service in care & education for the children under our care

1 / 568 Hume Highway Yagoona NSW 2199

info@gabriel

M 0431 929975